ቅ ደ ም-ተ ከ ተ ሳ ዊ

# የክርስቶስ ሕይወት

## ቅጽ 1
## ከክብር እስከ ገሊላ

በማርክ ኢ. ሙር

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

Copyright © 1996
College Press Publishing Company
2nd. Printing (1st. revision) 1997
5th. Printing (2nd. Revision) 2004
Moore Mark E. (Mark Edward) 1963 –
The Chronological Life of Christ/Mark E. Moore

Includes text from : The NIV Harmony of the Gospels/
Robert L. Thomas, editor and Stanley N. Gundry,
Associate Editor

Contents : V.1 From Glory to Galilee

ደራሲ ፡ ማርክ ኢ. ሙር
ትርጉም ፡ ተስፋዬ መስፍን
አርታኢያን ፡ ናሁሰናይ አፈወርቅ እና ሚናስ ብሩክ
የኮምፒውተር ጽሑፍ ፡ ፍቅርተ ጸጋዬ

አሳታሚና አከፋፋይ ፡-
ኤስ. አይ. ኤም ኢትዮጵያ
የመ.ሣ.ቁ. 127
አዲስ አበባ
የመጀመሪያ እትም ፡ 2000 ዓ.ም

# በህደግ ላይ የቀረቡ ምልክቶች መፍቻ


ምሳሌዎች


ጸሎት (ዓበይት ትምህርቶችና ምሳሌዎች የ ቀረቡበት)


የተፈጸሙ ትንቢቶች


የክርስቶስ መለኮትነት (ራሱ ያረጋገጠበትና ሌሎችም የመሰከሩለት)


የነገረ-ፍጻሜ ትምህርቶች


ፈውሶችና ሌሎች ታምራቶች


የእግዚአብሔር መንግሥት/ቤተ ክርስቲያን

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| ምድብ አንድ……ጀማሪዎች | 5 |
| ምድብ ሁለት……ሁለት መለኮታዊ ልደቶች | 44 |
| ምድብ ሶስት……ቀደምት የኢየሱስ ክርስቶስ ዓመታት | 73 |
| ምድብ አራት…… የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት | 116 |
| ምድብ አምስት… ከዮሐንስ ወደ ኢየሱስ መሸጋገር | 132 |
| ምድብ ስድስት… የገሊላ አገልግሎቱ | 208 |
| ምድብ ሰባት…… ከገሊላ ያደረገው ስንብት | 522 |
| ምድብ ስምንት… የክርስቶስ የመጨረሻው የይሁዳ | 675 |


አገልግሎት

## መግቢያ

ወደር የሌለው የናዝሬቱ ኢየሱስ ከሚታሰበው በላይ ልዩ ነው። ይህ አራት ምስክሮች የተናገሩት የእርሱ ታሪክ ነው። ስማቸውም ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ይባላል። «የተሟላ የታሪኩን ጉላ ያለ ገጽታ» ማግኘት እንዲቻል በዚህ ቅጽ የአራቱንም ምስክርነት አቀናጅተን አቅርበናል። ያም ሆኖ ግን እንደዚያ ማድረግ የራሱ ችግር ሊኖረው እንደሚችል እንረዳለን። ለምሳሌ ያህል እያንዳንዱ የወንጌል ጸሐፊ በራሱ የአጻጻፍ ስልት መጽሐፉን በጥንቃቄ አቀናብሮታል። እያንዳንዱ የራሱ የሆነ የአጻጻፍ ለዛ አለው። እንግዲህ አራቱንም በአንድነት ስናቀናጅ እያንዳንዱ የተለየ የሚያደርገውን ልዩ ባህርይ ልናሳጣው እንችላለን። የክርስቶስን ሕይወት በዚህ መልኩ አቀናጅቶ ለማቅረብ በሚደረግ ሙከራ ላይ በአሁኑ ወቅት አንዳንዶች የሚሰነዝሩት ትችት ይህን መሳይ ነው።

ይሁን እንጂ፣ አራቱን ወንጌሎች በአንድነት በማቀናጀት አንድ ወጥ አድርጎ ማቅረብ አስፈላጊ የሚሆንበት በቂ ምክንያቶችም ይኖራሉ-

(1) እያንዳንዱ ወንጌል የራሱ ለዛ አለው። እንደዚሁ ከሌሎች ነጥለን በማንበብ የዚያን ወንጌል ጣዕም ማጣጣም እንችልም። ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ጊዜ የማቴዎስ ወንጌልን ዐቢይ ሐሳብ ለመረዳት የተሻለው መንገድ የእርሱን አቀራረብ ከሉቃስና ከማርቆስ ጋር ማነጻጸር ነው። በሌላ አነጋገር አራቱንም ወንጌሎች አቀናጅቶ ማጥናት የእያንዳንዱን ወንጌል ልዩ ባህርይ ይበልጥ ጎልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል እንጂ አያደበዝዘውም።

(2) ወንጌሎቹ ሥነ ጽሑፋዊ ውጤቶች ብቻ አይደሉም። በወንጌሎቹ ውስጥ የምናገኘው የእውነተኛ ታሪኮችን ዘገባ ነው። ስለሆነም በፍርድ ቤት ምስክሮችን በምንመለከትበት ዓይነት ተቀራራቢ ለወንጌሎች ተመሳሳይ ግምት ሰጥተናል። የሚሰጡትን ምስክርነት

በማቀናጀት በይበልጥ የተሟላና ዘርዝር ያለ የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት ታሪክ መመልከት እንችላለን።

(3) እያንዳንዱን ወንጌል በተናጠል ማጥናት የዚያን ወንጌል ጸሐፊ ነገረ መለኮታዊ ግንዛቤ አጉልቶ ያሳየናል። በሌላ በኩል አራቱንም ወንጌሎች በአንድነት ማጥናት ቅደም ተከተላዊ በሆነ ደረጃ የኢየሱስን ሕይወት በጉልህ ያሳያል። ያም ማለት የአገልግሎቱን ዕድገት እንዲሁም ያለፈበትን ውጥረቱንና ስኬቱን ማየት ያስችለናል ማለት ነው። በአራት መነጽሮች ኢየሱስን ስንመለከት በአንድ መነጽር ብቻ ተጠቅመን በፍጹም ልናየው በማንችለው ሁኔታ እናየዋለን። ምናልባትም እግዚአብሔር አራት ወንጌሎችን የሰጠን በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

(4) አራቱንም ወንጌሎች አቀናጅቶ ማጥናት አዲስ አይደለም። ሰባኪዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ አዘጋጆችና ወንጌሎችን የሚያጠኑ ተማሪዎች በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ከሌሎች ወንጌላውያን ጽሑፎች ተጓዳኝ ምንባቦችን ሲወስዱ ኖረዋል። «ሰው ሁሉ ያደርገዋል» የሚለው አባባል ይህን የመሰለውን ዓላማን መሠረት ያደረገ ቅንጅታዊ አቀራረብን ትክክለኛነት ሊያረጋግጥ ይችላል። በተጨማሪም፣ ቅንጅታዊ የአጠናን መንገድ የረጅም ዘመን ክቡር የአሠራር ልምድን የተከተለ መሆኑ መታወቅ አለበት። *Study in the Life of Jesus Christ* ከተሰኘው ከአር.ሲ. ፎስተር መጽሐፍ አንስቶ እስከ *The Four- Fold Gospel* እስከ ተሰኘው የጂ ደብልዩ ምክጋርቪስ መጽሐፍ እንዲሁም ከትዝታ ወደ ኋላ መለስ ስንል እስከምናገኘው የቴሺያን *Diatessaron* ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እነዚህን አራት ባለ ግርማ የኢየሱስ ምስሎችን ሲያነጻጽሩ ኖረዋል። እንዲያውም ሉቃስ ምናልባትም ዮሐንስም ጭምር የጻፉት ሌሎች ወንጌሎችን በማጣቀስ ነበር የሚል መከራከሪያ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

## የተለየ የሚያደርጉት ገጽታዎች

ይዘን የቀረብነው በቶማስና ገንድሪ[1] የተዘጋጀው NIV harmony ተጓዳኝ ነው። በእርግጥ የNIV harmony የወንጌል ምንባቦችን በአራት ዐምዶች አቅርቧቸዋል። እኛ ግን በአንድ በማጠጋጋት አጠር ያለ ማብራሪያ አክለንበታል። ማብራሪያዎቹ መንታ ዓላማ አላቸው። የታቀዱት የዐውዱን ሐሳብ ትርጉም ለማብራራት መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም ከዚያ ባለፈ መልኩ ዓላማቸው አንባቢዎች በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ማየት እንዲችሉ ማድረግ ነው። በዚያን ዘመን ከኢየሱስ ጋር ስትራመዱ የፓልስታይንም የመንገድ አቧራ በእግራችሁ (በጫማችሁ) ላይ ያለ እስኪመስላችሁ ድረስ እውን የሆነ ምስል ሥለን እንደምናቀርብላችሁ ተስፋ እናደርጋለን።

ከአራቱም ወንጌሎች የተወሰዱት ምንባቦች በአንድነት ከመቀረባቸው በተጨማሪ እንደ አንድ «ወጥ ታሪክ» ማንበብ እንዲቻል በተለየ ዓይነት አጻጻፍ ተጽፈዋል። ማቴዎስን፣ ማርቆስን፣ ሉቃስንና ዮሐንስን ለመወከል ሲባል፣ ማቴ፣ ማር፣ ሉቃ፣ ዮሐ በሚሉ ረቂቅ ፊደሎች የተጻፉትን በማየት ብቻ አንብበው የትኛው ወንጌላዊ ምን እንደ ተናገረ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ይህም በአንድ ጊዜ አራቱንም ወንጌሎች ማንበብ ያስችላችኋል። እዚህ ላይ ግን በዚህ መልኩ ያቀናጃቸው ዐረፍተ ነገሮች ኢየሱስ በእውኑ የተናገራቸውን (i.e Jesus' *Ipsissima Verba*) ከማንኛውም ይልቅ በትክክል አቅርበዋል ማለታችን አይደለም። ይልቁንም በዚህ መልኩ መቅረቡ አራቱ ምስክሮች

---

[1] HarperSanFrancisco, Division of HarperCollins, 1988. በሰጡን ፈቃድ መሠረት መጠነኛ ልዩነት አድርገን የእነርሱን የክፍሎች አቀማመጥ መንገድ ተከትለናል።

በእያንዳንዱ ገጠመኝ ላይ ሊኖሩ የሚችሉትን ዝርዝር ጉዳዮች መመልከት ያስችለናል ማለታችን ነው አራቱም ወንጌሎች አጥጋቢ በሆነ መንገድ እውነቱን ይናገራሉ። ይሁን እንጂ የሚሰጡትን ምስክርነት በማነጻጸርና በማጣመር ሁኔታውን በተሟላና ባሸበረቀ መልኩ በድጋሚ ማቀናበር እንችላለን።

ግልጽ ማድረግ የሚገባን የዚህ መጽሐፍ ሌላ ገጽታም ይኖራል። ይህም የግርጌ ማስታወሻዎችን ይመለከታል። ዋነኛው ሐሳብ ገጾቹ ውስጥ ባለው ዝርዝር ተካትቶአል። ሆኖም ላቅ ያለ ችሎታ ያላቸው አንዳንድ ተማሪዎች የሚፈልጓቸው በርከት ያሉ ምሑራዊ ማብራሪያዎችና ማጣቀሻዎችም ይኖራሉ። ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ እነዚህን መሳይ መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻዎቹ ውስጥ በገጹ ግርጌ አስፍረናል።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። የልጁን የኢየሱስን ሕይወት ማጥናት ለእኔ ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ ስጦታ ነው። ይህ አስደሳች ሥራ የልቤን መንፈሳዊ ዝንባሌ ከፍ አድርጐታል። ይህ በእጃችሁ ያለው የእኔ የግሌ ከመሆን ይልቅ የእርሱ ጸጋ ውጤት ነው። መጽሐፉ ለእግዚአብሔር መልሼ የምሰጠው ቅንጣት ስጦታ ነው። መጽሐፉን ስታነቡ ወይም ስታጠኑ ከተባረካችሁበት እኔን እጅግ ያረካኛል።

ማርክ ኢ.ሙር

## ጥቅሶችን ለማመልከት

1. ምዕራፍና ቍጥርን ለመለየት (፥)
2. በአንድ ምዕራፍ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቍጥሮችን ለመለየት (፣)
3. በአንድ መጽሐፍ ላይ ምዕራፎችን፣ ወይም ከተለያዩ መጻሕፍት የተጠቀሱ ጥቅሶችን ለመለየት (፤)



# ምድብ አንድ
# ጅማሬዎች

**§ 1**
**የሉቃስ ወንጌል መግቢያ**
**(ሉቃ 1፥1-4)**

**[1]በእኛ መካከል ስለ ተፈጸሙት[1] ነገሮች ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸውን ያህል ጽፈውት ይገኛል፤ [2]ይህም ታሪክ ከመጀመሪያው አንሥቶ የዐይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች የነበሩት ያስተላለፉልን ነው። [3]ክቡር ቴዎፍሎስ ሆይ እኔም በበኩሌ ሁሉን ከመሠረቱ በጥንቃቄ ከመረመርሁ በኋላ ታሪኩን ቀደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፤ [4]ይህንንም የማደርገው የተማርኸው ነገር እውነተኛ መሆኑን እንድታውቅ ነው።**

*[1]በእርግጥ ስለታመኑት*

ከአራቱ ወንጌሎች የጸሐፊነትን ዓላማ በመግቢያው የገለጠ ሉቃስ ብቻ ነው። ስለ ሆነም የምጀምረው ከእርሱ ነው። በግሪኩ አዲስ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አራት ቁጥሮች በጥንቃቄ የተቀነባበረ አንድ ረጅም ዐረፍተ ነገር ሆነው ቀርበዋል። እንዲያውም አንዳንዶች በመላው የግሪኩ አዲስ ኪዳን ይህ ጥቅስ ከፍተኛ ጥራት ያለው ዐረፍተ ነገር ነው በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ። የተቀሩት ምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 2 የአረማይክ በሚመስሉ ሐረጎች የተሞሉና «ንጹሕ» ግሪክ አለመሆናቸው የሚገርም ነው። ስለሆነም ከቁጥር አንድ እስከ አራት ያሉት ሉቃስ ሐሳቡን የመሠረተባቸው መደበኛ መግቢያ ናቸው ማለት ነው። ይሁን እንጂ ቀጥሎ ባለው ክፍል ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተጠቅሞአል። ሉቃስ የተዋጣለት ጸሐፊ ነው። ገና ከጅማሬው አጻጻፉ ምሑራዊ ትኩረታችንን የሚስብ መሆኑን መረዳት እንችላለን!

ይህ በቁንጠኛ ሁኔታ የተጻፈ መግቢያ ቢሆንም ያልተለመደ ዓይነት አልነበረም:: በግሪክና በሒለናዊ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘንድ እንዲህ ዓይነት መግቢያ መጠቀም የተለመደ ነበር::[1] በሚያደርጉት ምርምርና ተአማኒነት ለአንባቢው ብቃታቸውን የማስተማመን ፍላጎት ነበራቸው:: ሉቃስም ወንጌሉን ለመጻፍ ያነሳሳውን ምክንያት (ቁ 1-2)፣ የማንነት ማስረጃዎቹን (ቁ 3) እንዲሁም ለየት ያለ ዓላማውን ይገልጻል::[2]

ሉቃስ ወንጌሉን መጻፍ ሲጀምር ያስፈረው ኤፒይዴፐር [*epideper*] የሚለው ቃል በእንግሊዝኛው መደበኛ ትርጉም (NIV) የእግሊዝኛውን የአጻጻፍ ዘይቤ ለመከተል ሲባል «ስለሆነም» ተብሎ በቍ 3 ላይ የቀረበ ነው:: በሉቃስ ይፋዊ መግቢያ ላይ ጉላ ስፍራን የያዘ በወቅቱ ታዋቂ የሆነ ቃል ነው::

ሉቃስ ለመጻፍ የተነሣሣው ከእርሱ በፊት በነበሩ ብዙዎች» ነበር:: እነዚህ ሰዎች ስለ ኢየሱስ መጻፋቸው ሉቃስ ለሚያቀርበው ትረካ ቀዳሚ ሁኔታዎችን አመቻችቷል:: በተጨማሪም የቪንሰንት (*Word Studies in the NT*, I:251) እንደሚለው ኤፒቼሪዮ (*epicheireo*) የሚለው ቃል በቃል ሲወሰድ፣ እጃቸውን ያሳረፉበት እንደማለት ሲሆን ቀደም ሲል ያደረጉት ሙከራ አለመሳካቱን የሚያመለክት ነው (Johnson, ገጽ 27-28 ይመ):: ምንም እንኳ ይህ ሊሆን የሚገባው አንደምታ ባይሆንም ሉቃስ አንዳች የጎደለ ነገር መኖሩን ይገነዘባል:: ይህም በጣም ሰፊ የሆነውን ተግባር እንዲፈጽም አነሳስቶት ሁለቱን መጻሕፍት ማለትም ሉቃስንና የሐዋርያት ሥራን ለማዘጋጀት አብቅቶታል:: እነዚህ

[1] በሔሮዶቱስ፣ በዲዮናስዮስ፣ በፖሊቢየስ፣ በሒፖክራተስ፣ በጆሴፈስ ወዘተ ሥራዎች የዚህ ዓይነት መግቢያ የተለመደ እንደ ነበር ከT.Callan, "The preface of Luke- Acts and Historiography," *NTS* 31 (1985): 576-581, ከH.J. Cadbury, "Commentary on the Preface of Luke-Acts," in *Beginnings*, ed. F.J. Foakes- Jackson እና K. Lake, 2:489-510 ይመ::

[2] D.J. Sneen, "An Exegesis of Luke 1:1-4 with Special Regard to Luke's Purpose as a Historian" *ExpT* 83 (1971): 40-43 ይመ::



መጻሕፍት የሚጀምሩት ከመጥምቁ ዮሐንስ ሲሆን ወንጌሉ ወደ ሮም ዘልቆ እስከ ገባበት ሁኔታ ድረስ ተከታትለው አቅርበዋል:: ሉቃስ ወደ ኋላ ተመልሶ የጀመረ ሲሆን ሌሎች ሦስት ወንጌላውያን ካቀረቡት ይልቅ ዘልቆ የሄደ ትረካ በማቅረብ ቀጥሏል::

ሉቃስ ለጽሑፍ ዝግጅቱ ሦስት ምንጮችን ተጠቅሞአል::[3] በመጀመሪያ፤ እርሱም ሆነ አንባቢዎቹ የሚያውቋቸውን ጉዳዮች ተጠቅሞባቸዋል - «*በእኛ መካከል ስለ ተፈጸሙት*» የሚለው የሚያመለክተው ይህንኑ ነው:: የዚህ ሐረግ ትርጉም ሉቃስ የተጠቀመበትን ግሥ በተሟላ መልኩ አያቀርብም:: ምናልባትም፣ «በእኛ መካከል ለፍሬ የበቁ ነገሮች ቢባል የተሻለ ይሆናል:: እንደ ታሪክ ዘጋቢነቱ ሉቃስ ስለ ተፈጸመ ድርጊት ብቻ አይነግረንም:: ከዚያ ይልቅ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳውንና ከሚጽፋቸው ነገሮች በስተ ጀርባ መለኮታዊ እቅድ መኖሩንም ጭምር ይጽፋል:: ሁለተኛ፣ ሉቃስ ቀደም ሲል የነበሩ ጽሑፎችን ተጠቅሞአል:: ቁጥር አንድ እንደሚገልጠው ቀደም ሲል ብዙዎች የኢየሱስን ታሪክ የተቻላቸውን ያህል ጽፈው ነበር:: ምናልባትም ይህ የማቴዎስንና የማርቆስንም ጽሑፎች ይጨምር ይሆናል::[4] ሦስተኛ፣ በዓይን ምስክሮች በቃል ሲተላለፍ የነበረ ምስክርነትም ነበር:: ይህ በቀላሉ ሊታይ አይገባውም:: ምስክርነታቸው ከታሪክ መጀመሪያ አንሥቶ እንደ ነበር ሉቃስ በአጽንዖት ይናገራል:: የተሟላ መረጃ የነበራቸውና በጣም የሚታመኑ ነበሩ:: እነዚህ ሉቃስ የዘረዘራቸውን ሦስት ምንጮች የማያገናዝብ የወንጌል አመጣጥ ዕንሰ ሃሳብ ከፍተኛ ስሕተት ላይ የመውደቅ ዕድል ይገጥመዋል::

[3] ከ R.H. Stein, "Luke 1:1-4 and *Traditionsgeschichte*." *JETS* 26/4 (Dec 1983): 421-430 ጋር ያነ::

[4] «ብዙዎች» የሚለው ማቴ እና ማር እንደማይጨምርስ ፒ. ፌሊክስ መከራከሪያ የሚያቀርቡ ቢሆንም (1) አንዳንድ የጎደላቸው ነገር መኖሩን በማየቱ፣ (2) በቁ 2 መሠረት ከሐዋርያቱ ምስክር የተለዩ በመሆናቸው ("Literary Dependence and Luke's Prologue." *MSJ* 8 1 [1997]: 61-82::

በተጨማሪም፣ እርሱ ራሱ የዓይን ምስክር አለመሆኑን ገና ከመጀመሪያው ግልጽ ማድረጉ የሉቃስን እውነተኛነት ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል::[5] ይህ የማይታመን የፈጠራ ታሪክ የሚጽፍ ሰው ሥራ ሳይሆን ቅንና እምነት የሚጣልበት ተመራማሪ ያቀረበው ነው::

ምርመራ ለሚለው ሉቃስ አስገራሚ ቃል ተጠቅሞአል:: የቃሉን አመጣጥ ስናጠና ጐን ለጐን እየሄደ መከታተል ማለት ነው:: ማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን በመያዝ እየተከታተለ የማያቋርጥ ጥያቄ የሚያቀርብ ዘጋቢን ሥዕል ያቀርባል:: ሉቃስ በጥንቃቄና በዝርዝር ምርምር ማድረጉን በአራት ቃላት ገልጿቸዋል::

1. *ሁሉን፦* ከአራቱ ወንጌሎች ሉቃስ ወንጌል ረጅሙና የተሟላ ይዘት ያለው ነው:: የሉቃስ ወንጌል ከሐዋርያት ሥራ ጋር ሲደመር የአዲስ ኪዳንን 27% ይሸፍናል:: ከጴጥሮስ ወይም ከዮሐንስ ሌላው ቀርቶ ከጳውሎስም እንኳ የበለጠ የምናነበው የሉቃስን ብዕር ወጤቶች ወይም የጽሑፍ ሥራዎች ነው:: ከሉቃስ ጽሑፎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ጅማሬዎች የተሟላ ግንዛቤ እናገኛለን::
2. *ከመጀመሪያው፦* የኢየሱስንና የዮሐንስን መወለድ አስመልክቶ የተሟላ ዝርዝር መረጃ ያቀረበልን ወንጌል ጸሐፊ ሉቃስ ብቻ ነው::
3. *በጥንቃቄ፦* «በትክክል» ቢባል የተሻለ ይሆናል:: ያደረገው ምርምር ጥንቃቄን፣ እቅጫዊ አቋምንና ትክክለኛነትን ያገናዘበ ነበር:: ከታሪክ ጸሐፊነቱ አኳያ ብዙዎች በሉቃስ ላይ ትችት አስተላልፈዋል፤ ሆኖም ይህን ያህል አልተሳካላቸውም ወይም በሥነ ቁፋሮ የተገኘው ማስረጃ የሚደግፋቸው ሆኖ አልተገኘም::
4. *ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ፦* የአተራረኩ ሁኔታ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ብቻ ሳይሆን ሥርዓትን የተከተለም ነበር:: ቃሉ የጊዜ ቅደም ተከተል አሰላለፍን የሚያመለክት ይመስላል (ከሉቃ 8፥1፤ የሐዋ ሥራ 3፥24፤ 11፥4 እና 18፥23 ጋር ያነጻጽሩ):: እንዲህ ሲባል ግን ዐቢይ ሐሳቡን ወይም ነገረ መለኮታዊ ዓላማውን ተዋፅዖ ለማሳካት ከቅደም ተከተላዊ አቀራረብ መንገዱ ዝንፍ አላለም ማለት ሳይሆን ቅደም ተከተላዊ አቀራረብን መከተሉን በመናገር ያፀና ወንጌል ጸሐፊ እርሱ ብቻ ነበር ማለት ነው:: የአራቱን ወንጌሎች ጥምረት በምንመለከትበት ጊዜ ሁሉ ይህን በአእምሮአችን መያዝ ይኖርብናል::

የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው እጅግ ክቡር ለነበረው ቴዎፍሎስ ነው:: ብዙ ጊዜ «ክቡር» የሚለው ማዕረግ የሚሰጠው ለፈረሰኞች (ለምሳሌ ባልደራሶች) ወይም ለአገረ ገዦች ነበር (ሐሥ 23፥26፤ 24፥3 ስለ ፊልክስ፣ ሐሥ 26፥25 ስለ ፊልጦስ ከሚናገረው አንጻር):: «ቴዎፍሎስ» ማለት፣ «የእግዚአብሔር ወዳጅ» ማለት ነው:: አንዳንዶች የዚህ ሰው ስም እግዚአብሔርን የሚወዱትን ሁሉ የሚወክል የፈጠራ አጠራር ነው ቢሉም «እጅግ ክቡር» የሚለው የአክብሮት መጠሪያ የሚያሳየው ተቃራኒውን ነው:: ይልቁንም የተጠቀሰው ሰው ወደ እምነት ሊያመጣው ወይም በእምነቱ እንዲጠነክር ሊረዳው የሚፈልገው የሉቃስ ወዳጁ ወይም በቅርቡ የተዋወቀው ሰው ሊሆን ይችላል:: ክርስትና ሕጋዊ ሃይማኖት መሆኑን ሉቃስ እያግባባው የነበረ ሮማዊ ባለ ሥልጣን (ምናልባትም በሮም የጳውሎስ ጠበቃ የነበረ ሰው ሳይሆን እንዳልቀረም ይታሰባል፤ ከሐሥ 28 ጋር ያነ):: ሌላው ሊሆን ይችላል ተብሎ ጠንካራ መከራከሪያ የሚቀርብበት ደግሞ ቴዎፍሎስ የመጽሐፉ

[5] ይሁን እንጂ ጆን ዌንሐም፣ "The Identification of Luke" *EQ* 63/1 [1991]: 3-44 እንደሚሉት ሉቃስ ከ70ዎቹ አንዱ (ምዕ 10)፣ በኤማሁስ መንገድ አብሮ የነበረ የቀለዮጳ ጓደኛ፣ በአንጾኪያ የነበረው የቀሬናው ሉኪዮስ (ሐሥ 13) እንዲሁም የጳውሎስ ዘመድ እንኳ ሊሆን እንደሚችል የመሟገቻ ሐሳብ አቅርበዋል::

ደጋፊ ወይም አሳታሚ ሊሆን መቻሉ ነው።[6] አንድ ጸሐፊ የመጽሐፉን ወጪ ለሚሸፍንለት ሰው በመታሰቢያነት መስጠቱ በዚያ ዘመን ያልተለመደ ጉዳይ አልነበረም። ይሁን እንጂ ሉቃስ እነዚህን ባለ ሁለት ቅጽ መጻሕፍት ያዘጋጀው ለቴዎፍሎስ ብቻ እንዳልነበር የዚያን ያህል እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ጽሑፉ በአድራሻ የተጻፈው ለዚህ ግለ ሰብ ቢሆንም ለሰፊው ለክርስቲያን ማኅበረ ሰብ እንዲደርስም ታስቦበት ነበር።

በመጨረሻም፣ በቁጥር 4 ስለ መጽሐፉ መሪ ሐሳብ እንመለከታለን፤ «የተማርኸው ነገር እውነተኛ መሆኑን እንድታውቅ ነው» (ከዮሐ 20፥31 ጋር ያነ)። ቴዎፍሎስ (እንዲሁም ሰፊው ክርስቲያናዊ ማኅበረ ሰብ) ኢየሱስን በተመለከተ የተማረው ነገር ሊኖር እንደሚችል ግልጽ ነው። እነዚህ ሁለት መጻሕፍት፣ ሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ደግሞ ይህንን ትምህርት ለፍሬ የማብቃት እቅድ አላቸው። ስለ ኢየሱስ የተናገረው ሁሉ «እውነተኛ መሆኑን» ማጽናት ይፈልጋሉ። አስፋሌይን [asphaleian] የሚለው ቃል በግሥም ሆነ በስም መልኩ ሲገለጽ አብዛኛውን ጊዜ የሚያመለክተው አንድን ሰው በእስር ቤት አስገብቶ መጠበቅን ነው (ማቴ 27፥64-66፤ ሐሥ 5፥23፤ 16፥24)። እርግጠኝነት ያለው እምነትን የሚያመለክት ቃል ነው። ይህ መጽሐፍ የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ነው። አሳማኝም ማራኪም ነው።

**§ 2**
**ዮሐንስ ኢየሱስን ማስተዋወቁ**
**(ዮሐ 1፥1-18)**

ሉቃስ መግቢያ አጻጻፍ እርሱ ራሱ በሚገባ የ ያውቀውን ግሪክኛ ታሪክ ሥነ ጽሑፍ ያንጸባርቃል። በሌላ በኩል የዮሐንስ መግቢያ ራሱ ባሕል የነበረውን የሆነውን የአይሁድ ጥበባዊ ሥነ ጽሑፍ[7] ያንጸባርቃል።

[6] E.T. Goodspeed. "Some Greek Notes: I. Was Theophilus Luke's Publisher?" *JBL* 73 (1954): 84 ጋር ያነጻጽሩ።

[7] Thomas Tobin, "The Prologue of John and Hellenistic Jewish Speculation," *CBQ* 52 (Apr 1990): 252-269 እንደሚገነመለከተው ዮሐንስን ከፊሎ ጋር



ለምሳሌ ያህል ተንዳኝ የሆኑ[8] የዕብራይስጥ ቅኔንና የምንባቡ መሪ ሐሳብ(ቦች) ፍንጭ የሚሆኑ የሚደጋገሙ ቁልፍ ቃላትን ይጠቀማል።[9]

ብዙ ምሑራን እንደሚያምኑት ይህ መግቢያ ቅኔ ብቻ ሳይሆን የቀረውን የመጽሐፉን ቃና እንዲያውም አስተዋዕያውንም እንኳ ሳይቀር የሚያስቀምጥ ጥንታዊ ክርስቲያናዊ መዝሙር[10] ነው። ስታሊ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፤ «የመግቢያው የመጀመሪያ አንጓ፣ የአጠቃላይ መግቢያውን ሥርዓታዊ አቀማመጥ፣ ቅላጼያዊ ቅርጽ ቃና እንደሚይዝ

ያነጻጽረዋል። ሁለቱም ተምሳሊታዊ ሥነ አፈታት እየተጠቀሙ ሊሆን ልዩነቱ ዮሐንስ አይሁዳዊ ምሑራዊ አቀራረብ (ሚድራሽ) ሲያንጸባርቅ ፊሎ ከእስክንድሪያ ሔለናውያን ባሕል የመጣ መሆኑ ብቻ ነው Kay Keng Khou, "The Tao and the Logos," *IRV* 87/344 [1998]: 77-84, ላይ ዮሐንስ ስለ ሎጎስ ያለው አመለካከት ቻይናውያን ስለ ታኦ ካላቸው አመለካከት ጋር ይስማማል ብሏል። ስለሆነም የዮሐንስ ፍልስፍና ከምዕራባውያን የፕላቶኒዝም ፍልስፍናና ከምሥራቃውያን ታኦ ፍልስፍና ጋር ይጣጣማል ማለት ነው።

[8] Mathias Rssi የዚህን ክፍል ግጥም በጥልቅ ይዳስሳል ("John 1:1-18," *Int* 31[Oct 1997]:394-401).

[9] Jeff Staley, "The Structure of John's Prologue: Its Implication for the Gospel's Narrative Structure" *CBQ* 48 (Apr 1986): 241-264 ይህን ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄያዊ የቃላት አጠቃቀም ስልት *Leitwort* ይለዋል። *Phos* እና *ginomai* እንዲህ ያሉ ቃላት እንደሆኑም ያመለክታል። ለምሳሌ ያህል *ginomai*፣ በመግቢያው chiastic structure ቢያንስ አንድ ጊዜ መታየቱንና የመግቢያውን ጭብጥ ሐሳብ በማስተሳሰር ረገድ ዋነኛ አካል እንደሆነ ያስተውላል» (ገጽ 249)።

[10] E.g. Barclay Newman. "Some Observations regarding a Poetic Restructuring of John1:1-18," *BT* 29 (Apr 1978): 206-212; Thomas Tobin. "The Prologue of John and Hellenistic Jewish Speculation." *CBQ* 52 (Apr 1990): 252 -269. ይሁን እንጂ የዮሐንስን መግቢያ ለመተንተን የሚደረግ አብዛኛው ሙከራ ለሁለት ስሕተቶች ሊጋለጥ ይችላል። የመጀመሪያው ቁጥር 6-8,13,15 ቀድሞ በነበረው ላይ በኋላ በቅኔው ላይ የተጨመሩ እንደሆኑ በማሰብ ከሌላ የተወሰደ እንደሆነ በጥብቅ የመመልከት ዝንባሌ ነው (cf. Charles Giblin. "Two Complimentary Literary Structures in John 1:1-8," *JBL* 104/1 (1985): 87-103. ሁለተኛው በዐውዱ መካከል፣ «ከዐቅም በላይ» የሆነ chiasm ተፈጥሯል ማለታቸው ነው። እርግጥ ነው ዮሐንስ የታወቀውን የአይሁዳውያንን ድግግሞሽ ስልት ተጠቅሟል፤ (ለምሳሌ ከ6-8 እና 15) ይሁን እንጂ በግልጽ ማየት የሚቻል chiasm አይደለም (አንዳንድ ምሑራን ከሚያቀርቧቸው የተለያዩ chiastic structure መመልከት እንደሚቻለው)።

ሁሉ የመግቢያው ሥርዓታዊ አቀማመጥ ቅርጽ የቀጣዩን ታሪክ አወቃቀር ቃና ይይዛል» (ገጽ 242)፡፡[11]

መግቢያው በአጻጻፉ ማራኪነት ብቻ ሳይሆን፣ በነገረ መለኮታዊ ይዘቱም ረቂቅ ነው፡፡[12] ዮሐንስ የሚያነሣቸው አንዳንድ ጽንሰ ሐሳቦች በጣም ጥልቅ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሌላው ቀርቶ እንዲሁ ላይ ላዩን የሚያነብ አንባቢ እንኳ ዋናውን ነጥብ ማለትም፤ ይኸውም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት አይስተውም፡፡

Yoh 1፥1-2

> 1በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ 2እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፡፡

«በመጀመሪያ» የሚለው ቢያንስ ሦስት መጻሕፍትን ያያይዛል፤ ዘፍጥረትን፣ ዮሐንስንና 1ዮሐንስን፡፡ ሦስቱም የሚጀምሩት በዚህ ሃሳብ ነው፡፡ ዘፍጥረትና ዮሐንስ ስለ ሥነ-አፈጣጠር በተለየ ሁኔታ ይናገራሉ፡፡ ዮሐንስና 1 ዮሐንስ ደግሞ በተለየ ሁኔታ ስለ ተሠግዎ ይናገራሉ (ዮሐ 1፥14፤ 1ዮሐ 1፥1-2)፡፡ ስለሆነም በአካል የተገለጠው ሕይወት ሰጪ ቃል ኢየሱስ ከሥነ ፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ ሙሉ ሕላዌ ነበረው፤ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ነበረ፡፡

[11] Jeff Staley, "The Structure of John's Prologue: Its Implication for the Gospel's Narrative Structure," *CBQ* 48 (Apr 1986): 241-264. መጽሐፉን የፊተኛው ከኋለኛው እንደ ሚበልጥ አድርጎ አምስት ክፍሎች ከፍሎታል (1፥1-8፤ 1፥19-3፥36፤ 4፥1-6፥71፤ 7፥1-10፥42፤ 11፥1-21፥25) በተጨማሪም ገጽ 264 ላይ ባለው ሠንጠረዥ መግቢያው ውስጥ ያለ ሐሳብ በቀጣዩቹ አምስት ክፍሎች በእያንዳዳቸው ውስጥ በድጋሚ መቅረቡን ያመለክታል፡፡

[12] ለምሳሌም ዮሐ 1፥1-18 በኢየሱስ አማካይነት እንደተከወኑ አድርጐ ሁለቱን የብሉይ ኪዳን ማዕከላዊ ማለትም ሥነ-ፍጥረትንና የዘፀአትን ታሪክ በድጋሚ ይከውናቸዋል፡፡ Cf. George Knight "The Light of God in Action," *Chr. Cent.* 115/35 [1998]: 1212-1214.



በእነዚህ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቁጥሮች ዮሐንስ ኢየሱስን አስመልክቶ አራት አስገራሚ ነገሮችን አጽንቶ ይናገራል - እርሱ ሕይወት ሰጪ ቃል (ሎጎስ) ነው፤ እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ የሕይወት ፈጣሪ ነው፤ እርሱ ብርሃን ነው፡፡

## ኢየሱስ ሕይወት - ሰጪ ቃል (ሎጎስ) ነው

ኢየሱስ «ቃል» ነው የሚለውን ስናነብ በተለምዶ የምናስበው ስለ እግዚአብሔር ቃል ማለት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ መንፈሳዊ ይዘት እንዲኖረው በማድረግ ኢየሱስ በሥጋ ወይም በአካል የተገለጠ የእግዚአብሔር መልእክት ማለት እንደ ሆነ እናስባለን፡፡ ይህ ግን ስሕተት ባይሆንም የተሟላ ግን አይደለም፡፡ ሕይወት ሰጪ ቃል ወይም «ሎጎስ» የሚለው ቃል ግን በግሪክ ፈላስፎችም ሆነ በዕብራውያን ነገረ መለኮት ምሑራን ዘንድ የበለጸገ ትርጉም ነበረው፡፡

ለምሳሌ ያህል ሶቅራጥስና አፍላጦን (ፕሌቶ) ቃል «በመለኮታዊ አስተሳሰብ» ውስጥ ያለ ሐሳብን ያመለክታል፡፡ በሌላ አነጋገር ሕይወት ሰጪ ቃል ወይም «ሎጎስ» በሰዋሰዋዊ ቅንብር የተዘጋጀ የሰዎች ንግግር ብቻ ሳይሆን ከላይ ወደ ሰዎች የወረደ የራሳቸው የአማልክት የተባራ ሐሳብ ጭምር ነበር፡፡ ዜኔ በሚባል ሰው (300 ዓ.ቅ.ክ) መሪነት ስቶይኮች ደግሞ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ወሰዱት፡፡ እንደ እነርሱ አስተሳሰብ ሕይወት ሰጪ ቃል ወይም «ሎጎስ» መለኮታዊ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ትእዛዝም ነው፡፡ ይህም አማልክት የሚያስቡትም ሆነ የሚናገሩት በስፍራና በጊዜ ውስጥ በቁሳዊ አካል ቅርጽ ይገለጣል ማለት ነው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እንደምናነበው «*እግዚአብሔር አለ ... እንዳለውም ሆነ*» እንደሚለው ያለ ነው፡፡ ስለሆነም የአማልክቱ ቃል የመፍጠር ኃይል አለው ማለት ነው (ሎጎስ ስፐርማቲኮስ - *logos spermatikos* የሚባለው ይኸው ነው)፡፡ ምስጢራዊ የሃይማኖት

ክፍሎችም (Mystery cults) አንድ ተጨማሪ እርምጃ ወደ ፊት ሄደዋል፡፡ ሕይወት ሰጪ ቃል ወይም «ሎጎስ» በሚለው ላይ ከአማልክት ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚለውን ሃሳብ አከሉበት፡፡ አምላክ ከሰው ጋር ከተነጋገረ መለኮታዊ መገለጥ ይሆናል፡፡ ሰው ከአምላክ ጋር ከተናገረ ግን ጸሎት ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱም ምስጢራዊና ቅዱስ ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ ለአማልክትና ለሰዎች ቃል የሚያቀብለው መልእክተኛ ሔርሜስ የሚባለው አምላክ እንደ ሆነ ይታሰብ ነበር፡፡ የግሪኮችን ፍልስፍና በሚመለከት እዚህ ላይ ይብቃን፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ፊሎ ይመጣል፡፡ የግሪኮችን ፍልስፍና የሚወድ አይሁዳዊ የነገረ-መለኮት ምሑር ነበር፡፡ ስለሆነም «ሎጎስ» ለሚለው ግሪኮች የሰጡትን ትርጉም ወይም ገለጻ ወስዶ ለብሉይ ኪዳን አዋለው፡፡ ስለ ሕይወት-ሰጪ ቃል (ሎጎስ) ሲናገር ምጡቅ በሆነው በእግዚአብሔርና በቁሳዊው ዓለም መካከል እንዳለ ድልድይ ነበር የሚያቀርበው፡፡ በምድርና በሰማይ መካከል እንደሚመላለስ ከፊል አምላክ ዓይነት ኃይል ያለው ነበር፡፡ ስለሆነም በአይሁድ ነገረ መለኮት እሳቤ ቃል፣ «አንዳች ውጤት የሚያስገኝ ንቁ ኃይል» የሚል ትርጉም አግኝቶአል፡፡ (1) ፍጥረት፣ ዘፍጥረት 1፡3፣ (2) ፈውስ፣ መዝሙር 107፡20፤ 147፡15:8፤ ወይም (3) መገለጥ፡፡

ለግሪኮች የሞፈጥር ቃል (ሎጎስ) ከሰዎች ፍልስፍና ውስጥ ጠልሎ የወጣ የአማልክት ሐሳብ ነበር፡፡ ለአይሁዶች በሰዎች ሕይወት ጉልህ እውነታ ሆኖ ከእግዚአብሔር አንደበት የወጣ ቃልን ይወክላል፡፡ ዮሐንስ ሁለቱንም አስተሳሰቦች ከራሱ ጋር አዛምዷቸዋል፡፡ ለእርሱ «ሎጎስ» በሥጋ የተገለጠ የእግዚአብሔር ጥበብና የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጸበት ባለሟል ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ለዮሐንስ ልዩነቱ ይህ «ሎጎስ» ወደ ምድር ሲወርድ ምንም የጠፋ ወይም የባከነ ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ይህ «ሎጎስ» የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚክል



ብቻ ሳይሆን በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለሆነም የእግዚአብሔር ሐሳብ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የበላይነቱን ይዟል፡፡

## ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው

ስለ ሎጎስ የቀረበው ይህ ሐሳብ በመጠኑም ቢሆን ኢየሱስን በተሻለ ሁኔታ እንድንረዳው ያስችለናል፡፡ ኢየሱስ በሥጋ ከመገለጡ በፊት በ«ሎጎስ» (በሚፈጥር ቃል) መልኩ እግዚአብሔር ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ጥንተ-ሕላዌ የነበረው መሆኑን ዮሐንስና ጳውሎስ ብቻ ሳይሆኑ፣ ኢየሱስ ራሱ በወዳጆቹና በጠላቶቹ ፊት ይ፤ንኑ ተናግሮአል (ዮሐ 6፥38፤ 8፥42፤ 16፥27፤ 17፥5)፡፡ በሥነ ፍጥረት መጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር (ዮሐ 1፥1-3፣18፤ 1ቆሮ 8፥6፤ ቈላ 1፥16፤ 1ዮሐ 1፥1)፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ባገለገለበትም ወቅት በዚያ ነበር (1ቆሮ 10፥3-4)፡፡ ምንም እንኳ በክብር፣ በኀይልና ባለጠግነት ከአብ ጋር እኩል ቢሆንም (ዮሐ 17፥5፤ 2ቆሮ 8፥9፤ ፊልጵ 2፥6)፣ ለእግዚአብሔር ለመገዛት እራሱን አሳልፎ ሰጥቷል፣ ከዚህም የተነሣ ከሰማይ የእግዚአብሔር ወኪል ሆኖ ተላከ (ዮሐ 6፥38፣51፤ 8፥42፤ 13፥3፤ 16፥27፣30፤ ሮሜ 8፥3፤ ገላ 4፥4፤ 1ዮሐ 4፥9-10)፡፡ በዚህ የመታዘዝ እርምጃው የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ሲል ራሱን ባዶ አደረገ ሥጋንም ለበሰ፡፡ የሰውን መልክ በመውሰድ (ሮሜ 8፥3፤ ፊልጵ 2፥7-8) እንዲሁም ራሱ ኀጢአት ሆኖ በመሞት (2ቆሮ 5፥21) ራሱን ዝቅ አደረገ፡፡

እዚህ ላይ እንግዲህ ሕይወት-ሰጪ ቃል (ሎጎስ) ከይሆዋ ጋር እኩል ከሆነ አንዳንዶች «አምላክ» ወይም» «አምላክ መሰል» ነው የሚሉት ለምንድነው? በግሪክ ቋንቋ፣ «ቃልም ሥጋ ሆነ» በሚለው በቍ 1 ያለው ሐረግ ውስጥ የግል የተሳቢ አመልካች ፊደል አይገኝም፡፡ ስለዚህም አንዳንድ የሃይማኖት ቡድኖች በግሪኩ ቋንቋ የሌለውን የወል ... አመልካች ፊደል መጨመር ከጅለዋል፡፡ እንዲህ ማድረጉ

ሁልጊዜም ባይሆን አንዳንዴ ትክክለኛ አተረጓጐም ነው። በግሪኩ የተሳቢ አመልካች ቃል አንድን የተለየ ነገር (ሰውን፣ ስፍራን ወይም ዕቃን) ይገልጻል። አንድ ሰው በጣቱ በመጠቆም «ይሄኛው» በማለት የማመልከት ያህል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በግሪክ ቋንቋ የተሳቢ አመልካች የሌለው ስም ለየት ተደርጎ የተጠቀሰውን የተጠቃሹን ማንነት ወይም ባሕርይ ያመለክታል። ስለሆነም፣ «ቃልም ሥጋ ሆነ» የሚለው ሐረግ የተጠቀሰው ቃል፣ «የእግዚአብሔር ባሕርይ/ ማንነት» ያለው መሆኑን ያመለክታል። ኢየሱስ፣ «አምላክ» ወይም «አምላክ መሰል» ነው ከማለት ይልቅ ይህ ቁጥር ስለ ኢየሱስ መለኮት ነው የሚለውን አቋም በትክክል የሚያጸና ነው።[13] (ማሳሰቢያ፣ ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ለየት የሚያደርግ የተሳቢ አመልካች መጨመር በፍጹም አግባብ በማይሆንበት በቁ 12 እና 18 ላይም ይገኛል። በተለይም፣ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» የሚለውን በዮሐንስ 4፥24 ይመ)።[14]

እንደ እውነቱ ከሆነም፣ ሰው የሆነው ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነው የሚለውን እንዳለ መቀበል እንደሚከብድ ግልጽ ነው። እንዲህ በማለት የተናገረው ዮሐንስ ብቻ ቢሆን ኖሮ እንደ ወፈፍተኛ ወይም ባለ ቅኔ ብቻ ቆጥረን ነገሩን ችላ እንለው ይሆናል።

[13] E.L. Miller, "The Logos was God" *EvQ* 53/2 (1981): 65-77, ይህን ሐረግ በተመለከተ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ በርካታ መደምደሚያዎች ላይ ደርሰዋል:- (1) theos ለሚለው ቃል "Divine" በጣም ደካማ ትርጉም በመሆኑ ተቀባይነት ማግኘት እንደሌለበት፣ (2) ጠቅለል ባለ መልኩና እዚያው የምናያቸው የሐረጉ ዓውዶች "*theos*" ለሚለው ቃል የሚስጡት ትርጉም የሚያመለክተው ለየት ያለ የአመልካች ተሳቢ እንዳለው ነው እንጂ የማንነት ወይም ቅጽላዊ መግለጫ እንዳልሆነ ነው። (3) በወንጌሉ 1፡1 ላይ እንደ ቀረበው ሁሉ በዚህም ሐረግ የተሳቢ አመልካች አለመኖሩ የሚያመለክተው ዮሐንስ በ«ሎጎስ» እና በ"theos" ፍጹም የሆነ እኩያዊ ንጽጽር ማድረግን እንዳልፈለገ ነው። (4) ሆኖም ከወንጌሉ 1፡2 ጋር ሲጣመር የክርስትናን (ሥሉስ) አምላክ ጽንሰ ሃሳብ ያመለክታል።

[14] በግሪክ ቋንቋ አመልካች ተሳቢ የሌላቸው ስሞችን በተመለከተ የተሟላ ዝርዝር ለማግኘት የC.H. Dodd, "New Testament Translation Problem, *BT* 28/1 (Jan 1977): 101-104 እና P.B Harner, "Qualitative Anarthrous Predicate Nouns: Mark 15:39 and John 1:1," *JBL* 92 (1973): 75ff ይመ።

ያሁን እንጂ ኢየሱስን ከይሆዋ ጋር በእኩልነት ደረጃ ያነጻጽሩት፤ ጴጥሮስና ጳውሎስም ይህንኑ አቋሙን ተጋርተውታል (ሮሜ 9፥5፤ 2ተሰ 1፥12፤ ቲቶ 2፥13፤ 2ጴጥ 1፥1፤ 1ዮሐ 5፥20) ከዚህም ባሻገር ወዳጆቹም ሆኑ (ዮሐ 1፥18፤ ማቴ 14፥33፤ 16፥16-19፤ ሉቃ 7፥13-16፤ 23፥39-43) ጠላቶቹ (ማር 3፥11፤ ማቴ 27፥54፤ ማር 15፥39፤ ሉቃ 4፥41፤ ዮሐ 3፥1-2) ስለ ኢየሱስ መለኮታዊነት መስክረዋል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ኢየሱስ ራሱ ይህንኑ ተናግሮአል። እንደ እግዚአብሔር ስግደት ተቀብሏል። (ማቴ 16፥16-17፤ 26፥6-13፤ ሉቃ 5፥8-9፤ 7፥36-50፤ 19፥35-40፤ ዮሐ 20፥27-29)። እግዚአብሔር ብቻ የሚያደርጋቸውን ተግባራት አከናውኗል (ማቴ 28፥18፤ ማር 2፥10፤ ዮሐ 5፥24-30፤ 14፥6፤ ሮሜ 3፥21-26፤ 5፥5-17፤ 1ቆሮ 15፥16-19፣35-38፤ ፊልጵ 3፥21፤ ቈላ 1፥16-17፤ 2፥3፤ ዕብ 1፥3)። በተጨማሪም በተለየ ሁኔታ አምላክነቱን በተመለከተ ተናግሮአል (ማቴ 10፥32-33፤ 16፥13-18፤ 28፥18፤ ማር 2፥10፤ 9፥41፤ 14፥62፤ ዮሐ 5፥30-40፤ 8፥23-24፣58፤ 9፥37፤ 10፥30፣36፤ 14፥9፤ 17፥1-3)። ይህ ሁሉ ኢየሱስ «እኔ ... ነኝ» በማለት በዮሐንስ ወንጌል የተናገራቸውን እንኳ በሙሉ ሳይጨምር ነው (6፥35፣41፣48፣51፤ 8፥12፣58፤ 9፥5፤ 10፥7፣9፣ 11፣14፣36፤ 11፥25፤ 14፥6፤ 15፥1፣5፤ ራእ 1፥8፣17፤ 22፥16)። ይህንን ሃሳብ ስናጠቃልለው አራቱም ወንጌላውያን፣ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስና ኢየሱስም ራሱ በዮሐንስ 1፡1 ላይ የተገለጸውን ኢየሱስ «ሕይወት ሰጪ ቃል» (ሎጎስ) በሥጋ የተገለጠ አምላክ መሆኑን ማረጋገጣቸው ነው።

3ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተፈጠረው ሁሉ
ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም። 4ሕይወት በእርሱ
ነበረች፤ ይህች ሕይወት የሰው ብርሃን ነበረች። 5ብርሃንም
በጨለማ ያበራል፤ ጨለማውም አላሸነፈውም።[u]

ዮሐ 1፥3-5

[u]5 ወይም ጨለማው ግን አላወቀውም

## ኢየሱስ የሕይወት ፈጣሪ ነው

ከዚህ ቁጥር (ዮሐ 1፥3) በተጨማሪ ኢየሱስ ዓለምን እንደ ፈጠረ በግልጽ የሚናገሩ ሌሎች ሁለት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች አሉ - 1ቆሮንቶስ 8፥6 እና ቈላስይስ 1፥16። ከእነዚህ ሦስት ምንባቦች፣ (1) ኢየሱስ ከአብ ሥልጣን በታች እንደ ነበረና (2) ፍጥረትን በማስገኘት ረገድ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትጋት የፈጸመ ባለሟል እንደ ነበረ እንማራለን። ኢየሱስ «ሎጎስ» (ሕይወት-ፈጣሪ-ቃል) ነው የሚለውን ሃሳብ በቀላሉ ዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ በማስገባት ማንበብ ይቻላል። በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር በቃሉ ኃይል መፍጠሩን እናስተውሳለን - «እግዚአብሔር አለ ... እንዳለውም ሆነ»። ሁለተኛ ዘፍጥረት 1፥26 ላይ «ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል እናስታውሳለን። በፍጥረት ጊዜ እግዚአብሔር ብዟዊ ስብዕና ነበረው። ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሑራን በዚህ ጥቅስ የሥላሴ ሐሳብ መኖሩን ተገንዝበዋል። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ፈቃድ በንቃት ያስፈጸመ ባለሟል እንደ ነበር ዮሐንስ ግልጽ በሆነ መንገድ አጽንቶታል።

ሕይወት ሰጪ ወይም ሎጎስ የሆነው ኢየሱስ (ቃል) በፍጥረት ሥራ ኃላፊነት ስለ ነበረው ዮሐንስ፣ «ሕይወት በእርሱ ነበረች» ለማለት ችሏል። በመሠረቱ፣ በግሪክ ቋንቋ ሕይወት ለሚለው ሦስት ቃላት አሉ፤ ባዮስ (*Bios*)፣ ሳይኪ (*psyche*) እና ዞይ (*zoe*) ባዮስ (ባዮሎጂ የተሰኘው ቃል መሠረት)፣ እዚህና አሁን ስላለው ዓይነት ሕይወት ማለትም የሕይወት ዕድሜን ያመለክታል። ሳይኪ (ቃል በቃል ነፍስ) የሚያመለክተው (1) ግለ ሰባዊ ሕይወትን፣ የግለ ሰብን ሰብዕናና (2) የሰውን እስትንፋስ ነው። እዚህ ላይ ዮሐንስ የሚጠቀምበት ዞይ የሚለው ሦስተኛው ቃል (ከባዮስ ማለትም ውጫዊ ከሆነው ሕይወት በተቃራኒ) የሚያመለክተው ውስጣዊውን ሕይወት ነው። «ሕያውነት» ብለን የምንጠራው ሕይወት ነው።

እንዲያውም ዮሐንስ ስለ «ዘላለማዊ ሕይወት» በሚናገርበት ስፍራ ሁሉ የተጠቀመው ይህንን በዚህ ዞይ (*zoe*) የሚለውን ቃል ነበር። (ዮሐ 3፥15-16፣36፤ 4፥14፣36፤ 5፥24፣39፤ 6፥27፣40፣47፣54፣68፤ 10፥28፤ 12፥25፣50፤ 17፥2-3፤ 1ዮሐ 1፥2፤ 2፥25፤ 3፥15፤ 5፥11፣13፣20)። ስለዚህ ኢየሱስ የሚሰጠን በስፍር የሚለካ ሕይወት ሳይሆን ጥራት ያለውን ሕይወት ነው። አንድ ሰው ወደ «ዘላለማዊ ሕይወት» የሚገባው ሲሞት አይደለም። አንድ ሰው ዘላለማዊ ሕይወት የሚያገኘው ሕያው ከሆነው ክርስቶስ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ነው (ዮሐ 5፥40፤ 1ዮሐ 5፥11-12)። በቃሉ አማካይነት ከኢየሱስ ጋር ስንገናኝና (ዮሐ 5፥24፣39፤ 6፥63፣68) እምነታችንን በእርሱ ላይ ስናደርግ (3፥15-16፣36፤ 6፥40፣47፤ 20፥31፤ 1ዮሐ 5፥13) እርሱ ስጦታ አድርጎ የሚሰጠንን ሕይወት እንቀበላለን (ዮሐ 10፥28፤ 17፥2-3)።

ኢየሱስ ራሱ ሕይወት ነው (1ዮሐ 1፥1-2)! ከእርሱ ጋር ግንኙነት ስናደርግ እኛም ሙሉ በሙሉ ሕያዋን እንሆናለን (ሮሜ 8፥10-11 ጋር ያነ)። በእርግጥ የዚህ ዘላለም ሕይወት የወደፊት ገጽታም አለው - ማለትም ለዘላለም የሚዘልቅ ነው። የበለጠ ፋይዳ የሚሰጠው ግን በአሁኑ ጊዜ መጀመሩ ነው (ዮሐ 10፥10፤ 1ዮሐ 3፥14-15፤ 5፥11-13)። የዚህ ሁሉ መቋጫው - ኢየሱስ ከኃጢአቴ ያድነኛል የሚለው ነው። ያም የዘላለም ሕይወት ነው (ዮሐ 6፥51)። በግሌ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም የሚዘልቅ ኅብረት አድርጌአለሁ።

## ኢየሱስ ብርሃን ነው

ኢየሱስ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ብርሃንም ነው። በዮሐንስ ይህ ጠንከር ያለ መሪ ሐሳብ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ 72 ጊዜ

ከተጠቀሰው «ብርሃን» (*phos*) የሚለው ቃል 33ቱ የሚገኘው በዮሐንስ ጽሑፍ ነው:: በማቴዎስ 4፥16 እና በሉቃስ 2፥32 ላይ ካሉት ትንቢታዊ ንግግሮች ሌላ «ብርሃን» የሚለውን ቃል ኢየሱስን ለመግለጽ የተጠቀመበት የወንጌል ጸሐፊ ዮሐንስ ብቻ ነው:: ሌሎች ጸሐፊዎች የተጠቀሙበት ከዓለም ጋር ካላቸው ዝምድና አንጻር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰዎች ለመግለጽ ነው:: ዮሐንስ ግን በኢየሱስ ሰውኛ መግለጫ ያገኙትን ሁለቱን የብርሃንና የሕይወትን መሪ ሐሳቦች አጣምሮ ያቀርባቸዋል (1፥9-14፤ 8፥12፤ 9፥5፤ 12፥35-36፣46):: በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለውን ውጊያ በተመለከተ ስዕላዊ ገለጻ በማቅረብ ረገድም ዮሐንስ ከሌሎች በጣም ይለያል (ዮሐ 1፥5፤ 3፥19-20፤ 1ዮሐ 2፥8፤ ከ2ቆሮ 6፥14 ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ ከሥነ ምግባር አንጻር ብርሃንና ጨለማን እያነጻጸሩ ማቅረብ በመሠረቱ በክርስቲያን ነገረ መለኮት የተጀመረ ሳይሆን ቀደም ሲል በግሪክ ፍልስፍና አገልግሎት ላይ ውሉአል:: አማልክት ብርሃን ባለበት ድባብ ውስጥ እንደሚኖሩ የሚገልጽ የሃሳብ ሥዕል ነበር:: እንደ ኖስቲኮችና ኢሰናውያን ሁሉ ብሉይ ኪዳንም ይህንኑ ተመሳስሎት ተጠቅመዋል:: ያም ሆኖ ግን እዚህ ላይ እግዚአብሔር ብርሃን ተብሎ መጠራቱ (1ዮሐ 1፥5) ዮሐንስ ኢየሱስን በድጋሚ እግዚአብሔር አድርጎ እንደገለጸው ያመለክታል::

በዮሐንስ ጽሑፎች መሠረት የብርሃን ዋናው አገልግሎት በዙሪያችን የከበበንን እውነታ መግለጥ ነው:: ስለዚህም አካባቢያቸውን (ከሥነ ምግባር አንጻር) ማየት ስለሚችሉና (ከሥነ ምግባር አንጻር) ተገቢ ምላሽ ስለሚሰጡ በብርሃን የሚመላለሱ መልካም ሰዎች ናቸው (ዮሐ 3፥19-21፤ 1ዮሐ 1፥7፤ 2፥9 ከሮሜ 13፥12 ጋር ያነ):: በሌላ በኩል ደግሞ በጨለማ የሚመላለሱ ሁሉ ለመሰናክል የተጋለጡ ናቸው (ዮሐ 11፥10፤ 12፥35፤ 1ዮሐ 2፥11):: በብርሃን ውስጥ በግልጽ መኖርን ወይም የጨለማን መሠወሪያነት የመምረጥ ነጻነትም አለ:: ከነገረ ፍጻሜ



አኳያ የክፉዎች ዕጣ ፈንታ በጨለማ ሲመስል የጻድቃን ዕጣ ፈንታ ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም በሚቀርብበት በእግዚአብሔር በራሱ ልዩ ብርሃን ተመስሏል (ራእ 21፥23፤ 22፥5)::

ስለ «ብርሃን» የምንነጋገረው ይሄ ንግግር አንድ ትልቅ ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል፤ ዮሐንስ «ጨለማው ግን ገና አላወቀውም» ሲል ምን ማለቱ ነው? ካታላምባኖ (*Katalambano*) የሚለው ይህ ግሪክኛ ቃል፣ «ታች» እና «መውሰድ/መቀበል» የተሰኙትን ቃላት በማቀናጀት የሚገኝ ጥምር ቃል ነው:: ስለሆነም ሥርወ ቃሉ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ፣ «መያዝ መቆጣጠር» የሚለውን ያመለክታል:: ይህ ቃል በሁለት አቅጣጫዎች ሊሄድ ይችላል:: በመጀመሪያ፣ በአእምሮ መያዝን ወይም በቁጥጥር ሥር መሆንን ያሳያል (ለምሳሌ መረዳትን፣ ግንዛቤንና ማስተዋልን ከሐሥ 25፥25፤ ኤፌ 3፥18 ጋር ያነ) ሊያመለክት ይችላል:: «ያዝኩት» ወይም «ተረዳሁት» በሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር እንጠቀምበታለን:: ሁለተኛ፣ ዋናው ትርጉሙ አንድ ነገርን ጉልበትን በመጠቀም መያዝ (ለምሳሌ ማሸነፍ፣ ተጭኖ መያዝ፣ ማጥፋት ከዮሐ 8፥3፤ 12፥35፤ 1ቆሮ 9፥24፤ 1ተሰ 5፥4) ነው:: የግሪኩ ቃል በአንድ ጊዜ ሁለቱንም ሃሳቦች ሲይዝ እንደሚችል መረዳቱ አስፈላጊ ነው:: ይሁን እንጂ ተመጣጣኝ የአማርኛ ቃል ስለሌለ «ይሄ ወይም ያኛው» ትርጉም ለማለት እንገደዳለን::

ስለሆነም ይህ ቁጥር ሁለት ዓቢይ ትርጉሞችን ይዞአል:: በመጀመሪያ፣ ጨለማ ብርሃኑን አላሸነፈውም:: ይህም ማለት ወደ አንድ ክፍል ስትገቡና ብርሃን ስታበሩ ጨለማው ብርሃኑን አያዳፍነውም:: ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ወደ ጨለማው ዓለም ሲመጣ አሸነፈ እንጂ አልተሸነፈም:: ምናልባት ብርሃኑ መስቀል ላይ መቸንከሩን ግምት ውስጥ በማስገባት ስናስብ ይህ አባባል እንግዳ ሊሆን ይችላል፤ ያም ቢሆን ግን የመቸንከሩ ታሪክ የሚያልቀው በትንሣኤ ነው:: ሁለተኛው

አጽንዖት የሚገልጠው ጨለማ የብርሃንን እውነታ መረዳት ወይም ማስተዋል አለመቻሉ ነው። በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ከማንም የበለጠ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ የተረዱት ነበር።[15]

ዮሐ 1፥6-9

[6]ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ። [7]ሰዎች ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ፣ ስለ ብርሃን ምስክር ሆኖ ለመቆም መጣ፤ [8]ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ ራሱ ብርሃን አልነበረም። [9]ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጪ የሆነው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም እየመጣ ነበር።[ii]

*[ii]ወይም ደሀ ወደ ዓለም ለሚመጣ ለማንኛውም ሰው ብርሃን የሚሰጥ እውነተኛው ብርሃን ነበረ።*

መጥምቁ ዮሐንስ አስገራሚ ታሪክ አለው። ከኢየሱስ በፊት እንደሚመጣ ትንቢት ተነግሮለታል (ኢሳ 40፥3-4፤ ሚል 3፥1፤ 4፥5)። የሰዎችን ልብ በስብከቱ በማዘጋጀት ለኢየሱስ መንገድ መጥረግ የእርሱ ሥራ ነበር። ወደዚህ ዓለም የመጣው የካህናትን የዘር ሐረግ ተከትሎ ነበር። አባቱ ዘካርያስ ከአብያ የካህናት ዘር ሐረግ ሲሆን (1ዜና 24፥10) እናቱ ደግሞ ከአሮን ዘር ሐረግ የተገኘች ነበረች (ሉቃ 1፥5)። የወላጆቹ መካንነትና በተአምር የመፀነሱ ጉዳይ በሉቃስ 1 እና በማቴዎስ 1 ላይ ተገልጾአል። ኢየሱስና ዮሐንስ በአንድ መልኩ ዘመዳሞች ነበሩ (ምናልባትም የእህትት ወይም የአጐት ልጆች ሳይሆኑ አይቀሩም) ዮሐንስ በስድስት ወር አንጋፋው ነበር (ሉቃ 1፥36)። በስምንተኛ ቀኑ ተገርዞ በናዝናዊነት ተለየ (ሉቃ 1፥15)። ስለ ዮሐንስ የልጅነት ሕይወት የምናውቃቸውን ሌሎቹን መረጃዎች ሁሉ የምናገኘው ከሉቃስ 1፥80 ነው።

[15] ጨለማ ብርሃንን እንዴት ሊረዳው እንዳልቻለ የፕሌቶ ዋሻ ጥሩ ማስረጃ ነው (*Republic*, VII).



ዮሐንስ የነቢይነት አገልግሎቱን የጀመረው እ.ኤ.አ. በ25 ዓ.ም- በጢባርዮስ ቄሣር 15ኛ ዓመት ነበር (ሉቃ 3፥1)። ከዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ሲሰብክና ሲያጠምቅ በነበረበት ወቅት (ዮሐ 1፥28) ብዙዎችን ወደ ራሱ መሳብ ችሎ ነበር (ማቴ 3፥5)። ጠቅለል ተደርጎ ሲገለጽ፣ እግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች» የሚል ነበር፤ አገልግሎቱ ደግሞ የኀጢአትን ይቅርታ ያገኙ ዘንድ በውሃ ውስጥ በመጥለቅ እንዲጠመቁ ማድረግ ነበር (ማር 1፥14)። ስብከቱ በጣም ኃይለኛ ስለ ነበር አንዳንዶች ከሞት በኋላ በድጋሚ በአካል የተገለጠ ኤልያስ፣ ኤርምያስ ወይም ሌላ ነቢይ እንደሆነ አድርገው ይቈጥሩት ነበር (ማቴ 16፥14)። ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ የበለጠ ታላቅ ሰው እንደ ነበር ኢየሱስ ተናግሮለታል (ማቴ 11፥11)። ይሁን እንጂ በጣም የሚገርመው ነገር ዮሐንስ አንድም ተአምር አለማድረጉ ነበር (ዮሐ 10፥41)። ምናልባትም ካከናወናቸው ተግባራት ሁሉ የሚበልጠው ኢየሱስን ማጥመቁ ነው። ይህን ካደረገ በኋላ አገልግሎቱ ወደ ፍጻሜ ተቃረበ። ምንም እንኳ ማጥመቁን ቢቀጥልም፣ ማድረግ የነበረበትን ሁሉ እንዳከናወነ ራሱ ተናግሮአል (ዮሐንስ 3፥30)።

ሄሮድስ ያዘጋጀው ፈንጠዝያ ግብዣና የክፉዋ ሚስቱ የሄሮድያዳ የብቀላ እርምጃ ለመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነቢይ ሞት ምክንያት ሆነ። የዮሐንስ አንገት የተቀላው በሙት ባሕር አካባቢ በነበረው ምሽግ ነበር። በተንኮል ቢገደልም እንኳ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቆአል። እውነተኛ ብርሃን ለሆነው ለኢየሱስ መንገድን ሲያዘጋጅና ወደ እርሱም ሲያመለክት ኖሮአል።

ኢየሱስ ለሰዎች ሁሉ ብርሃን መስጠቱ እውነት የሚሆነው እንዴት ነው (ቁ 9)? ኢየሱስ ዓለም አቀፍ አዳኝ ስለ መሆኑ የሚያመለክቱ የሚመስሉ በርካታ ጥቅሶች አሉ (ዮሐ 1፥9፣29፤ 4፥42፤ 12፥32፤ ሮሜ 5፥18፤ 11፥32፤ 1ጢሞ 2፥6፤ 4፥10፤ 1ዮሐ 2፥2)።

ሰዎች ሁሉ ክርስቲያኖች አለመሆናቸው ግልጽ ነው። ስለዚህም እነዚህ ምንባቦች ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ አድኖ ሁሉንም ነገር ብሩህና ፍልቅልቅ አድርጎአል ማለታቸው ሊሆን አይችልም። እንዲያውም ጨለማው ብርሃንን ሊቀበለው እንዳልፈለገ ነበር ዮሐንስ የተናገረው (ቁ 5)። በእነዚህ ምንባቦች ተቀባይነት ያለው መግለጫ የሚሰጡ ቢያንስ ሦስት ገለጻዎች አሉ። በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ በእርግጥ በታሪክ ውስጥ ከማንኛውም ሰው ይልቅ ሰዎች ላይ በጎ ተፅዕኖ አሳድሯል። እርሱ ለ33 ውሱን ዓመታት ያህል በዚህ ምድር በመኖሩ ዓለም የተሻለች፣ ይበልጥ ጥበብና ርኅራኄ ያለባት ስፍራ ሆናለች። ሁለተኛ፣ እርሱ ያሳደረው በጎ ተፅዕኖ በመሠረታት ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ዛሬም እንደ ቀጠለ ነው። የኢየሱስ ተከታዮች ባይኖሩ ኖሮ ዓለም በሳይንስ፣ በትምህርት፣ በፖለቲካና በሕክምና ረገድ አሁን ካለበት ይልቅ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ወደ ኋላ በቀረ ነበር። ሦስተኛ፣ ብርሃን የሚገኝበትን መንገድ በማዘጋጀቱ እያንዳንዱ ሰው አብርሆት እንዲያገኝ ዕድል አስገኝቷል።

ዮሐ 1፥10-13

[10]እርሱ በዓለም ውስጥ ነበረ፤ ዓለም የተፈጠረው በእርሱ ቢሆንም እንኳ፣ ዓለም አላወቀውም። [11]ወደ ራሱ ወገኖች መጣ፤ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፤ [12]ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው። [13]እነዚህም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፣ ከደም[*] ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።

*[*]ሌላ ትርጉም «ከተፈጥሮ ውልደት» ይለዋል*

እዚህ ላይ በረከት ያሉ የመግቢያ ገለጻዎችን መስጠት ተገቢ ይሆናል፤ (1) በኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ታላቅ መብት ተሰጥቶናል። ኤግዞስያ (*exousia*) የሚለው ቃል በቃል፣ «ኃይል» ወይም «ሥልጣን» ማለት ነው። (2) በሥጋ ልጆች ባለመሆናችን የማደጎ ልጆች ሆነን ወደ ቤተ ሰቡ መግባት ከበረከ[illegible] ቁ 14 ...

(3) ለኢየሱስ ምላሽ ስንሰጥ፣ በእምነት ስሙን ስንቀበል (ገላ 3፥26 ጋር ያነ) እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ስንመራ (ሮሜ 8፥14) በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ውል ተፈጽሟል። (4) ሰላምን ለሚያወርዱ (ለሚያስተራርቁ) ኢየሱስ ራሱ ይህን ተስፋ ሰጥቷል (ማቴ 5፥9)።

በዘፍጥረት 6፥2፣4 ከተጠቀሱትና ምንነታቸው በውል ካልታወቀ ሁለት ጥቅሶች ባሻገር በእነዚህ ቊጥሮች የተጠቀሰው ይህ ሃሳብ የአዲስ ኪዳን ጽንሰ ሐሳብ ነው። አጠር ያለ የአዲስ ኪዳን ዳሰሳ ብናደርግ የእግዚአብሔር ልጆችን እንዴት መለየት እንደምንችልና እነርሱም ሊጠብቁ የሚችሏቸው ጥቅሞች ምን እንደ ሆኑ ግልጽ ይሆንልናል። በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ልጆች በተግባራቸው ይታወቃሉ፤ (1) ኃጢአት ማድረግን ይተዋሉ (1ዮሐ 3፥9-10፤ 5፥18)። (2) እርስ በርስ ይዋደዳሉ (1ዮሐ 4፥7)። (3) በኢየሱስ ያምናሉ (1ዮሐ 5፥1)። (4) እግዚአብሔርን ይወዳሉ፣ ትእዛዙንም ይጠብቃሉ (1ዮሐ 5፥2)። ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔር ልጆች አንዳንድ በረከቶችን መጠበቅ ይችላሉ፤ (1) ዓለምን ማሸነፍ እንችላለን (1ዮሐ 5፥4)። (2) ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረት አለን፤ ስለዚህም «አባ፣ አባት» ብለን መጥራት እንችላለን (ሮሜ 8፥15፤ ገላ 4፥6)። (3) ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን (ሮሜ 8፥17)። (4) ወደ ፊት ኢየሱስ ሲመለስ ሌሎች በረከቶችንም እንጠብቃለን (ሮሜ 8፥19-21፤ 1ዮሐ 3፥1-2)።

እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተለዩ ናቸው። እነርሱን አስመልክቶ ቁ 13 ሦስት ያልተለመዱ ገለጻዎችን ያቀርባል። በመጀመሪያ፣ በሌላ ትርጉም «ከተፈጥሮ ውልደት» የሚለው ግሪክኛው በቀላሉ «ደም» ይለዋል። ሁለተኛ፣ «ከሰው ፈቃድ» የሚለው፣ «ከሥጋ ፍላጎት/ ምኞት» ቢባል ምናልባት የተሻለ ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ሦስተኛ፣ «ከወንድ ፈቃድ» የሚለው አንድ ሰው ዘር ለመተካት ያለውን ነገር ያመለክታል። እነዚህ ሦስቱም በሥነ-ተዋልዶ የሚኖሩትን

አካላዊ፣ ስሜታዊና ተዛምዶአዊ ግንኙነቶችን ነው የሚያመለክቱት። የእግዚአብሔር ልጆች ሲል ዮሐንስ ይህን ማለቱ አልነበረም። ምንም እንኳ በዘመኑ የነበሩት የግሪኮች የአምልኮ ድርሳናት አማልክትና ሰዎች የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሚያደርጉ አዘውትረው ቢናገሩም፣ የእግዚአብሔር ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ከመንፈሳዊው እንጂ ከአካላዊ አንጻር አለመሆኑን ዮሐንስ አጥብቆ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| ዮሐ 1፥14 | [14]ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን[m] ክብር አየን። |

*[m]ወይም ብቸኛ ልጁ የሆነውን*

ተሠግዎ በታሪክ ውስጥ ምናልባት አስደናቂው ታሪክ ሳይሆን አይቀርም። አንድምታው ጥልቅና ሰፊ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ግንኙነት ማድረግ መፈለጉንና ከእኛ ጕስቋላ ማንነት የተነሣ ያንን ማድረግ የሚችለው በእኛ ደረጃ ከተናገረና ከእኛ እንደ አንዱ ከሆነ ብቻ መሆኑን ያመለክታል። እግዚአብሔር በእርግጥ ተፈጥሮችንና መከራችንን እንደሚረዳ ያመለክታል (ዕብ 2፥17-18)። ኢየሱስ የመጣው ለኃጢአታችን ለመሞት በመሆኑ የእኛ ኀጢአት ምን ያህል አስከፊ ነገር እንደ ሆነ ያመለክታል። እግዚአብሔር ሰውን መውደዱንና በሰው ልጆች ታሪክም ውስጥ ተሳትፎ ማድረጉን ይነግረናል። እንዲያውም በታሪክ ዓቢይ ተዋናኙ እርሱ ነው። በመለኮትና በሰው ልጆች መካከል ያለውን ድልድይ መሻገር እንደሚቻል ይነግረናል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ሕልዎት ባለበት በዚያ ኅብረት የማድረግ ተስፋ አለን።

ኢሳይያስ 9፡6-7 ስለ ተሠግዎ ትንቢት ይናገራል። በእርግጥ እግዚአብሔር በሰው አካል ውስጥ ይኖራል ብሎ ማሰብ እንኳ እጅግ



አስቸጋሪ ነው። ከዚህም የተነሣ በአንዳንድ አይሁዶችና እስላሞች ዘንድ ተሠግዎ የክርስቲያኖች ኢ-መንፈሳዊነት መታወቂያ ተደርጐ ተወስዷል። ይሁን እንጂ ወደ አምልኮ ድርሳንነት የሚጠጋው ይህ እውነት ለሚቀበሉት ሁሉ ታላቅ ተስፋና መጽናናት ይሆንላቸዋል። ስለ ተሠግዎ በጣም እርግጠኛ የሆኑ ማስረጃዎች አሉን፦ ትንቢት፣ የክርስቶስ ባሕርይና ያደረጋቸው ተአምራቶች እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ግንኙነት ያደርግ ዘንድ እኛ ወዳለንበት ደረጃ መምጣት ያስፈልገዋል የሚለው ምክንያታዊነት ናቸው። በአጭር አገላለጽ፣ እኛ ወደ እግዚአብሔር መውጣት ስለማንችል፣ እርሱ ወደ እኛ ወረደ።

ተሠግዎን የምንቀበል ከሆነ እንዲህ ዓይነቱን ከአእምሮ በላይ የሆነ ነገር ማመን ያስቻለን ምን እንደ ሆነ አንዳንድ ማስረጃዎችን ማቅረብ እንዳለብን መጠበቁ አግባብ አይደለምን? «ኢየሱስ እግዚአብሔር ያደረገውን አድርጓል? እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች አድርጎአልን?» በማለት መጠየቅ ተገቢ አይሆንም? ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ፣ አስተማማኝ የሆነ «አዎን ትክክል ነው!» የሚል ነው።

1. ትንቢት ተነግሮለት ነበር (ኢሳ 9፥6-7)
2. ተአምራት አድርጎአል (ዮሐ 10፥25)
3. በሥልጣን አስተምሯል (ማቴ 7፥28-29)
4. ልዕለ ተፈጥሮአዊ ዕውቀት ነበረው (ማቴ 21፡1-3፤ 24፥1-2፤ 26፥17-35፤ ማር 2፥6-8፤ ዮሐ 1፡47-49፤ 2፥23-25፤ 4፥16-19፣28-30፤ 11፡4፣11-15፤ 14፡29፤ 16፥4፤ 18፥4፤ 21፥5-6 18-19)
5. ምንም ኀጢአት አልነበረበትም (ዮሐ 8፡46፤ 2ቆሮ 5፥21፤ ዕብ 4፥15፤ 1ጴጥ 2፥22)

6. ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ ነበር (ዮሐ 1፡1-5፣18፤ 3፡35-36፤ 10፡25-30፤ 14፡1-11)

7. ስግደት አምልኮ ተቀብሏል (ማቴ 16፡16-17፤ 26፡6-13፤ ሉቃ 5፡8-9፤ 7፡36-50፤ 19፡35-40፤ ዮሐ 20፡27-29)።

በተሠግዎ አማካይነት (ሎጎስ) ሕይወት ሰጪ ቃል የእግዚአብሔር፣ ብቸኛና «አንድያ» (*monogenes*) ልጅ ሆነ። ግሪክኛው «አንድ» እና «መወለድ» የተሰኙት ጥምር ቃል ነው። ስለዚህም አንዳንድ ትርጉሞች «ብቸኛ ሆኖ የተወለደ» በሚል መልክ አስቀምጠውታል። ችግሩ ግን በአንድ በሆነ መንገድ (ያለ ተሠግዎ) ኢየሱስ ተፀነሰ የሚል ፍንጭ የሚሰጥ መሆኑ ነው። በእርግጥ ቃሉ፣ «ብቸኛ ልጅ» ማለት ሊሆን ይችላል (ሉቃ 7፡12፤ 8፡42፤ 9፡38) «ለየት ያለ» ቢባል ይበልጥ ትክክል ይሆን ነበር። እንዲያውም ዮሐንስ ይህንን ቃል በተጠቀመበት ቦታ ሁሉ (ከ9 መካከል 5ቱ አግባቦች) «ለየት ያለ» ተብለው ቢተረጎሙ ይበልጥ ትክክል ይሆናል (ዮሐ 1፡14፣18፤ 3፡16፣18፤ 1ዮሐ 4፡9)። አጽንዖት የተሰጠው ለተወላጁ ወይም ለሰውየው የተለየ ባሕርይ እንጂ እምብዛም ለመወለዱ ሁኔታ አይደለም። (ከእግዚአብሔር ጋር በተያያዘ መልኩ በቍ 18 ላይ እንዳለው ቃሉ ሲጠቀስ መወለድ የሚለውን አያመለክትም። «እርሱ ከምድቡ አንዱና ብቸኛው ነው» እንደ ማለት ነው (ዕብ 11፡17 ጋር ያነ)።

ዮሐ 1፡15-18

[15]ዮሐንስም «ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ስለ ነበረ ከእኔ ይልቃል ብዬ የመሰከርሁለት እርሱ ነው» በማለት ጮኾ ስለ እርሱ መሰከረ። [16]ከእርሱ ሙላት ሁላችንም በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል፤ [17]ሕግ በሙሴ በኩል ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መጣ፤ [18]ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ ልጅ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው።

*በቍ 14 እና 18 ወይም ብቸኛ ልጅ*



ሁላችንም «በጸጋ ላይ ጸጋ» (ቍ 16) እንደምንቀበል በማንበባችን በእርግጥ ደስተኞች ነን። አንዳንድ ትርጉሞች ቍ 16ን፣ «በበረከት ላይ በረከት» ብለው ያቀርቡታል። ይህ ግን በትክክል ምን ማለት ነው? ምን ማለት እንደሆነ ከመመርመራችን በፊት በመጀመሪያ ደረጃ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው ማን መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል፤ ሐዋርያው ዮሐንስ ነው ወይስ መጥምቁ ዮሐንስ? የጻፈው በ95 ዓ.ም ሐዋርያው ዮሐንስ ከሆነ ምናልበት፣ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ በሙሴ ከተሰጠው ሕግ እጅግ ልቆ ተገኘ፣ የሙሴንም ሕግ ተካ» ማለቱ ሊሆን ይችላል።[16] አዲሱ መደበኛ ትርጉም የመጥምቁ ዮሐንስን ቃል የሚጨርሰው ቁ. 15 ላይ ነው። ሆኖም የጥቅሱን መጨረሻ ቍ. 16፣17 እንዲያውም ቍ 18 ላይ እንኳ ልናደርገው እንችላለን። ታዲያ፣ ይህን ሉተናገረው ለዮሐንስ መጥምቁ «ጠጠር ያለ ነገረ መለኮት» ይሆንበት ይሆን? (ዮሐ 1፡23፣29፣33 ጋር ያነ)። እንግዲህ ይህንን የተናገረው መጥምቁ ዮሐንስ ነበር ብለን ካሰብን፣ «እግዚብአሔር በተደጋጋሚ ሕዝቡን ባርኮአል። አሁን ደግሞ በኢየሱስ በኩል ታላቁን ስጦታውን ተቀበልን»[17] ማለቱ ሊሆን ይችላል።

የትኛውንም አመለካከት ብንቀበል ቍ. 17 የቍ. 16 ገለጻ በመሆን ያገለግለል። በኢየሱስ በኩል የመጣው በረከት በሙሴ ሕግ በኩል ከመጣው ጋር ተነጻጽሮአል። ዘፀአት 33-34 ለዚህ ሐሳብ መሠረት ወይም ዳራ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፤ እንዲያውም በትክክል

---

[16] ይህን አመለካከት በW.J Dumbrell , "Law and Grace: The Nature of the Contrast in John 1:17," *EvQ* 58 (Jan 1986): 25-37 ይመ። *anti* የሚለውን እንደ ንጽጽር አድርጎ ያነበዋል። ስለዚህም ይህ የአዲስ ማኅበረ ሰብ መጀመርን፣ («የእግዚአብሔር ልጆች» ቍ 12) አዲስ ሕግ መስጠቱን (ጸጋ) እንደሚያመለክት ይናገራል።

[17] ይህን አመለካከት Z.C. Hodges, "Grace after Grace - John 1:16," *BibSac* 135 (Jan 1978 ): 34-45 ይመ።

ለመናገር 33፥13 ወይም 34፥6[18] በተለየ ሁኔታ ዳራ ሊሆኑ ይችላሉ:: እስራኤል ስትናፍቅ የነበረው፣ ለእኛም እጅግ ስንፈልገው የነበረው መምጣቱን ዮሐንስ ይናገራል:: «ሕግ ከሥጋ ባሕርይ የተነሣ ደክሞ ሊፈጽም ያልቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኀጢአተኛ ሰው አምሳል፣ የኀጢአት መሥዋዕት እንዲሆን በመላክ ፈጸመው» (ሮሜ 8፥3)::

ከድነት ጋር ሌሎች ብዙ በረከቶችም መጥተዋል:- መንፈስ ቅድስ፣ ሰላም፣ ድል፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች፣ በቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ጋር ኅብረት ማድረግ፣ የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ፣ የአካል ፈውስና ዓላማ ያለው ሕይወት ጥቂቶቹ ናቸው:: በእርግጥም በክርስቶስ በበረከት ላይ በረከት ተቀብለናል::

ኢየሱስ ከሰጠን ታላላቅ በረከቶች አንዱ ስለ እግዚአብሔር ፍንጭ ማሳየቱ ነው:: ሙሴ እግዚአብሔርን ማየት እንዲችል ጠይቆት ነበር (ዘፀ 33÷18) እግዚአብሔር ግን ጀርባውን ማለትም እርሱ ካለፈ በኋላ የሚቀረውን ክብር ብቻ እንዲያይ ፈቀደለት:: ማንም ሰብዓዊ ፍጡር ከዚህ ሕይወት ሳይለይ እርሱን ማየት እንደማይችል እግዚአብሔር ተናግሯል (ዘፀ 33÷20)::

እንግዲያውስ እግዚአብሔር ከአዳም ጋር በአትክልቱ ቦታ ስለ መመላለሱ የሚገልጸውን ዘፍ 3÷8ን ወይም በመምሬ ትልልቅ ዛፎች አቅራቢያ ለአብርሃም መገለጡን እንደሚናገረው ዘፍጥረት 18÷1ን ስለመሳሰሉት ምንባቦችስ ምን እንላለን? እነዚህ መገለጦች (theophanies) ማለት እግዚአብሔር በሌላ ግዙፍ አካል ምሳሌ መገለጡን የሚያመለክቱ ናቸው በማለት መደምደም ይኖርብናል:: ኮትሬል እንደሚሉት (*God the Creator*, p. 230) የዚህ ዓይነት አካሎች መገለጡ ለተሰጠበት ቅጽበት ብቻ እም ሀበ አልቦ የተገኙና በኋላ ግን ወደ ምንምነት ተቀይረው የተሠወሩ ናቸው:: በመቀጠልም፣ «መንፈስ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ለቁሳዊው ዓለም እንደማይታይ ሁሉ፣ ያልተፈጠረና ምጡቅ በመሆኑ በመንፈሳዊው ዓለምም የማይታይ ነው» ብለዋል (ገጽ 231)::

ኢየሱስ ግን መረዳት በምንችልበት መንገድ፣ በሕይወት መኖራችንን በማይጻረር ሁኔታ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አሳየን:: እርሱን ስናይ፣ የሰውን አምሳል ተላብሶ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ተግባርና ባሕርይ እንመለከታለን:: ቍ. 18 በኢየሱስ ከተቀበልናቸው ታላላቅ በረከቶች ስለ አንዱ የሚገልጽ ብቻ ሳይሆን፣ አምላክ መሆኑን በድፍረት ከሚያጸኑት አባባሎች አንዱ ነው::

**§ 3**
**የኢየሱስ የዘር ሐረግ**
**(ማቴ 1፥1-17፡ ሉቃ 3፥23-38)**

ሉቃስ የተጠቀመበት መግቢያ ጥሩ የግሪክ ታሪክ አጻጻፍ ዓይነት ነው:: የዮሐንስ መግቢያ ደግሞ የአይሁድን የጥበብ ሥነ ጽሑፍ ያሳስበናል:: የማቴዎስ መግቢያ የአይሁድን ሕጋዊ ወይም ሃይማኖታዊ ሰነድ ይመስላል:: ከዚህም ባሻገር የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን የሚጀምረውም ሆነ የሚፈጽመው የትውልዶችን የዘር ሐረግ በማዘረዝር ነው:: የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን የሚያበቃው በ1ኛ እና በ2ኛ ዜና መዋዕል መጻሕፍት ነው:: ኦሪት ዘፍጥረት «የ ... የትውልድ ሐረግ እንደሚከተለው ነው» የሚለውን አባባል እንደ መጽሐፉ ዋነኛ መክፈያ ይጠቀምበታል (ዘፍ 6÷9፤ 10÷1፤ 11÷10፣27፤ 25፡12፣19፤ 36፡1፣9፤ 37፡2):: ማቴዎስም ቢሆን የሚጀምረው፣ የትውልድ ሐረግ» (*biblos geneseōs*)[19] በማለት ነው::

[18] የሚጋጩ አመለካከቶችን L.J Kuyper, "Grace and Truth: An Old Testament Discription of God , and Its Use in the Johannine Gospel" *Int* 18 (1964 ): 3; and A. Hanson, "John 1:14-18 and Exodus 34 ," *NTS* 23 ( 1976 ): 90-95 ይመ::

[19] J.Nolland, "What Kind of Genesis Do We Have in Mt 1:1?" *NTS* 42/3 [1996]: 463-471 የማቴዎስ ወንጌልን ዘፍጥረት ድጋሚ እንደ ሆነ አድርገን

ልክ የትውልድ ሐረጎችን ከዘረዘረ በኋላ በቁጥር 18 ላይ «የልደት ታሪክ» (ቃል በቃል ውልደት) የሚለውን ሐረግ መጠቀሙ ትኩረት የሚሰጠው ይመስላል። ስለሆነም ይህ ቃል የማቴዎስን መግቢያ በቅንብብ ያስቀምጠዋል።

የትውልድ ሐረጎች ሦስት ጠቃሚ ተግባሮች አላቸው፦ (1) የአንድን ዘር ሐረግ ባሕርይ ለማሳየት - በሌላ አነጋገር የአንድ ሰው ዘርያዎች ልክ እንደ ሰውዬው እንደ ሆኑ ይታሰብ ነበር። የሴት ትውልድ ከቃየን ትውልድ ጋር በንጽጽር በቀረበበትም ስፍራ የሆነው ይኸው ነበር (ዘፍ 4:25 እና የሚከተሉት)። (2) በተለዩ ሰዎች በኩል እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ያደረገውን ለማሳየት። ይህ የጋራ ማንነትን ለመመሥረት ይረዳል። (3) ማን ማንን እንደ ወለደ (ባይሎጂያዊ የውልደት ሐረግ) መኖሩን ለማረጋገጥ።

ሦስተኛው ዓላማ ሕጋዊና ፖለቲካዊ ውል ለማድረግ አስፈላጊ ነበር።

(1) ንብረት የሚከፋፈለው በቤተሰብ ውስጥ ባለ ዝምድና ነበር።

(2) የአሮን ክህነት «ማን ቢወልድ ማንን» (ባይሎጂያዊ የውልደት ሐረግ) መታወቅ አለበት ይሉ ነበር። እንዲያውም በዕዝራ ዘመን የትውልድ ሐረጋቸውን በመዘርዘር ማንነታቸውን ማስረገጥ ያልቻሉ ካህናት ንፁሕ እንዳልሆኑ ይቈጠሩ ነበር (ነህ 7:61-64)። ድብልቅ ጋብቻ በበዛበት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በነበረው ወቅት ይህ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል (ዕዝራ 2:59-63፤ 10:9-44፤ ነህ 13:[illegible])።

(3) የትውልድ ሐረጎች የዘርያን ሰንሰለት «ንፁሕ» አድርጎ የመጠበቂያ መንገድ ነበር (ዘዳ 7:1-4፤ 23:1-8)። በተለይ ደግሞ

---

[illegible] እንደሚገመት የመቅረዱ ኢየሱስ ከአዳም ጋር ያለውን የሚመስለው ዳዊትን ነው።

የግሪኮች ፍልስፍናና ባህል ከተስፋፋበት ዘመን በኋላ ይህን ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

(4) በምድረ በዳ ይሰፍሩ በነበሩበት ጊዜ እንኳ (ዘኍ 2:2፤17፤ 10:1-28)። የአይሁድ ወታደራዊ አደረጃጀት የተመሠረተው በነገድ ላይ ነበር (ዘኍ 1:2-4)።

(5) በመቅደሱ ውስጥ ቀረጥና መባ የሚሰበሰበው በዘር ሐረግ መሠረት ነበር (ዘኍ 7:11-89)።

(6) ከይሁዳ ነገድ የሆነው የዳዊት ሥርወ መንግሥት በቀጥታ የተዋረድ ሥርዓት ላይ የተደገፈ ነበር። በተለይም ከመሲሐዊ ትንቢት ፍጻሜ ጋር በተያያዘ ይህ በጣም አስፈላጊ ነበር (ኢሳ 11:1-5)።

1 የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የሆነው
የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የሚከተለው ነው፤ ማቴ 1:1-17
2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፤
ያዕቆብ ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤ 3 ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤
ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤ ኤስሮምም አራምን ወለደ፤ 4 አራም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብ ነአሶንን ወለደ፤ ነአሶን ሰልሞንን ወለደ፤ 5 ሰልሞን ቦዔዝን ከረዓብ ወለደ፤
ቦዔዝ ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድ እሴይን ወለደ፤ 6 እሴይ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ።
ዳዊት የኦርዮ ሚስት ከነበረችው ሰሎሞንን ወለደ፤ 7 ሰሎሞን ሮብዓምን ወለደ፤
ሮብዓም አቢያን ወለደ፤ አቢያን አሣፍን ወለደ፤ 8 አሣፍ ኢዮሳፍጥን ወለደ፤ ኢዮሳፍጥ
ኢዮራምን ወለደ፤ ኢዮራም ዖዝያንን ወለደ፤ 9 ዖዝያን ኢዮአታምን ወለደ፤ ኢዮአታም
አካዝን ወለደ፤ አካዝ ሕዝቅያስን ወለደ፤ 10 ሕዝቅያስ ምናሴን ወለደ፤ ምናሴ አሞንን
ወለደ፤ አሞንም ኢዮስያስን ወለደ፤ 11 ኢዮስያስ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኢኮንያንንና
ወንድሞቹን ወለደ፤ 12 ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣ ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤ ሰላትያልም
ዘሩባቤልን ወለደ፤ 13 ዘሩባቤል አብዩድን ወለደ፤ አብዩድ ኤልያቄምን ወለደ፤
ኤልያቄምም አዛርን ወለደ፤ 14 አዛር ሳዶቅን ወለደ፤ ሳዶቅ አኪምን ወለደ አኪምም
ኤልዩድን ወለደ፤ 15 ኤልዩድ አልዓዛርን ወለደ፤ አልዓዛር ማታንን ወለደ፤ ማታን

ያዕቆብን ወለደ፤ [16]ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ፤ ዮሴፍም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የማርያም እጮኛ ነበር። [17]እንግዲህ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ዐሥራ አራት ትውልድ፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ዐሥራ አራት ትውልድ፣ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ልደት ዐሥራ አራት ትውልድ ይሆናል።

*[18] 11 ዮስያን ማለት ነው፤ ቁ 12ንም ይመ።*

*[19] 17 ወይም መሲሕ «ክርስቶስ» (በግሪክ) እና «መሲሕ» (በዕብራይስጥ) በዐቱም «የተቀባው የሚል ትርጉም አላቸው።*

ማቴዎስ የትውልድ ሐረግን 14 ስሞችን እያንዳንዳቸው በእስራኤል ታሪክ ዓቢይ ወቅቶችን ወክለው ቀረበ ሦስት ምድቦች ማለትም አብርሃም፣ ዳዊት፣ ምርኮ በማለት ከፋፍሎ አስፍሮአል (ቁ 17)። ማቴዎስ ኢየሱስ የመላው አይሁድ ታሪክ ፍጻሜ መሆኑን የማሳየት ዕቅድ ነበረው። ችግሩ ግን ሦስተኛው የስሞች ምድብ የያዘው 13 ትውልዶችን ብቻ መሆኑ ነው። ማቴዎሥው ቆጠራ ላይ ተሳስቶ ይሆን? ባለሙያ ቀረጥ ሰብሳቢ በትውልድ ቆጠራ ላይ የመሳሳቱ አጋጣሚው ከፍ ያለ አይደለም። የባሰውን ግራ የሚያጋባው ሌላው ጉዳይ ደግሞ በቍ. 9 ላይ ማቴዎስ በ1ኛ ዜና መዋዕል ላይ ባለው የትውልድ ሐረግ የሚገኙትን አራት ስሞችን (አካዝያ [illegible] አሜስያስ እና ኢዮአቄምን) መዝለሉ ነው። በሌላ አነጋገር ማቴዎስ 14/17/14 ስሞችን ማስፈር ይችል ነበር እርሱ ግን አራቱን በመገደፉ 14/13/14 የሚለው ሥርዓት ሊከተል ችሏል።

እዚህ ላይ አንድ ማወቅ ያለብን ነገር አይሁድ "የተሟላ" ዝርዝር ስለማቅረብ ይህን ያህል ደንታ የሌላቸው መሆኑን ነው (ይህን መሳዩ ነገር የሚጠብቁት በዋናነት ምዕራባውያን ናቸው)። እነርሱ ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡት ሐቁ በግልጽ መነገሩ ላይ ነው። በትውልድ ቆጠራ ውስጥ ብዙውን ጊዜ የሚገደፉት ይህን ያህል አስፈላጊ እንዳልሆኑ የሚታሰቡ ወይም ቤተሰቡ የማይኮሩባቸው ናቸው። ከዚህም በላይ



«አባት» «ልጅ» ወይም «ወለደ» የሚሉትን ቃላት አንድ ሰው ከአያቱ ወይም ከልጅ ልጅ ወይም በዘር ሐረጉ ዝቅ ባለ ደረጃ ያለውን ግንኙነት ለማመልከት ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህ ቃላት በቤተ ሰቡ ያሉ ሁሉንም ሰዎችን ዝምድና ለመግለጽ ይጠቀሙባቸዋል እንጂ በሳይንሳዊ መንገድ የውልደት ዝምድናን አያሳዩም። ስለሆነም ከትውልድ ሐረጉ የጎደሉት ሰዎች ስም ቢገደፍም እንኳ አንድ አያት ዘር ተከትሎአል ብለን በትክክል መናገር እንችላለን።

አንዳንዶች እነዚህ ግድፈቶች የወንጌሉን ቃል በብራና ያሳፈረው ጸሐፊ ስሕተት ውጤት እንደ ሆነ ያስባሉ። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ስሞች የተገኙት በ1ኛ ዜና መዋዕል 3:11-12 ነው። የጸሐፊው ዓይን ከአካዝያስ ተንሸራቶ ዓዛርያስ ላይ በማረፉ በመካከል ያሉ ሦስት ስሞችን ዘለሎአቸው ይሆናል።[20] ምናልባትም የዮአቄም የተገደፈው ከልጁ ከኢኮንያን ስም ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ነው የሚል ገለጻ መስጠትም ይቻላል (1ዜና 3:16 )። ያም ሆነ ይህ ማቴዎስ ሲጽፍ ስሕተት ፈጽሞአል የሚል ክስ ተሰንዝሮበታል።

ይሁን እንጂ የተሻለ ተቀባይነት ያለው መግለጫ ማቴዎስ የትውልድ ሐረጉን እያንዳንዳቸው ዐሥራ አራት ትውልዶችን በያዙ ሦስት ምድቦች ሆን ብሎ አስቀምጧል የሚለው ነው። በሌላ አነጋገር የአጻጻፍ ቅንብሩን ለመከተል ሲል አራቱን ነገሥታት ሆን ብሎ ገድፎአቸዋል። እዚህ ላይ፣ «ማቴዎስ በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ዐሥራ አራት ሰዎችን ማስቀመጥና በመካከል ባለው ምድብ ግን 13 ሰዎችን ብቻ ማስፈር የፈለገው ለምንድነው?» የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

[20] J. Nolland "Jeconiah and His Brothers (Mt 1:11)," *BBR* 7 [1997]: 169-178. ላይ እንደሚሉት ከእነዚህ መሐል የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ሆን ተብሎ የተገደፉት ከአክዓብ ዘር ጋር የተጋቡ በመሆናቸውና በዚህም ምክንያት ከእርግማን በታች በመሆናቸው ነው (1ነገ 21:21-24)።

ለሁለቱም ጥያቄዎች በዳዊት ምክንያት የሚል መልስ መስጠት ይቻላል::[21]

ቁጥር 1 ላይ ሌሎች የትውልድ ሐረጐችን ቅደም ተከተል ባልጠበቀ ሁኔታ ማቴዎስ ሆነ ብሎ ዳዊትን ከአብርሃም በፊት እንዳደረገው ተመልክተናል:: ዳዊትን መጀመሪያ ያደረገው ለምንድነው? ለጉዳዩ የተለየ አጽንዖት ለመስጠት ነው:: እንዲያውም ቁጥር 1 ላይ ዳዊት ተቀዳሚውን ቦታ መያዙ የጠቅላለው መጽሐፍ ቁልፍ ነው:: የማቴዎስ ልዩ አጽንዖት ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ፣ ቃል የተገባለት የዳዊት ልጅ መሆኑን መግለጹ ነው:: እንግዲህ ይህን ግንዛቤ በመያዝ አሁን ወደ ቁጥር 6 መለስ በማለት ለዳዊት፣ «እጥፍ ድርሻ» እንሰጠዋለን:: በሌላ አነጋገር ዳዊትን ሁለቴ ስንቆጠር ዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱ ትውልዶች ቀመር ወዲያውኑ 14/14/14 ይሆናል:: በጣም አስገራሚው ነገር ደግሞ የዳዊት ስም በዕብራይስጥ አኃዛዊ ተመን 14 መሆኑ ነው:: ይህን መሳዩ «አኃዛዊ ትርጉም አሰጣጥ» ጉዳይ (*gematria*) ለብዙዎቻችን እንግዳ ቢሆንም በአይሁድ መምህራን ዘንድ ግን የተለመደ የአተረጓጐም ዘዴ ነበር:: የዕብራይስጥ ቋንቋ ፊደሎቹን ቁጥርን የመቀመሪያ ስልት አድርጐም ይጠቀምባቸዋል:: ስለሆነም ልጆች ከስሞቻቸው ፊደሎች ጋር ሂሳብንም አብረው ይማራሉ:: በመሆኑም ይህን መሳዩን የአቈጣጠር ዘዴ የተለመደና ማንም በቀላሉ የሚረዳው አድርጐታል:: እንደ ሉቃስና እንደ ዮሐንስ ሁሉ ማቴዎስም የመጽሐፉን

---

[21] ይህን የትውልድ ሐረግ በቀላሉ ማስታወስ እንዲቻል ከማድረግ ባሻገር በአዋልድ ጽሑፎች 14 ቁጥር ጥቅም ላይ ውሏል:: (ለምሳሌ 2ኛባሮክ 53-74 ጊዜው መመላቱንና የመሲሑ ዘመን መምጣቱን ለማመልከት የH.C Waetjen, "The Genealogy as the Key to the Gospel According to Matthew *JBL* 95/2 (1976): 205-230 ይመ::



መግቢያ ያዘጋጀው በሚገርም መልኩ ለአንባቢዎቹ በሚመጥን መንገድ ነበር::[22]

የማቴዎስን የትውልድ ሐረግ አቀራረብ የተለየ የሚያደርገው ሌላው ገጽታ ሴቶችንም መጨመሩ ነው:: በትውልድ ሐረግ አቀራረብ ውስጥ ሴቶችን መጨመር በአብዛኛው ያልተለመደ ቢሆንም የማይደረግ ነገር ነው ማለት አይደለም (1ዜና 1፡32፤ 2፡17-21፣24፣26):: ይሁን እንጂ በምሳሌነት እንደሚያገለግሉ መጠበቅ ይቻላል:: በተለይ ደግሞ እነዚህን ሴቶች መጨመሩ ጉዳዩን አሳፋሪ ያደርገዋል:: ትዕማር አመንዝራና ከሥጋ ዘመዶቿ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ነበረች (ዘፍ 38፡6-30):: ረዓብ በትውልዷ የሌላ አገር ዜጋ የሆነች ሴትኛ አዳሪ ነበረች (ኢያሱ 2፡1፣3፤ 6፡17፣23፣25፤ ዕብ 11፡31):: ሩትም እንዲሁ የባዕድ አገር ሰው ነበረች:: ቤርሳቤህ አመንዝራ ከመሆንዋ በተጨማሪ ከኬጢያዊ[23] ጋር በመጋባቷ እንደ ሌላ አገር ሴት ሳትቆጠር አትቀርም::

እነዚህ ሴቶች በመሲሑ የዘር መስመር ውስጥ አልነበሩም! ይሁን እንጂ ቦግ ብሎ በሚታይና የእግዚአብሔርን ጸጋ በሚያሳስብ መልኩ ስማቸው በዚያ ሰፍሮአል:: ማርያም እንደ ተደፈረች ስትቆጠርና[24] በዚህም ምክንያት ከቤተሰብና ከወዳጆቿ ስትገለል እነዚህ ሴቶች አጠገቧ ቆመው፣ «አይዞሽ ምን ሊሰማሽ እንደሚችል እንረዳለን» ሊሏት ይችሉ ነበር::

---

[22] ይህን «የቍጥር ቀመር»ን በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት፣ B.M. Newman, "Matthew 1:1-18: Some Comments and a Suggested Restructuring," *BT*. 27/2 (Apr 1976 ): 209-212 ይመ::

[23] F.H. Graves, "Matthew 1:1-17," *Rev Exp* 86 (1989): 595-600 ጋር ያነ::

[24] ማርያምን በተመለከተ የነበሩት ጥንታዊ የአይሁድ አስተሳሰቦች የተሰሳሰሉ አልነበሩም:: አንዳንዶች ዮሴፍ ወይም አንድ ሮማዊ ወታደር እንደ ደፈራት ያስባሉ አንዳንዶች ግን ሴሰኛ እንደ ነበረች አድርገው ነው የሚያቀርቧት::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማቴዎስ ማርያምን ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ይገልጸታል፡፡ አምስቱም ሴቶች በዳዊት የዘር መስመር ወንድ ልጆችን ወልደዋል፡፡ የመጀመሪዎቹ አራቱ «ከ...» (*ek tes*) የሚል ተመሳሳይ የሆነ የቋንቋ አወቃቀር ስልት ተጠቅመዋል፡፡ ማርያምን በተመለከተ ሲናገር ግን፣ «የኢየሱስ ክርስቶስ እናት» (ወይም «ኢየሱስን የወለደች» - በ1952 ትርጉም) (*ex hes egennethe*) በማለት የአነጋገር መዋቅሩ ይለወጣል፡፡ ስለ ሆነም ማቴዎስ ረቀቅ ባለ መንገድ የኢየሱስን ከድንግል መወለድ የሚናገር ይመስላል፡፡

ሉቃስ ወደሚያቃርበው የትውልድ ሐረግ ዝርዝር ከመሄዳችን በፊት ልናየው የሚገባን አስገራሚ የሆነ ነገረ መለኮታዊ እንቆቅልሽ አለ፡፡ በ1ኛ ሳሙኤል 7፥12-17 እግዚአብሔር በሰሎሞን የትውልድ ሐረግ በኩል ዙፋኑ ላይ የሚቀመጥ ዘር ምን ጊዜም እንደሚኖር ለዳዊት ቃል ገብቶለት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኤርምያስ 22፥30፣ «አንድ እንኳ የረባ ዘር የማይወጣለት፣ አንድ እንኳ በዳዊት ዙፋን የሚቀመጥ፣ ወይም በይሁዳ የሚገዛ የማይኖረው ነውና፣ በሕይወት ዘመኑ የማይከናወንለት መካን ሰው ብላችሁ መዝገቡት» የሚል እናነባለን፡፡ እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔር ሁለቱንም ተስፋዎች እንዴት መፈጸም ይችላል?

ኢየሱስ የዮሴፍ የማደጐ ልጅ እንደ መሆኑ መጠን በሕጉ መሠረት የዮሴፍ ዘር ሐረግ ወራሽ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ ኢየሱስ የዮሴፍ የሥጋ ልጅ አለመሆኑን ማቴዎስ በ18-25 ብቻ ሳይሆን በቁ 16 ጭምር ግልጽ አድርጐአል፡፡ ከቁ 2-16 ባሉት ማቴዎስ 39 ጊዜ «የ ... አባት ሆነ» (*egennesen* ) የሚለውን ግሥ ተጠቅሟል፡፡ ከዚያም በድንገት ቁጥር 16 ላይ የማርያም እጮኛ ስለ ነበረው ዮሴፍ ሲናገር ግን አቀራረቡን ይለውጣል፡፡ ኢየሱስ የዮሴፍ የማደጐ ልጅ (በዚህ ምክንያት በሕጉ መሠረት የዳዊት ዙፋን ወራሽ) ለማርያም ደግሞ በሥጋ ልጇ



እንደ ነበር ማቴዎስ በረቀቀ ሆኖም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ገልጾታል፡፡ ስለሆነም በ2ኛ ሳሙኤል 7፥12-17 እና በኤርምያስ 22፥30 የተነገሩት ተፈጽመዋል ማለት ነው፡፡

²³ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር ዕድሜው ሠላሣ ሉቃ 3፥23-38
ዓመት ያህል ነበር፤ ሕዝቡም እንደ መሰላቸው የዮሴፍ ልጅ
ሆኖ፣ የኤሊ ልጅ ²⁴የማቲ ልጅ፣ የሌዊ ልጅ፣ የሚልኪ ልጅ፣ የዮና ልጅ፣ የዮሴፍ
ልጅ፣²⁵የማታትዮ ልጅ፣ የአሞጽ ልጅ፣ የናሆም ልጅ፣ የኤሲሊም ልጅ፣ የናጌ ልጅ፣
²⁶የማአት ልጅ፣ የማታትዩ ልጅ፣ የሴሜይ ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣ የዮዳ ልጅ፣ ²⁷የዮናን
ልጅ፣ የሬስ ልጅ የዘሩባቤል ልጅ፣ የሰላትያል ልጅ፣ የኔሪ ልጅ፣ ²⁸የሚልኪ ልጅ፣
የሐዲ ልጅ፣ የዮሳስ ልጅ፣ የቆሳም ልጅ፣ የኤልሞዳም ልጅ፣ የኤር ልጅ፣ ²⁹የዮሴዕ
ልጅ፣ የአልዓዛር ልጅ፣ የዮራም ልጅ፣ የማጣት ልጅ፣ የሌዊ ልጅ ³⁰የስምዖን ልጅ፣
የይሁዳ ልጅ የዩሴፍ ልጅ፣ የዩናም ልጅ፣ የኢልያቄም ልጅ፣ ³¹የሜልያ ልጅ፣ የማይናን
ልጅ፣ የማጣት ልጅ፣ የናታን ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ ³²የእሴይ ልጅ፣ የኢዮቤድ ልጅ፣
የቦዔዝ ልጅ፣ የሰልሞን ልጅ የነአሶን ልጅ፣ ³³የአሚናዳብ ልጅ፣ የአራም ልጅ፣ የአርኒ
ልጅ፣ የኤስሮም ልጅ፣ የፋሬስ ልጅ፣ የይሁዳ ልጅ፣ ³⁴የያዕቆብ ልጅ፣ የይስሐቅ ልጅ፣
የአብርሃም ልጅ፣ የታራ ልጅ፣ የናኮር ልጅ፣ ³⁵የሴሮህ ልጅ፣ የራጋው ልጅ፣ የፋሌቅ
ልጅ፣ የአቤር ልጅ፣ የሳላ ልጅ፣ ³⁶የቃይንም ልጅ፣ የአርፋክስድ ልጅ፣ የሴም ልጅ፣
የኖኅ ልጅ፣ የላሜህ ልጅ፣ ³⁷የማቱሳላ ልጅ፣ የሄኖክ ልጅ፣ የያሬድ ልጅ፣ የመላልኤል
ልጅ፣ የቃይናን ልጅ፣ ³⁸የሄኖስ ልጅ፣ የሴት ልጅ፣ የአዳም ልጅ፣ የእግዚአብሔር
ልጅ፡፡

*ü32 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሳላ ይላሉ*
*ü33 አንዳንድ ቅጆች አሚናዳብ ልጅ የአዲም ልጅ  የአርኒ ልጅ ይላሉ፤ ሌሎች ቅጆች ሰፋ ያለ ልዩነት ያሳያሉ፡፡*

በማቴዎስና በሉቃስ የትውልድ ሐረግ አቀራረብ ሦስት ዋና ዋና ልዩነቶች አሉ፡፡

(ሀ) ማቴዎስ ከአብርሃም ይጀምርና ወደ ኢየሱስ ይሄዳል፤ ሉቃስ ግን ከኢየሱስ ይጀምርና ወደ ኋላ እስከ አዳም ድረስ ይሄዳል፡፡

(ለ) የሉቃስን ዝርዝር ከታች ወደ ላይ ገልብጠን ከማቴዎስ ዝርዝር ጐን ብናስቀምጠው በአብርሃምና በዳዊት መከከል ያለው ትውልድ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ይሆናል። ይሁን እንጂ በዳዊትና በዮሴፍ መካከል በጉልህ የሚታይ ሁለት ለየት ያለ ዝርዝር አላቸው። በሁለቱም ዝርዝሮች ቅደም ተከተላቸውን በተመሳሳይ ሁኔታ ጠብቀው የሚገኙ ስሞች ሰላትያልና ዘሩባቤል ናቸው (ማቴ 1፡12፤ ሉቃ 3፡27)።

(ሐ) የሉቃስ ዝርዝር በዳዊትና በክርስቶስ መካከል አርባ ትውልዶችን አስፍሮአል፤ የማቴዎስ ግን ሃያ ስድስት ብቻ ነው ያሳፈረው።

ይህንን ልዩነት እንዴት መግለጽ ይቻላል? ሁለት የተለያዩ ዝርዝሮችን የምንመለከት ይመስላል። ታዲያ እነዚህ የማንኛው ዝርዝር ናቸው? የተለያዩ በርካታ ዕንሰ - ሃሳቦች ተሰንዝረዋል።[25] የመጀመሪያው ጁሊየስ አፈሪካነስ (240 ዓ.ም) ያቀረበው ነው። እርሱ እንደሚለው ማቴዎስ የትውልድ ሐረግ ዝርዝሩን ያቀረበው በዮሴፍ ወላጅ አባት በኩል ሲሆን፣ ሉቃስ ግን በዮሴፍ ሕጋዊ አባት በኩል ያለውን የዘር ሐረግ ነው ያቀረበው በሌዋውያን ጋብቻ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣ ለእርሱ ዘር መተካት የታናሽ ወንድሙ ኃላፊነት ነበር። በዚህ መንገድ ውርስን ከማስከበር አኳያ የሞተው ሰው እንደ ሕጋዊ አባት በሕይወት ያለው ደግሞ እንደ ወላጅ አባት ይቆጠሩ ነበር። ይህ ዕንሰ - ሃሳብ የተመሠረተው የዮሴፍ ሕጋዊ አባት የሞተው ልጅ ሳይወልድ ነበር በሚለው ግምት ላይ ነው። ምንም እንኳ እንዲህ ሲሆን የሚልበት ሁኔታ ቢኖርም በምንባቡ ውስጥ ጉዳዩ እንዲህ እንደነበረ የሚጠቁም ምንም ምክንያት የለም።

ሁለተኛው ዕንሰ - ሃሳብ ደግሞ በጄ.ግሬሽም ማኪን፣ *The Virgin Birth of Christ* በተሰኘው መጽሐፍ ማቴዎስ የዮሴፍን ሕጋዊ የዘር ሐረግ ሉቃስ ደግሞ የዮሴፍን የውልደት ዘር ሐረግ ያቀርባሉ የሚለውን አቋም በመጀመሪያ የገለጸበት ነው። ልዩነቱ የማቴዎስ አተራረክ ሕጋዊውን ወራሽ ወደ ዳዊት ዙፋን ማመልከቱ ሲሆን ይህም ወደ ዮሴፍ መምጣት ነበረበት። በዚህ አተራረክ መሠረት ደግሞ የዘር ሐረጉ ኢኮንያን ላይ ስለሚቋረጥ (ኤር 22፡30) የሥጋ አባትን በማለፍ የዙፋን ወራሽ ወደነበረው ቀጥሎ ለነበረው ሕጋዊ ሰው (ማለት ሰላትያል ማቴ 1፡12፤ ሉቃ 3፡27 ጋር ያነ) ያሸጋግረዋል። ስለዚህም ማቴዎስ አቅጣጫውን በመለወጥ በሥጋ አባት ከነበረው ሕጋዊ አባት ወደነበረው አዙሮታል። ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ ማቴዎስ፣ «የዳዊት ዙፋን ወራሽ ማን ነው?» የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ ሉቃስ ግን፣ «የዮሴፍ አባት ማን ነው?» ብሎ ይጠይቃል። ይህ አስተሳሰብ መሠረት ያደረገው የማቴዎስ አተራረክ በመካከል ያሉትን ዘለሎ ሕጋዊውን አባት ፍለጋ ሄዷል የሚለውን ግምት ነው። በድጋሚ ይህ በእርግጥ ሊሆን የሚችል ቢሆንም ከጽሑፉ ይህን ለማለት የሚያስችለን ወይም የሚጠቁመን ምንም ማግኘት አንችልም።[26]

ሦስተኛው አስተሳሰብ ደግሞ የሉቃስ ዘገባ የማርያምን ቤተሰብ ይዘረዝራል እንጂ በፍጽም ስለ ዮሴፍ የሚነገረን የለውም የሚል ነው። ቤተሰቡ ውስጥ ወራሽ የሚሆን ወንድ ልጅ እንዳልነበረና ታላቅ ልጅ እንደ ነበረች የምንገምት ከሆነ ሕጋዊ ወራሽ ትሆናለች ማለት ነው (ዘኍ 27፡1-11፤ 36፡1-12)። ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ ከዮሴፍ ጋብቻ ስትፈጽም እርሱም በተጨባጭ ሁኔታ በዚያ የዘር ሐረግ ወራሽ ይሆናል ማለት ነው። ስለሆነም በሉቃስ አተራረክ ዮሴፍ የማርያምን ስፍራ በመውሰድ በዘር ሐረግ ዝርዝር ውስጥ ገብቶአል።

[25] R. Thomas & S. Gundry, *A Harmony of the Gospels* (Chicago: Moody, [illegible]) ገጽ 313-319 ይ።

[26] አር.ፒ. ኔትልሆርስት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዕንሰ - ሃሳቦች ላይ አስደናቂና የሚለይ ሌላ አስተሳሳብ አቅርበዋል። እርሳቸው እንደሚሉት ሁለቱም የትውልድ ሐረግ ዝርዝሮች የሚያቀርቡት የዮሴፍን ዘር ሐረግ ነው፤ ይሁን እንጂ ማቴዎስ የእናቱን የዘር ሐረግ ሲከተል ሉቃስ ግን የአባቱን የዘር ሐረግ [illegible]ል። "Genealogy of Jesus," *JETS* 31 (June 1988): 169-172 ይመ።

አራተኛውም ፅንሰ - ሃሳብ እንደ ሦስተኛው ሁሉ በሉቃስ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር ውስጥ የማርያም የዘር ሐረግ ቀርቧል ይላል:: ይሁን እንጂ ዮሴፍ የዚያ ዘር ሐረግ ክፍል ሳይሆን በሉቃ 3፥23 በቅንፍ የገባና «ሕዝቡም እንደ መሰላቸው (የዮሴፍ) ልጅ፣ የዔሊ ልጅ» ተብሎ ሊነበብ ይገባል:: ከዚህም በላይ የኢየሱስ አያት እንደ መሆኑ መጠን «ልጅ» የሚለው ቃል በእርግጥ ዔሊን የሚመለከተው ሊሆን ይችላል:: ምናልባታም ሉቃስ የማርያምን ስም በዘር ሐረግ ዝርዝሩ ያላሰፈረው ሴቶች በዘር ሐረግ ዝርዝር ውስጥ የሚገቡት እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ብቻ በመሆኑ ሊሆን ይችላል:: ምንም እንኳ ማቴዎስ ዝርዝሩ ውስጥ የአራት ሴቶችን ስም ቢጨምርም ሉቃስ ግን አንድም የሴት ስም አላስገባም::

ይህ የመጨረሻው ፅንሰ - ሃሳብ የማቴዎስ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር የሚናረው ሕጋዊ አባትን ወይም የሩቅ ዝምድናን ሳይሆን በሥጋ መወለድን የሚያመለክት አድርጐታል:: ስለሆነም ማቴዎስ፣ «ወለደ» የሚለውን ቃል ሲጠቀም በመደበኛው ወይም በተለመደው መንገድ እንጂ በምሳሌያዊ መንገድ አልነበረም:: ከዚህም በተጨማሪ ማቴዎስ ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ጋር ስላለው ግንኙነት የሰጠው ትኩረት ጠንካራ ድጋፍ የሚያገኘው የትውልድ ሐረጉ የሚያቀርበው የትውልድ ሐረግ የዮሴፍን ትክክለኛ ወላጅ (እንዲሁም ሕጋዊ የዘር ሐረግ) ለማሳየት ማቴዎስ ማለትም ኢየሱስ የዳዊትን ዙፋን ለመውረስ ያለውን ባለመብት የሚገልጽ ቢሆን ነበር:: ሉቃስ ከተፈጥሮአዊ ውልደቱ አንጻር የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ ማቅረቡ የኢየሱስን ሰብዓዊነት አጽንዖት ለመስጠት ከነበረው ዓላማ ጋር ይስማማል::

ከእነዚህ አዳጋች ጉዳዮች ባሻገረ ከትውልድ ሐረግ ዝርዝሩ የምንማራቸው በርካታ ጠቃሚ ትምህርቶች ይኖራሉ:: በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ትኩረት በሰዎች ላይ መሆኑ ነው:: ይወደናል፤ በየስማችን ይጠራናል ድርሻችንን እንድንወጣና ለእርሱ በመታዘዝ



እንድንኖር ይጠብቅብናል:: ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም በማይታወቁና በሞራል ውድቀት ውስጥ በሚገኙ ሰዎች እንኳ መጠቀም ይችላል:: የእግዚአብሔር እቅድና መንገድ ደካማ ከሆነው የእኛ ጥረት እጅግ የበለጠ ነው:: ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው፤ ዓላማው ይፈጸማል! ሰዎች በሚያደርጉት ተሳትፎ ታሪክን ይሠራል፤ በፈቀደው አቅጣጫም ይመራዋል:: አራተኛ፣ እነዚህ የትውልድ ሐረጐች ስለ ኢየሱስ ማንነት ፍንጭ ይሰጡናል:: በሰው አነጋገር የማርያም ልጅ፣ ከሕጋዊው አንፃር የዮሴፍ ልጅ፣ በመሠረታዊ ደረጃ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው::

# ምድብ ሁለት
# ሁለት መለኮታዊ ልደቶች

ይህ ለየት ብሎ የቀረበው የሉቃስ (ምዕ 1-2) ወንጌል ክፍል አንዴ ወደኋላ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደፊት ሄድ መለስ በማለት የኢየሱስንና የዮሐንስን ልደት ድራማ በሚመስል ልብ-አንጠልጣይ ሁኔታ እያነጻጸረ ይተርካል። የታዋቂ ሰዎችን ሕይወት ታሪክ በዚህ መልኩ ማቅረብ በግሪኮችና በሮማውያን ዘንድ የተለመደ ነበር። ዋናው ዓላማቸው እንዲህ ያለውን ሕይወት አስመልክቶ ምን ማለት እንችላለን? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ነበር። ይኸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ሉቃስ 1-2 በዕብራውያን አስተሳሰብና ሐረጎች የተሞላ ነው። በተደጋጋሚ የብሉይ ኪዳንን ዐቢይ ሐሳብና ነገረ መለኮት ያስተጋባል (በተለይ መሳ 13፥2-7፤ 1ሳሙ 1-3፤ ዘፍ 18፥11 ጋር ያነ)። ስለዚህም በዕብራዊ መቼት የተጠመቀ ታሪካዊ ግሪክ-ወ-ሮም አቀራረብ አለን። ሉቃስ በዚህ ትረካ በጥንቃቄና በጥበብ የገጸ ባሕርያቱን ባሕል አንጸባርቋል።

ከዚህም በተጨማሪ አንድ ሰው ከዓይን ምስክር ብቻ ሊጠብቅ የሚችላቸው ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ (ለምሳሌ ያህል መልአኩ ከዕጣን መሠዊያው በስተ ቀኝ ቆሞ መታየቱ፣ ቁ 11)። አጫጭርና ማራኪ የሆኑት ትረካዎቹ የሚያሳስቡን ሉቃስ ከዓይን ምስክሮች ያገኘውን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ እያቀረበ እንደ ነበረ ነው። (ከ1፥1-4 ጋር ያነ)። ምንም እንኳ ሉቃስ ጠንቃቃ ታሪክ ጸሐፊ ቢሆንም እዚህ ላይ እያቀረበ ያለው ግን ያለፈውን የሚመለከት አይደለም። እዚህ ላይ ሉቃስ ለኢየሱስ የሕይወት ታሪክ መሠረት የሚሆን ነገርን እያስቀመጠ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ትንቢታዊ በሆነ መልኩ የወደፊቱን ያመለክታሉ። በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ምን ሊገጥመን እንደሚችል ከወዲሁ መናገር እንድንችል ይረዱናል።



አር. ኢ. ብራውን፣ (*The Birth of the Messiah*) በተሰኘ መጽሐፋቸው በዚህ ክፍልና በዳንኤል 9-10 መካከል ተጻራሪ ወደሆኑ አንዳንድ ነጥቦች ትኩረታችንን ይስባሉ። ለምሳሌ፣ (1) ሁለቱም በራእይ መልአክን ማየታቸውን ይናገራሉ። (2) መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መልአኩ ገብርኤል መገለጥ የምናነበው በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ብቻ ነው። (1፥10-11 እና ዳን 9፥20-21)። (3) ገብርኤል የተገለጠው ለጭንቀት ጸሎት መልስ በመሆን ነበር። (1፥13 እና ዳን 9፥20)። (4) መልአኩን ከማየታቸው የተነሣ ዳንኤልም ሆነ ዘካርያስ ዲዳ ሆነዋል (1፥20-22 እና ዳን 10፥15)።

**§ 4**
**የዮሐንስ መወለድ ለዘካርያስ መገለጥ**
**(ሉቃ 1፥5-25)**

5ይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን፣ ከአብያ የክህነት
ምድብ የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱ
ኤልሳቤጥም ከአሮን ነገድ ነበረች። 6ሁለቱም የጌታን
ትእዛዝና ሥርዐት ሁሉ ጠብቀው ያለ ነቀፋ የሚኖሩ
በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ፤ 7ይሁን እንጂ ኤልሳቤጥ
መካን በመሆኗ ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜ
የገፉ ነበሩ።

ታላቁ ሄሮድስ ብልጥ ፖለቲካኛ፣ በቤተ ሰብ ሕይወቱ ያልተሳካለት፣ ሕንፃዎችን ማስገንባት የሚወድና ኃይለኛ የፍቅር ስሜት ያለው ነበር። የራሳቸውን ውስጣዊ ሕዝባዊ ዐመፅ መፍታት ከቃታቸው በኋላ የአይሁድ ንጉሥ እንዲሆን በሮም የተሾመ ነበር። ከ37 ዓ.ቅ.ክ እስከ 4 ዓ.ቅ.ክ ድረስ ገዝቷል።

በዚያን ዘመን እያንዳንዳቸው 900 የሚሆኑ ካህናትን የያዙና ሙሉ በሙሉ 21,600 የሚሆኑ (Josephus *Against Apion*, 2.108 - በአጠቃላይ 20,000 እንደ ነበሩ ገምቷል) ካህናትን ያካተቱ ሃያ አራት የካህናት ምድቦች ነበሩ። እያንዳንዱ ምድብ በየስድስት ወሩ አንድ ስምንት ያገለግላል። በሰንበት ቀን ከ24 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው በምድቦቹ ውስጥ ያሉ ሰዎች በሙሉ ያገለግላሉ። በሌሎቹ ሰድስት

ቀናት ግን በዕጣ የሚመረጡ 50 ወይም ያንን የሚያህሉ ያገለግላሉ። ፋሲካን፣ በዓለ ሃምሳንና የዳስ በዓልን በመሳሰሉ ታላላቅ በዓሎች ሃያ አራቱም ምድቦች ውስጥ ያሉት በሙሉ ያገለግላገሉ። በቀረው ጊዜ ግን በይሁዳ እዚህና እዚያ በተበታተኑ ቤቶቻቸው ውስጥ ይኖራሉ። ዘካርያስ ካህን ብቻ ሳይሆን የካህንን ልጅ ያገባ ነበር፤ ይህም ዕጥፍ ክብር ነበር። የንጽሕናና የእውነተኛ መንፈሳዊነት አርአያ በመሆን የኖሩ ደስ የሚሉ አረጋውያን ነበሩ።

የሚያሳዝነው ግን፣ ይኖሩ የነበሩት የመካንነት «መርገም» ውስጥ ነበሩ። በዚያ ዘመን ልጆች ከእግዚአብሔር የሚሰጡ በረከቶች እንደሆኑ ይታሰብ ነበር (ዘፀ 23፥26፤ ዘዳ 7፥14) የዚህ ተቃራኒ የሆነው መካንነት ደግሞ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ መርገም ይቈጠር ነበር (ኢዮ 15፥34)። የአንዲት ሴት መካንነት ሲወገድ ከእግዚአብሔር በረከትን እንደ ተቀበለች ሲታሰብ ተቃራኒው ከሆነ ደግሞ እንደ መርገም ነበር የሚታሰበው (1ሳሙ 2፥5፤ ኢሳ 54፥1፤ ገላ 4፥27 )።

መካንነት መርገም የሆነበት ምክንያት ልጅ የሌላት ሴት ባልዋ ከሞተ በኋላ የሚረዳትና የሚንከባከበት ሰው ስለማይኖር ነበር (ኢዮ 24፥21)። ከዚህም በላይ የሌሎች ሴቶች ማላገጫና መጠቋቈሚያ ትሆናለች (ዘፍ 11፥30፤ ሦራ፤ ዘፍ 25፥21፤ 29፥31፣ ራሔል)።

በዕድሜያቸው መግፋት ምክንያት ዘካርያስና ኤልሳቤጥ እግዚአብሔር የመካንነትን «መርገም» ያስወግድልናል የሚል ተስፋቸው በሙሉ ተሟጥጦ ነበር። ዕድሜአቸው ገፍቶ እንደ ነበር ሉቃስ አጠንክሮ ይናገራል። ከቀን ወደ ቀንም እርጅና እየተጫጫናቸው መጣ። እዚህ ላይም የምንመለከተው አሳዛኝ የሆነውን የአይሁድ ባልና ሚስት የመካንነት ምስል ነው። ልጅ እንደሚወልዱ ብርቱ ተስፋ ነበራቸው። በዕድሜ እየገፉ ሲሄዱ ግን ከወደብ ርቃ በዓይን እንደማትታይ መርከብ



ሕልምና ተስፋቸው ሁሉ እየበነነ ይሄድ ጀመር። አሁን ባለበት ሁኔታ ደግሞ ተስፋ ራሱ ከዘመናት በፊት የነበረ ትዝታ ያህል ደብዝዞአል።

ዕድሜያቸውን በተመለከተ የሚቀርቡ ግምቶች አንዱ የሌላውን ያህል ትክክል ሊሆን ቢችልም አንድ አይሁድ 60 ዓመት ካልሆነው በቀር እንዳረጀ አይቈጠርም ነበር። ስለዚህም 80 ዓመት ያህል ሊሆናቸው እንደሚችል መገመት ይቻላል ማለት ነው።

ሉቃ 1፥8-17

8አንድ ቀን ዘካርያስ በምድቡ ተራ፣
በእግዚአብሔር ፊት በክህነት በሚያገለግልበት ጊዜ፣
9በሥርዐተ ክህነቱ መሠረት ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ
ለማጠን በዕጣ ተመረጠ። 10ዕጣን በሚታጠንበትም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ሆኖ
ይጸልይ ነበር። 11የጌታም መልአክ ከዕጣን መሠዊያው በስተቀኝ ቆሞ ታየው።
12ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፤ በፍርሃትም ተዋጠ። 13መልአኩ ግን እንዲህ አለው፤
«ዘካርያስ ሆይ አትፍራ፤ ጸሎትህ ተሰምቶአል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ
ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። 14በእርሱ ተድላና ደስታ ታገኛለህ፤
ብዙዎችም እርሱ በመወለዱ ደስ ይላቸዋል፤ 15በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና የወይን
ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ በእናቱም ማሕፀን ሳለ በመንፈስ
ቅዱስ ይሞላል። 16ከእስራኤልም ሰዎች ብዙዎቹን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው
ይመልሳቸዋል 17የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው፣ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ
ይመልስ ዘንድ፣ ለጌታ የተገባ ሕዝብ ለማዘጋጀት በኤልያስ መንፈስና ኃይል በጌታ ፊት
ይሄዳል።

*[a]15 ወይም ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ*

አንድ ካህን ውሎውን የሚጀምረው ጠዋት በማለደ ተነሥቶ የመቅደሱን ግቢ በማጽዳት ነበር። የሚቀጥሉት ተግባሮች ለመደልደል ገና ከጥዋቱ ቢያንስ ሦስት ዕጣዎች ይጣላሉ፤ እነዚህም (1) መሠዊያው ላይ እሳት ማቀጣጠልና ጥዋት የሚቀርበውን መሥዋዕት ማቅረብ (2) በዕለቱ የሚያገለግለውን ካህን መሰየም፥ (3) በወርቃማው የሻማ መቅረዝ

ላይ ከሮችን ለማቀጣጠል ማዘጋጀት በቅድስት ውስጥ ዕጣን ለማጠን ማዘጋጀት:: ይህ ሦስተኛው ተግባር በዕለቱ ከሚከናወኑት እጅግ ቅዱሱ አገልግሎት ነበር:: ዕጣን ወደ ላይ የሚርገውን የቅዱሳን ጸሎት ይወክላል (መዝ 141÷2፤ ራእ 5÷8፤ 8÷3፣4):: በጌታ ፊት ያለ ማቋረጥ እንዲያጥን ጥዋትና ማታ ይቀርባል (ዘፀ 30÷8):: ይህ ከጸሎቱ ሰዓት (9 ሰዓት) ጋር ተያይዞ የሚቀርበው የቀትር መሥዋዕት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም:: ይህን ተግባር አንድ ካህን በሕይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ ብቻ እንዲፈጽም ይፈቀድለት ነበር:: ሁሉንም እንዲህ ዓይነት አገልግሎት ማከናወን የሚችል ከሆነ በእርግጥም ዕድለኛ ነበር::

ዕጣንን መሠዊያው ላይ በማጠን የተቀደሰ ተግባር እንዲያግዙት ዘካርያስ ሁለት ጓደኖቹን ወይም ዘመዶቹን ይመርጣል:: አንደኛው መሠዊያውን ባለፈው ምሽት የቀረበውን መሥዋዕት በማስቀገድ ያነፃል:: እያመለከ እያለ ከቅድስቱ ውስጥ የኋሊት እያፈገፈገ ይወጣል:: በዚህ ጊዜ ሁለተኛው ሰው ወደ ፊት ይመጣና ከመሠዊያው ላይ ፍም በመውሰድ የዕጣኑ መሠዊያ ውጫዊ ጫፍ ላይ ያደርጋል:: እርሱም ይሰግድና የኋሊት እየሄደ ከቅድስቱ በመውጣት የተቀደሰ ተግባሩን ይፈጽም ዘንድ ዘካርያስን ብቻውን ይተወዋል:: ውስጣዊው አደባባይ በስተ ደቡብ ካለው ከባለ ሰባት ቅርንጫፍ የሻማ መቅረዝ የሚወጣውን ደብዘዝ ያለ ብርሃን ያገኛል:: በስተ ሰሜን በኩል ገጸ ሕብስቱ፣ በስተ ምዕራብ በቅድስተ ቅዱሳኑ አጠገብ ደግሞ የዕጣን መሠዊያ ይገኛል::

ትክክለኛውን ጊዜ ጠብቆ ዕጣኑን መሠዊያው ላይ ያደርጋል:: መሥዋዕቱ ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር እየወጣ መሆኑን ሲያዩ ካህናቱና በስተውጭ ያሉት ሰዎች አክብሮት የተሞላበት አምልኮና ጸሎት ያቀርባሉ:: በዚህ የጸሎት ሰዓት ለመገኘት በመላ ከተማዋ የነበሩ ብዙ ሰዎች ወደ መቅደሱ ይመጡ ነበር:: በጣም ከዘገዩ እግዚአብሔር እንዳይቀስፋቸው ስለሚፈሩ አብዛኞቹ ካህናት ተግባራቸውን በፍጥነት ይፈጽማሉ:: ስለሆነም የዘካርያስ መዘግየት ያልተለመደ ነበር

ረዳቶቹ ትተውት ከሄዱ በኋላ ዘካርያስ ብቻውን ነበር ... ወይም ደግሞ እርሱ እንደዚያ ያስብ ነበር:: መልአኩ በድንገት ጉራ ብሎ አገኘው:: ሉቃስ እንደ ተጠቀመበት አገላለጽ ከሆነ ዘካርያስ በአገልግሎቱ ተመስጦ ስለ ነበር እርሱ ሳያውቀው መልአኩ በዕጣኑ መሠዊያና በወርቁ መቅረዝ መካከል ጥቂት ጊዜ ቆሞ ነበር:: በመጨረሻ ዘካርያስ መልአኩን ባየ ጊዜ በጣም ደነገጠ:: መላእክትን በተመለከቱ ሰዎች ዘንድ ይህ በጣም የተለመደ ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ ዘካርያስ ቅድስት ውስጥ ብቻውን እየገለገለ ስለ ነበር ለመፍራት ምክንያት ነበረው:: ገብርኤል ግን በተለመደው የመላእክት አነጋገር፣ «አትፍራ [መፍራትህን አቁም]» በማለት ሊያጽናናውና ሊያረጋጋው ሞከረ::

ከዚህም በማስከተል ገብርኤል፣ «ጸሎትህ ተሰምቶአል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች» አለው:: በእግዚአብሔር የተቀደሰ ስፍራ ሆኖ በሕይወት ዘመኑ አንዴ የሚያከናውነውን ሃይማኖታዊ ተግባር እያከናወነ ሳለ ሽማግሌው ዘካርያስ ልጅ ስለ መውለድ እየጸለየ አልነበረም:: እየጸለየ የነበረው ስለ እስራኤል መዳን ነበር:: በሀይራካነስና አሪስቶቡለስ (67-63 ዓ.ቅ.ክ) ዘመን ተካዶ የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት በ63 ዓ.ቅ.ክ ሮማውያን ኢየሩሳሌምን ድል ሲያደርጉ ተመልክቶአል:: በንጉሥነት የተሾመው ክፉው ኤዶማዊው ሄሮድስ በ37 ዓ.ቅ.ክ ንጉሥ ሆኖ ሲሾም ምስክር ነበር:: ጸሎቱ ለአገሩ ነበር በእርግጥ ሁኔታው የዳንኤልን ዓይነት ይመስላል (ዳን 9÷4-19)::

ይሁን እንጂ ሌላ አስገራሚ ነገር እየሆነ ነበር:: የሚወለደው ተራ ዓይነት ልጅ አልነበረም:: ስሙን፣ ዮሐንስ ማለትም «ጌታ ለጋስ ነው» ብለው ይሰይሙታል:: የተለየ የአመጋገብ ሥርዓት ይኖረዋል (ቁ 15):: ይህ ደግሞ የዕድሜ ልክ ናዝራዊ ስዕለት የተሳለ ሰው መግለጫ ነበር (ለምሳሌ ሳምሶን፣ መሳ 13÷4፣5፡ ሳሙኤል፣ 1ሳሙ 1÷11):: በወላጆቹ በጣም የሚወደድ ልጅ ይሆናል (ቁ 14):: ብዙ እስራኤላውያንን

ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል (ቁ 16-17)። በኤልያስ ኃይል የሚያገለግል፣ ሕዝቡን ለጌታ መምጣት የሚያዘጋጅ የእግዚአብሔር ሰው ይሆናል (ኢሳ 40÷3-5፤ ሚል 3÷1-5፤ 4÷5-6)። የኋላ ኋላ ለ400 ዓመት አቋርጦ የነበረው የነቢይ ድምፅ እንደ ገና መሰማት ይጀምራል።

> 18ዘከርያስም መልአኩን፣ «ይህን በምን አውቃለሁ?
> እኔ ሽማግሌ ነኝ፤ ሚስቴ በዕድሜ ገፍታለች አለው ሉቃ 1÷18-20
> 19መልአኩም መልሶ እንዲህ አለው» እኔ በእግዚአብሔር
> ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፤ ይህን እነግርህና ይህን የምሥራች አመጣልህ ዘንድ
> ተልኬአለሁ፤ 20እነሆ፣ ጊዜውን ጠብቆ የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፣ ድዳ
> ትሆናለህ፤ መናገርም አትችልም።»

ለዛካርያስ ይህንን ሁሉ መቀበል በጣም አስቸጋሪ ነበር። ጨርሶ ሊያምነው የሚችለው ነገር አልነበረም። ስለዚህም ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጠየቀ። ምንም እንኳ ይህን ማለቱ ለእኛ ምክንያታዊ ቢሆንም ለገብርኤል[1] ግን አሳማኝ ምክንያት አልነበረም። መቼም እርሱ በእግዚአብሔር ፊት የሚገኝ መልአክ ነው። ማንኛውንም ነገር ማወቅ የሚችልበት ቦታ ላይ ነበር። የመረጃ ምንጩም እጅግ አስተማማኝ ነበር።

ዘካርያስ ማረጋገጫ ፈልጎ ነበርና፣ ገብርኤል አንድ ማረጋገጫ ሰጠው። ዮሐንስ እስከሚወልድበት ጊዜ ድረስ ዲዳ ሲሆን ነው። አንጄርሰን እንደሚሉት ይህ የሚናገረው ዲዳ ስለ መሆን ሳይሆን

[1] የስሙ ትርጉም፣ «እግዚአብሔር ታላቅ ነው» ከተሰኘው ከገብርኤል ሌላ (ዳን 8÷16፤ 9÷21፤ ሉቃ 1÷19፣26) በስም የተጠቀሰ መልአክ ሚካኤል ብቻ ነው (ይሁዳ 9፤ ራእ 12÷7፤ ዳን 10÷13፣21፤ 12÷1)። በተጨማሪም ለመጨረሻ ጊዜ ገብርኤል የተናገረው (ዳን 9-10) የመሲሑን መምጣት በተመለከተ ነበር። ስለሆነም ዘካርያስ (እኛም ጭምር) ሲጠብቅ የነበረውን የመሲሑን መገለጥ መልእክት ይዞ ሲመጣ መቀበል ተገቢ ይሆናል።



መስማት አለመቻልን ነው።[2] እሳቸው እንደሚሉት «ይህ የተለየ ዓይነት ቅጣት ዘካርያስ ላይ ሊደርስ የቻለው የሰማውን ባለማመኑ ነበር፤ ... ስለዚህም የመልአኩ ቃል እስኪፈጸም ድረስ ከእንግዲህ ምንም ቃል አይሰማም» (ገጽ 23-24)። በሉቃስ 1÷62 እንደምንመለከተው ግን ዮሐንስ በተወለደ ጊዜ ጐረቤቶቹ ከዘካርያስ ጋር ሐሳብ ለመለዋወጥ በምልክት ቋንቋ ተጠቅመዋል። እርሱም በንግግር ሳይሆን በጽሑፍ ለጥያቄያቸው መልስ ሰጣቸው። ይህ ደግሞ መስማትም ሆነ መናገር እንደማይችል ይጠቁማል። ስለሆነም ምናልባት ማለት የምንችለው ጸጥታ [Stōpao] የሚለው ቃል መስማትና መናገር አለመቻልን ሁለቱንም እንደሚያካትት ነው።

የዘካርያስ ዲዳነት ምልክት እንዲሰጠው በመጠየቁ የመጣበት ቅጣት መሆኑን ምንባቡ የሚለው ባይኖርም እንደ ተግሣጽና እንደ ምልክትም የተደረገ ይመስላል። እንዲያውም በቂ መረጃ ከተሰጣቸው በኋላ ምልክት በሚጠይቁ ሰዎች ላይ ኢየሱስ ራሱ ነቀፋ ሰንዝሮ ነበር (ማቴ 12÷38-39፤ ሉቃ 11÷29፤ ዮሐ 6÷36)።

ይሁን እንጂ ጌዴዎን (መሳ 6÷3፣8-39) እና ሕዝቅያስ (2ነገ 28÷8) ምልክትን በጠየቁ ጊዜ ያለ ምንም ዓይነት ነቀፋ ወይም ቅጣት የጠየቁት ተሰጣቸው። አካዝ ምልክት እንዲጠይቅ ተነግሮት ነበር፤ እርሱ ግን አልፈለገም (ኢሳ 7÷11)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የምልክት ጥያቄና በአዲስ ኪዳን ይህን መሳይ ነቀፋ የመሰንዘሩ መሳይ ቅራኔ ለምን ተከሰተ? ሕዝቅያስም ሆነ አካዝ እየተነጋገሩ የነበረው ከሰብዓዊ ፍጡር መልእክተኛ ጋር ሲሆን

[2] J.G.Andersan, "A New Testament of Luke 1:20" *BT* 20 (Jan 1969):21-24። ይህ የመሠረቱት በሚከተሉት ማስረጃዎች ላይ ነው፣ (1) ሰብዓ ሊቃናት (LXX) ይህን ሐረግ የተጠቀሙበትን መንገድ። (2) *siapaŏ* የሚለው ሥርወ ቃል (3) *esĕ siopăn* = "በዝምታ ትኖራለህ" የሚለውን ቀጥተኛ ያልሆነ አቀራረብ። (4) ዓውደ ምንባቡ።

የአዲስ ኪዳኑ ምንባቦች ግን የሚናገሩት ስለ መለኮታዊ መልእክተኞች (ለምሳሌ ገብርኤልና ኢየሱስ) እንደ ነበር አስተውሉ:: በተጨማሪም ኢየሱስ በተአምራቱ ገብርኤል ደግሞ ቅድስት ውስጥ በመገኘቱ ለታማኝነታቸው በቂ መረጃ አቅርበው ነበር:: ስለሆነም ተጨማሪ ምልክት አስፈላጊ አልነበረም ማለት ነው::

[21]በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ዘካርያስ ከቤተ መቅደሱ
ሳይወጣ ስለምን እንደ ዘገየ በመገረም ይጠባበቅ ነበር ሉቃ 1፥21-25
[22]ከወጣ በኋላም ሊያናግራቸው አልቻለም፤ በምልክት
ከመጥቀስ በስተቀር መናገር ባለመቻሉ በቤተ መቅደስ ውስጥ ራእይ እንዳየ ተገነዘቡ::
[23]ዘካርያስም የአገልግሎቱ ወቅት በተፈጸመ ጊዜ ወደ ቤቱ ተመለሰ:: [24]ከዚህ በኋላ
ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች፤ አምስት ወራትም ራሷን ሰወረች፤ [25]እርሷም፤ «ጌታ
በምሕረቱ ነቀፌታዬን ከሰው መካከል ሊያስወግድልኝ ተመልክቶ በዚህ ጊዜ ይህን
አድርጎልኛል» አለች::

ከመቅደሱ ውጭ ለጸሎት መጥተው የነበሩ ሰዎች ጭሱ ወደ ሰማይ ሲወጣ እያዩ ነበር:: ጸሎታቸውን መጸለይ ጀመሩ:: ሆኖም ዘካርያስ ወደ ውጭ አለመውጣቱን ተገነዘቡ:: ብዙ በቆየ መጠን ብስጭታቸው እየጨመረ መጣ:: ምናልባትም በእግዚአብሔር ተቀሥፎ ይሆናል:: ድንገት ከዚህ በፊት አይተው በማያውቁት ሁኔታ ከውስጥ ወጣ:: አንዲትም ቃል መተንፈስ አልቻለም:: ይሁን እንጂ በመጨረሻ በተለይ ዓይነት መግባቢያ መንገድ የሆነውን ነገራቸው::

ሳምንቱ ካበቃ በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ወደ ነበረችበት ወደ ቤቱ ተመለሰ:: እንደ ተባለውም በእርግጥ ፀነሰች:: ይህ ደግሞ የተመልካችን ትኩረት የሚስብ ነበር:: ይህም ሁኔታ አምስት ወር ሙሉ ራሷን እንድትሰውር አድርጓታል:: በዚያ የተቀደሰ ብቸኝነት ውስጥ ሆና የእግዚአብሔር በረከት እስኪገለጥ ቆየች:: ከተሰወረችበት ስትወጣ ክብር



ለእግዚአብሔር ይሁን! በሐሜት ተሞልታ ነበር የመካንነትን መርገም እግዚአብሔር ከእርሷ አስወግዶአል::

**§ 5**
**ኢየሱስ እንደሚወለድ ለማርያም ተነገራት**
**(ሉቃ 1፡26-38)**

እዚህ ላይ እያየን ያለነው ታሪካዊ «የልደት ዓዋጅ» ነው:: ይሄ ዓይነቱ የአጻጻፍ መንገድ የዝነኛ ሰዎች የሕይወት ታሪክ በሚጻፍበት ወቅት የተለመደ ነበር (ለምሳሌ፣ ሱቶኒየስ፣ «አውግስጦስ» 94፣ in *Lives of the Twelve Caesars*) «እንዲህ ዓይነቱን ያልተለመደ ሕይወት እንዴት መግለጽ ይቻላል?» ለሚለው አስፈላጊ ጥያቄ መልስ ለመስጠት የታቀደ ነበር ታልቤርት እንደሚለው:: «ቀኖናውያን ወንጌሎች በሙሉ ከዚህ ዓይነት ችግር ጋር ይጋፈጣሉ:: ኢየሱስ የተለየ ዓይነት ሕይወት ሊኖረው የቻለው በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ በእርሱ ላይ በመውረዱ ነበር በማለት (ማር 1፥9-11) ማርቆስ መግለጫ ሰጥቷል:: ዮሐንስ የሰጠው ገለጻ ደግሞ ቅድመ ዓለም የነበረው ቃል ሥጋ ሆኖ በእኛ መካከል ኖረ የሚል ነበር (ዮሐ 1፥14)»[3] ማቴዎስና ሉቃስ ደግሞ ከድንግል ከመወለዱ የተነሣ ኢየሱስ የተለየ እንደ ሆነ ገልጠዋል::

[26]በስድስተኛው ወር፣ እግዚአብሔር መልአኩ
ሉቃ 1፥26-29 ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ናዝሬት ከተማ
ላከው፤ [27]የተላከበትም ከዳዊት ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል
ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር::
[28]መልአኩም እርሷ ወዳለችበት ገብቶ፣ «አንቺ የተወደድሽ ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤
ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ የተባረክሽ ነሽ አላት:: ማርያምም በንግግሩ እጅግ
በጣም ደንግጣ፣» ይህ ምን ዐይነት ሰላምታ ይሆን? እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር::

[3] CH. Talbert, "Luke 1:26-31, "*Int* 39 ( July 1985 ) 288-291.

ኤልሳቤጥ የስድስት ወር እርጉዝ እያለች[4] እግዚአብሔር ለሌላ ተልዕኮ ገብርኤልን ላከው:: በዚህ ጊዜ ግን የተላከው ወደ ኢየሩሳሌም ሳይሆን ወደ ናዝሬት ነበር:: በዚህ ጊዜ የተላከው ወደ አንዲት ወጣት ልጃገረድ ነበር እንጂ ወደ አንድ በዕድሜ የገፋ ሽማግሌ አልነበረም:: ሁለቱም መልእክቶች ልጅ ትወልዳላችሁ የሚሉ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ:: በሁለቱም ጊዜ የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል በመስጠት ገብርኤል ከፍርሃት አረጋጋቸው:: ማርያምም ሆነች ዘካርያስ የምሥራቹ እንዴት እውን ሊሆን እንደሚችል እየተገረሙ ቢሆኑም፣ ማርያም ግን መልአኩ በነገራት መልእክት ሙሉ እምነትና መሰጠት ነበራት::

አንዲት ልጃገረድ ዐሥራዎቹ ዓመታት ውስጥ ስትገባ ትታጫለች:: የወደፊቱ ሙሽሮች ወላጆች ሁኔታውን ያመቻቻሉ፣ እንዲያውም እጮኛን የሚመርጡ እነርሱ ነበሩ:: ምንም እንኳ አሁን ካለን ባሕል ጋር ባይጣጣምም ይህ እስከ ዛሬም ድረስ ውጤታማ የሆነ የጋብቻ መንገድ ነው:: ወጣቱ በቂ ገንዘብ ካጠራቀመ በኋላ ሽማግሌ ይመርጣል:: ሽማግሌውም ከወጣቱ ወላጆች ጋር ወደ ሙሽሪቷ ቤት ይሄዳል:: ወላጆቿ ይቀበሉና የሚጠጣ ነገር ያቀርቡላቸዋል:: እነርሱ ግን የጥሎሹ ዋጋ እስኪወሰንና ሙሽራዋን እንደሚሰጧቸው ቃል እስከሚገቡላቸው ድረስ አንጠጣም ይላሉ:: ከዚያ በኋላ የእርሷ ወላጆች በእነርሱም በኩል ሽማግሌ የሚሆን ሰው ይመርጡና ድርድሩ ይጀምራሉ:: ጉዳዩ እልባት ካገኘ በኋላ ምግብና መጠጥ ይቀርባል፣ ስምምነት ላይ በመደረሱም ሁሉም ደስታቸውን ይገልጣሉ:: ቀለበት የመሰዋወጡ ጊዜ ከሠርጉ በፊት ምናልባት አንድ ዓመት ሊቀድም ይችላል:: ይህ ውል ሕጋዊና እጅግ ጽኑ በመሆኑ የሚፈርሰው በሞት ወይም በፍቺ ብቻ ነው:: በሞት ከተለያት ሴትዮዋ መበለት ትሆናለች::

[4] ኢ.ደርሼም ትክክል ከሆኑ (1:135 ) የአቢያ ምድብ ያገለገለው በጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ላይ ነበር፡ ስለሆነም አሁን ያለነው ሚያዝያ ወር አካባቢ ነው ማለት ነው:: ስለሆነም ኢየሱስ የተወለደው (በታህሳስ መጨረሻ ወይም ጥር መግቢያ ላይ ይሆናል ማለት ነው::)



ይሁን እንጂ ሠርጉ እስከሚፈጸም ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድም:: በአይሁድ ትውፊት መሠረት ማርያም ምናልባት ዐሥራ አምስት ዓመቷ ሊሆን ይችላል::[5] ይህ ወቅት በማርያም ሕይወት ውስጥ አስደሳች ጊዜ ነበር ወጣት ናት፡ ድንግል ናት፣ በዚያ ላይ ታጭታለች:: ሁሉም ነገር ትክክለኛ መንገዱን ይዞ እየሄደ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ሳለች ገብርኤል ተገልጦ «እጅግ የተወደድሽ ሆይ፣ ሰላም ለአንቺ ይሁን» የሚል አስደናቂ ዓይነት ሰላምታ አቀረበ:: ከዚህም «ሰላም ለኪ ማርያም» (Ave Maria) የሚለው ታዋቂ አባባል ተገኘ:: ምንም እንኳ እነዚህ ቃላት ቢያስፈሯትም ትኩረቷን በመሳባቸው ለመልእክቱ ቀና ምላሽ እንድትሰጥ አድርገዋታል::

**ሉቃ 1፡30-33**

[30]መልአኩም እንዲህ አላት «ማርያም ሆይ፤
በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ:: [31]እነሆ
ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ
ትዪዋለሽ:: [32]እርሱ ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክ የአባቱን
የዳዊትን ዙፋን፣ ይሰጠዋል፣ [33]በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሣል፣
ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም::

ዘካርያስ ገብርኤልን ሲያይ ፈርቶ ነበር:: ማርያም በንግግሩ ተደናግራ ነበር መላእክት በሚገኙበት ወቅት የሚከሰተው ፍርሃት የተለመደ ጉዳይ ነው:: በተጨማሪም ምንጊዜም መላእክት፣ «አትፍራ ወይም አትፍሪ» በማለት ይናገራሉ:: (ዘፍ 15፡1፡ 26፥24፡ ዳን 10፥19፡ ማቴ 28፡5፡ ሉቃ 1፥13፣30፡ 2፥10፡ ሐሥ 18፥9፡ ራእ 1፥17):: ብዙውን ጊዜ መላእክት ፍርድን ወይም ጥፋትን እንደሚያመጡ ይታወቃል፡

D.Robinsan, "The Incredible Announcement," *His* 35 (Dec1974): 2-4 ጋር ያነ:: እርሳቸው እንደሚሉት፣ "ዮሴፍ ሽማግሌ ሰው ነበር የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም "ዮሴፍ 18 ዓመት ሊሆነው እንደሚችል ይናገራሉ::

በዚህን ጊዜ ግን እንዲህ አልነበረም። ማርያም ሐሜት ማድረግ እንጂ መፍራት አልነበራባትም። ልጅ ትወልዳለች ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለች።

«ኢየሱስ» የሚለው የተወሰደው «ኢያሱ» ከሚለው የዕብራይስጥ ስም ሲሆን ትርጉሙ፣ «እግዚአብሔር ያድናል» ማለት ነው። ጠላቶቻቸውን ድል በማድረግ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራ በመሆኑ ኢያሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። «ክርስቶስ» የተሰኘው የኢየሱስ መጨረሻ ስም ሳይሆን ሥልጣኑን የሚያመለክት እንደሆነም መገንዘብ ይኖርብናል። «ክርስቶስ» የሚለው የግሪክ ቃል፣ «መሲሕ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል አቻ ትርጉም ነው። የሁለቱም ትርጉም፣ «የተቀባ» ማለት ነው። ሌሎቹ የኢየሱስ ስሞችና ማዕረጎች የሰው ልጅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ እግዚአብሔር፣ ጌታ፣ ቃል፣ አገልጋይ፣ አዳኝ፣ የእግዚአብሔር በግ፣ ሊቀ ካህን፣ አማላጅ፣ የኋለኛው አዳም፣ ነቢይ፣ ካህን፣ ንጉሥ የተሰኙት ናቸው።

ከብሉይ ኪዳን ትንቢት አንጻር ገብርኤል ኢየሱስን የገለጸበት መንገድ የሚያስደንቅ ነበር «ልዑል» ለእግዚአሔር የሚሰጥ እጅግ ከፍ ያለ መጠሪያ ነው። ስለሆነም ኢየሱስ የራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል ማለት ነው። በጣም የሚገርመው፣ ኢየሱስ «የልዑል እግዚአብሔር ልጅ» ተብሎ የተጠራው ጌርጌሴኖን በሚባል ስፍራ አጋንንት በነበሩበት ሰው ብቻ መሆኑ ነው (ማር 5÷7፡ ሉቃ 8÷28)። ከዚያም ይልቅ በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ ኢየሱስ እኛም የልዑል ልጆች መሆን እንደምንችል መናገሩ ነበር (ሉቃ 6÷35)። በኢየሱስ ደም በኩል የልጅነትን መንፈስ ተቀብለናል (ዮሐ 1÷12፡ ሮሜ 8÷14-17፡ ዮሐ 3÷1-2)።

«የዳዊት ዙፋን» የአይሁድ መንግሥትን ንጉሣዊ የቤተሰብ የዘር ሐረግ ያመለክታል። ዳዊት የእግዚአብሔር ሕዝብ ንጉሥ ዓይነተኛ ምሳሌ ሆኗል። 2ኛ ሳሙኤል 7÷16 (1ዜና 17÷11-15 ጋር ያን) ይህን ተስፋ ቃል ያቀርባል፡ «ቤትህና መንግሥትህ በፊቴ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡ ዙፋንህም እንደዚሁ የጸና ይሆናል»። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ራሱ፡ «አንድ እንኳ በዳዊት ዙፋን የሚቀመጥ የማይኖረው» በማለት በተናገረለት በኢኮንያን ዘመን ከወራሾቹ አንዱ ከመንግሥቱ የዘር ሐረግ ወጥቶአል። ከኢየሱስ የዘር ሐረግ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው ከዳዊት እንጂ ከኢኮንያን የዘር ሐረግ ያልነበረው ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ በሆነ ጊዜ ሁለቱም ተስፋዎች ተፈጽመዋል።

ማርያም ከቅድሳት መጻሕፍትን የምታወቅ ነበረች። ባቀረበችው፡ «ውዳሴ» ቢያንስ ሠላሳ ቃላትን ወይም ሐረጎችን ከብሉይ ኪዳን ተጠቅማለች። ስለ ዳዊት ዙፋን የተነገረው ነገር ከድንግል ስለሚወለደውና ለዘላለም በዳዊት ዙፋን ላይ ስለሚነግሠው ልጅ የሚያመለክተውን ኢሳይያስ 7÷14 ላይ ያለውን ክፍለ እንድታስብ ሳያደርጋት አለቀረም። እነዚህ መሲሐዊ ትንቢቶች ስለ ልጅዋ ማንነት ተጨማሪ ዕውቀት እንዲኖራት አስተዋዕዖ ሳያደርጉ አይቀሩም።

የዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባት የሆነው ያዕቆብ የመላው አይሁድ ሕዝብም አባት እንደሆነ ይታሰብ ስለ ነበር፡ «የያዕቆብ ቤት» የሚለው ጠቅላላ አይሁድን የሚወክል ነው። ብዙውን ጊዜ በትንቢት ጽሑፎች በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል (ኢሳ 2÷5-6፡ 8÷17፡ 10÷20፡ 14÷1፡ 29÷22፡ 46÷3፡ 48÷1፡ 58÷1፡ ኤር 2÷4፡ 5÷20፡ ሕዝ 20÷5፡ አሞ 3÷13፡ 9÷8፡ አብድ 1÷17-18፡ ሚክ 2÷7፡ 3÷9)።

[34]ማርያምም መልአኩን፦ «እኔ ወንድ ስለማላውቅ
ሉቃ 1÷34-38 ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለችው። [35]መልአኩም መለሶ
እንዲህ አላት፦ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤
የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱስ ሕፃን የእግዚአብሔር ልጅ
ይባላል። [36]እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ መካን

የተባለችውም ስድስተኛ ወሯን ይዛለች:: 37ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና::» 38ማርያምም፣ «እነሆ እኔ የጌታ ባርያ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች::» ከዚያም መልአኩ ተለይቶአት ሄደ::

*[u]35 ወይም የሚወለደው ሕፃን ቅዱስ ይባላል::*

ብዙዎች ድንግል የመውለዷን ታምራት መቀበል ይከብዳቸዋል::[6] እርግጥ ነው «ፓርቴኖስ» (*Parthenos*) የተሰኘው የግሪክ ቃልና «አልማ» (*alma*) የተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል፣ ሁለቱም «ወጣት ሴት» ተብለው ሊተረጐሙ ይችላሉ::[7] ይሁን እንጂ ማርያም «ወንድ ስለማላውቅ» በማለት ስለ ተናገረች ዐውዱ የሚያመለክተው «ድንግል» የሚለውን ቃል መሆን አለበት:: ማቴዎስና ሉቃስ የሚናገሩትን ለማመን ፈቃደኞች ነን? ወይም ደግሞ በሌላ መንገድ ለማስቀመጥ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ የመፍጠር ተአምር ማድረግ ይችላልን? የማቴዎስና የሉቃስ አንባቢዎች በቅድመ ሳይንስ ዘመን ይኖሩ ስለነበር እንዲህ ያሉ ታሪኮችን ሊያምኑ ይችሉ ነበር ማለቱ ምንም አይጠቅምም:: ሕፃናት ከየት እንደሚመጡ ለማወቅ የግድ «ዘመናዊ» መሆን የለባችሁም::[8] ሐኪም እንደ መሆኑ መጠን ሉቃስም ይህንን በቀላሉ ሊቀበለው አይችልም ነበር:: ማቴዎስና ሉቃስ የአረማውያን ድርሳነ - አምልኮ የመሰለ ሐሳብ ቀድተው እያቀረቡ ነበር ማለትም አይቻልም ምክንያቱም በእነዚህ

[6] R.E. Brown, "The Problem of Virginal Conception" *TS* 33 (1972): 3-34 ጋር ያነ:: ስለ ድንግል መውለድ ጠበቅ ያለ መከራከሪያ ለማግኘት፣ የዴቪድ ማክሊዮድ፣ "The Virginal Conception of Our Lord in Mt 1:18-25," *EmJ* 8 (1999): 3-42 እና የኤስ ሌዊስ ጆንሰን, "The Genesis of Jesus" *BS* 122 (1965) :331-332 ይመ::

[7] C.H. Dodd, "New Testament Translation Problems I," *BT* 27/3 (July 1976): 301-305 ያነ:: ይሁን እንጂ ይህን J. Carmignac, "The Meaning of *parthenos* in Lk 1:27 - A Reply to C.H. Dodd," *BT* 28 (1977): 327-330 ጋር ያነ::

[8] D.M.Smith, "Luke 1:26-38," *Int* 29 (Oct 1975): 411-417, በጣም ርቀው በመሄድ ደናግላን እንደማይፀንሱና እንደማይወልዱ የጥንት ሰዎች ባያውቁም በዚህ ዘመን ያለነው እናውቃለን ብለዋል:: ይህን መሳዩ በዘመን አቈጣጠር የተመሠረተ ትምክህት የተሳሳተ ነው::



ድርሳናተ - አምልኮ ከድንግል መፀነስ ጋር በእውነት የሚነፃፀሩ ሃሳቦች አልነበሩም::[9] ከዚህም በተረፈ በአይሁድ ታሪክ ከድንግል የተወለደ መሲሕ ከዚያ በፊት ተሰምቶ አያውቅም ነበር ይህም ኢየሱስን እንደ አረማውያን ከፊል ወይም ትንሽ አምላክ እንዲታሰብ የማድረግ ችግር ውስጥ ሊከተው እንደሚችል ሉቃስ ይገነዘባል:: ከዚህም በተጨማሪ ባሕላዊው ታሪክ ቀጥሎ ባለው መንገድ መሄድ ነበረበት:- (1) በአይሁድነት ማዕቀፍ ውስጥ ኢየሱስን ከሰውነት ወደ መለኮትነት ከፍ ማድረግ:: (2) ከአይሁዳዊ ግለ ሰብነት ወደ ግሪኮች ከፊል አምላክነት እንዲለወጥ ማድረግ:: (3) ማቴዎስና ሉቃስ በየግላቸው ይህን ተመሳስሎት እንደ ታሪክ ይወስዱታል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በሃምሳ ዓመት ውስጥ ይሆናል:: ይህ አስተሳሰብ የድንግል መወለድ እም ሀበ አልቦ (*ex nihilo*) የሆነ ጉዳይ መሆኑን እንድናምን ይጠይቃል:: ይህ ደግሞ ከምሑራዊው ፓርቲኖጄኔሲስ (parthenogenesis - ማለትም ያለ ወንዶ ዘር ልጅ መውለድ) ከሚሉት ጋር ተመሳሳይ ነው![10] ያም ሆነ ይህ ጉዳዩ እግዚአብሔር በኤደን አትክልት ስፍራ ሕይወት መፍጠር ከቻለ ማሕፀንም ውስጥ ሕይወትን መፍጠር ይችላል ወደሚል መደመምደሚያ እንመጣለን::

ማርያም ስለ ፀነሰችበት ትክክለኛ ሁኔታ አንድ ሰው አክብሮት የጐደለው ስሜታዊ መገረም ሊያድርበት ይችላል:: ሐቁ ግን እንዴት ሊሆን እንደቻለ አለማወቃችን ነው:: ቁጥር 35 መንፈስ ቅዱስ በማርያም

[9] J.Nolland, *Luke*, in Word Biblical Commentary Vol 35a ( Dallas: Word, 1989), pp. 57-58 ላይ «ስለ መለኮታዊ አባትነት ከሚናገሩት የአረማውያን ድርሳናተ አምልኮ በማንኛቸውም የዚህን በድንግልና የመፀነስን ልምድ ፅንሰ ሃሳብ አናገኝም:: እነርሱ የሚንቀሳቀሱት ጨርሶ ልዩ በሆነ የሃሳብ ዓለም ውስጥ ነው:: በመጨረሻ እጅግ ትክክል የሆነው መግለጫ ኢየሱስ የተወለደው ያለ ሰብዓዊ አባት ጣልቃ ገብነት ነው::» በተጨማሪ H.D. Buckwalter, "The Virgin Birth of Jesus Christ: A Union of Theology and History" *EJ* 13 (1995): 3-14.

[10] N.T. Wright, "God's Way of Acting," *ChrCen* 115/35 (1998): 1215-1217.

ላይ «ይመጣል» ይላል። በብሉይ ኪዳን ይህ ሐረግ ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል መቀበልን እንጂ ከእርሱ ጋር አካላዊ ግንኙነት ማድረግን አያመለክትም። ምንም እንኳ የአረማውያን ድርሳነ አምልኮ አማልክትና ሰዎች በአንድ ላይ ይኖሩ እንደ ነበር ቢናገርም በዚህ ምንባብ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስና በማርያም መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተደርጐአል እንድንል የሚያስችለን ምንም ዓይነት ሰዋስዋዊ፣ ዐውዳዊ ወይም ነገረ መለኮታዊ መሠረት የለንም።

ለማርያም ይህንን ሁሉ ማመን በጣም አስቸጋሪና አስፈሪ ነበር። አስቸጋሪ የሆነበት ምክንያት ድንግል መሆንዋን በማወቋ ነበር። ከዚህም የተነሣ ገብርኤል ምልክት ሰጣት። መካንና በዕድሜ ገፍታ የነበረችው ዘመዷ ኤልሳቤጥ አርግዛ ነበር። እንግዲህ እግዚአብሔር ለኤልሳቤጥ ቃል የገባላትን ማድረግ ከቻለ፣ ለማርያምም እንዲሁ ታማኝ ይሆናል። ምንም እንኳ የማርያምና የኤልሳቤጥ ዝምድና እንዴት እንደ ነበር ባናውቅም፣ ኤልሳቤጥ አያቷ መሆን እስክትችል ድረስ ከማርያም ይልቅ እጅግ አንጋፋ እንደ ነበረች ግን እናውቃለን።

ይህን ለማመን የሚያስቸግር ብቻ ሳይሆን የሚያስፈራም ጭምር ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ አመንዝራ ሴት በድንጋይ መወገር ነበረባት (ዘሌ 20÷10)። ምናልባት ባትገደል እንኳ፣ የምትወደውን ሰው በእርግጥ ማጣቷ የማይቀር ነበር (ገብርኤል ጣልቃ ባይገባ ኖሮ በእርግጥም ልታጣው ትችል ነበር)። ከዚህም በላይ እንዲህ ዓይነቷን «የተደፈረች» ሴት ማን ይፈልጋታል። ከዚህም ባሻገር በዚያ ባሕል ያላገባች ሴት ሥራ የማግኘት ዕድል እንኳ አይኖራትም ነበር። የምትኖረው በጣም ትንሽ በሆነች መንደር ውስጥ ስለ ነበር የሆነውን ነገር ሰው ሁሉ በቀላሉ ማወቅ ይችላል። አሉባልታው እያደገ መጥቶ በማርያም ላይ ክፉ ወሬ ለማስወራት ረጅም ጊዜ አይፈጅም ነበር። ይህች ውድና ንጽሕት ልጃገረድ «በአጉል አኗኗር» ሰውን ሁሉ ታደናግጥ ነበር።



ምንም እንኳ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ብታውቅም በእግዚአብሔር የነበራት እምነት ማርያምን፣ «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» እንድትል አድርጓታል። ግሪኩ optative ማለትም በጉ ምኞትን በሚገልጥ ያልተለመደ ዓይነት ግሥ ይጠቀማል። እዚህ ላይ ልናስወግዳቸው የሚገቡን ሁለት ጽንፎች ይኖራሉ። አንደኛው ማርያምን ማምለክ ነው (በካቶሊኮች ዘንድ በአብዛኛው የተለመደው «ማርዮላትሪ» - Mariolatry)። እርግጥ ነው ታላቅ ናት ሆኖም እንስት አምላክ አይደለችም። የሳንቲሙ ሌላው ገጽታ ደግሞ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ ያለው ይህችን ከአእምሮ በላይ የሆነች ሴት ችላ የማለት ዝንባሌ ነው። ከአብርሃም፣ ከሣራ እና ከዘካርያስ ጋር ሲወዳደር የማርያም እምነት ከሁሉም ይበልጥ ደምቆ ያበራል። ብዙ ችግር ሊደርስባት ይችል ነበር። ያም ቢሆን ያለ ማወላወል የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቷ እንዲፈጸም ራሷን ሰጠች።

**§ 6**
**ማርያም ኤልሳቤጥን ጥየቃ መሄዷ**
**(ሉቃ 1÷39-45)**

39 ማርያምም በዚያው ሰሞን በፍጥነት ተነሥታ
ወደ ደጋው አገር ወደ አንድ የይሁዳ ከተማ ሄደች፤
40 ወደ ዘካርያስ ቤትም ገብታ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ
አቀረበች። 41 ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች
ጊዜ፣ ፅንሱ በማሕፀኗ ውስጥ ዘለለ፤ ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች፤
42 ድምፅዋን ከፍ አድርጋ እንዲህ አለች፤ «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ
የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። 43 ለመሆኑ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እኔ
ማን ነኝ? 44 እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ ጆሮዬ እንደ ገባ፣ በማሕፀኔ ያለው ፅንስ በደስታ
ዘሎአልና። 45 ጌታ ይፈጸማል ብሎ የነገራትን ያመነች እርሷ የተባረከች ናት»።

ከናዝሬት ወደ ኮረብታማው አገር ወደ ይሁዳ ለመሄድ ለማርያም ከ3-4 ቀን ሊወስድባት ይችላል። የተጠቀሰ መንደር ወይም ስፍር ስለሌለ ርቀቱን ከ50-70 ማይሎች ማጥበብ ይቻላል። ገብርኤል ያንን ዓዋጅ በነገራት ምናልባት በአንድ ወይም በሁለት ቀናት ውስጥ የነበራትን ጥቂት አስፈላጊ ነገሮች በመያዝ ለጉዞ ተነሣች (ወላጆቿ ምን ሊያስቡ

እንደሚችሉ ሊደንቀን ይችላል):: ወደ ኤልሳቤጥ ቤት በደረሰች ጊዜ ገና ሳምንት እንኳ ያልሞላት እርጉዝ ነበረች::

በመጀመሪያዎቹ የእርግዝናዋ ወሮች ለማርያም ከሰው ዓይን ለመሸሸግ ተገቢው ስፍራ ይሄ ነበር:: ስለ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ኤልሳቤጥ ማረጋጋጫ ታቀርብላታለች:: የኤልሳቤጥን ያህል የሚያምናትና ከጐኗ በመቆም የሚደግፋት ሰው ሊኖር አይችልም:: ማርያም በመጨረሻ የእርግዝናዋ ወራት በተለይም በይሁዳ የበጋው ሙቀት ሲበረታ ቤትን በማፅዳትና ምግብ በማብሰል ማርያም ኤልሳቤጥን ታግዛታለች::

ኤልሳቤጥ የማርያምን ሰላምታ ስትሰማ ወዲያውኑ ማሕፀኗ ውስጥ የነበረው ዮሐንስ ዘለለ:: ሉቃስ የተጠቀመበት ቃል «ቦረቀ» ተብሎ መተርጐም ይቻላል:: ብዙ ጊዜ ደግሞ ከመሲሑ ጋር በተያያዘ በደስታ ከመዝለል ጋር ይያያዛል (ለምሳሌ ሚልክ 4÷2):: «ሕፃን» በግሪክ ብሬፎስ (brephos) የሚያመለክተው ገና ያልተወለደ ልጅን ነው:: ይህ አንድ መለኮታዊ ማረጋገጫ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል:: በመጀመሪያ፣ ማርያም ለኤልሳቤጥ ሰላምታ ስታቀርብ ፅንሱ ዘለለ ማርያም ከተናገረችው ይልቅ የዮሐንስ መዝለል ማሕፀኗ ውስጥ ስለ ነበረው ምስጢር ተናገረ:: ሁለተኛ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ባይሆን ኖሮ ገና ማሕፀን ውስጥ የነበረው ዮሐንስ መቼ በደስታ መዝለል እንዳለበት እንዴት ማወቅ ይችል ነበር?

ከ60 ዓመት በላይ ስለ ሆናት ይህች እርጉዝ ሴት በአሥራዎቹ ውስጥ ስላለችው ዘመዷ በደስታ ስትጮህ ማርገዝ የሰፈሩ ሰው ምን እያለ ይሆን? እንደ ልጇ ሁሉ ኤልሳቤጥ የሰጠችውን ምላሽ ትንቢታዊ ነበር:: በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ[11] ማርያምና ኢየሱስ ሁለቱም የተባረኩ

[11] እዚህ ላይ በጣም የታወቁት ሁለቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ተፈጽመዋል፡ (1) ስለ ኢየሱስ ያለውን እውነት መመስከር (ዮሐ 15÷26)፡ (2) ሐሳባችንን መምራትና በእኛ አማካይነት ስለ ኢየሱስ መናገር (ማቴ 10÷19-20)::



የእግዚአብሔር መሣሪያዎች መሆናቸውን ተናገረች:: «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» የሚለው አይሁዳውያን «አንቺ ከሴቶች ሁሉ መካከል እጅግ የተባረክሽ ነሽ» የሚሉት የአባባል ዓይነት ነው:: በሌላ አነጋገር ከእግዚአብሔር ከተቀበለችው በረከተ አንጻር ማርያም፣ «ንግሥት» ናት:: በማርያም ማኅፀን ውስጥ በማደግ ላይ የነበረው ያ ትንሽ ሕይወት፣ ያ ሽል - እሹ እኮ ለኤልሳቤጥ ጌታዋ ነበር! ኤልሳቤጥ በማኅፀን የነበረውን የክርስቶስን ጌትነት ተገነዘበች::

**§ 7**
**ውዳሴ**
**(ሉቃ 1÷46-56)**

በይዘቱም ሆነ በአጻጻፍ ስልቱ ይህ ቅኔ ከሌሎች ሁለት ቅኔዎች ጋር ሊነጻጸር ይችላል፡ በ2÷13-14 ካለው «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም» *Gloria in Excelsis* እና 2÷18-32 ካለው *Nunc Dimittis* ጋር በምንባቡ ውስጥ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንደደረገው ንግግር ያገለግላሉ ይህም ማለት በምንባብ ውስጥ ለተጠቀሱት ቁልፍ ተዋንያን የራሳቸው የሆነ ድምፅ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ:: እነዚህ ሦስቱም ቅኔዎች ወይም አባባሎች የብሉይ ኪዳን የተውጣጡ ምርጥ ጥቅሶች ናቸው::

46 ማርያምም እንዲህ አለች፤
«ነፍሴ» ጌታን ከፍ ከፍ ታደርገዋለች፤
47 መንፈሴም በመድኀኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ትለኛለች፤
48 እርሱ የባሪያውን መዋረድ ተመልክቶአልና::
ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ በፅዕት ይሉኛል
49 ኃያል የሆነው እርሱ ታላቅ ነገር አድርጐልኛልና፤
ስሙም ቅዱስ ነው፤
50 ምሕረቱም ለሚፈሩት ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል::
51 በክንዱ ብርቱ ሥራ ሠርቶአል
በልባቸው ሐሳብ የሚታበዩትን በትኖአቸዋል፤
52 ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአቸዋል፤

ትሑታንን ግን ከፍ ከፍ አድርጐአቸዋል፤
53 የተራቡትን በበጐ ነገር አጥግቦአቸዋል፤
ሀብታሞችን ግን ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል፤
54 ምሕረቱን በማስታወስ ባሪያውን
እስራኤልን ረድቶአል
55 ይህም ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፣
ለአብርሃምና ለዘሩ ያለውን
ለዘላለም ለመጠበቅ ነው።
56 ማርያምም ሦስት ወር ያህል ኤልሳቤጥ ዘንድ ከቆየች በኋላ ወደ ቤቷ
ተመለሰች።

ምንም እንኳ ማርያም የገጠር ልጃገረድ ብትሆንም ቅኔዋ ቀላል አልነበረም።[12] የተጻፈው ደረጃውን በጠበቀ የግሪክ ቋንቋ ቢሆንም እንደ ማንኛውም የብሉይ ኪዳን ዕብራይስጥ ቅኔ ሁሉ በጥንቃቄና በጥበብ ተቀምሯል። እንደ ይዘቱ ሁሉ ጥልቅ ነገረ መለኮታዊ ግንዛቤውም አስደናቂ ነው። በርካታ የብሉይ ኪዳን ሐረጐችንና ሐሳቦችን ያጣቅሳል።[13] ምንም እንኳ ሐና የነበረችበት ሁኔታ ከማርያም ይልቅ ከኤልሳቤጥ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፥ በአብዛኛው መልኩ የሐናን ጸሎት ይመስላል (2ሳሙ 2፥1-10)[14] ይህ ቅኔ ማግኒፊካት (Magnificat) ይባላል፤ ይህም የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም «ማክበር፤ ከፍ ከፍ ማድረግ» (Magnify) ማለት ነው።

---

[12] R.C. Tannehill, "The Magnificat as Poem," *JBL* 93 (1974): 263-275, ላይ ይህን የማርያምን ቅኔ ጥልቀት ይተነትናል።

[13] J. Koontz, "Mary's Magnificat," *BibSac* 116 (Oct 1959): 336-349, እያንዳንዱ የቅኔው ስንኝ የሚያነሳቸው የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎችን አሰፍረዋል (ገጽ 339) ይህም ከሦስቱን የዕብራይስጥ የብሉይ ኪዳን ምድቦች የተወሰዱ ማጣቀሻዎችንም ይጨምራል።

[14] እንዲያውም አንዳንድ የጥንት ቅጆች ይህ ቅኔ የኤልሳቤጥ መሆኑን ያመለክታሉ (S. Benko, "The Magnificat: A History of the Controversy," *JBL* 86 (1967): 263-275 ይመ)።

እርግጥ ነው እንዴት ተጠብቆ እንደ ኖረ የተነገረን ነገር የለም። ማርያም ስትናገር እየሰማች ኤልሳቤጥ ጻፈችው ቢባል እንኳ የሚመስል አይደለም። ከማርያም አንደበት የወጡትን ቃላት ሁለቱም ሴቶች ቃል በቃል ማስታወስ ቻሉ ማለትም ይከብዳል። እንዲህ ያለ ጥልቀትና ግልጽነት ያለው ቅኔ በድንገት የፈለቀ የምስጋና መግለጫ ነው ማለትም እንዲሁ የሚመስል ጉዳይ አይሆንም። እንዲህ ሲባል ግን ሉቃስ ጻፈው ለማለት እንዲያውም አስተካክሎ ጻፈው (ምንም እንኳ ከአረማይክ ወደ ግሪክ የተረጐመው እርሱ ሊሆን ቢችልም) የሚለውንም ሃሳብ በፍጹም አያመለክትም። ከዚህ የተሻሉ ገለጻዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል ማርያም ይህን ቅኔ የተቀኘችሁ ወደ ይሁዳ እየመጣች እያለ ወይም ደግሞ ሦስት ወር ሙሉ ኤልሳቤጥ ቤት በቆየችበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳ ምንባቡ መንፈስ ቅዱስ ማርያም ላይ ወርዶ ይህን ቅኔ እንድትቀኝ አደረጋት ባይልም፣ ማሕፀንዋ ውስጥ ሕይወት ለመፍጠር መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይል በእርስዋ ላይ ወርዶ ነበር። ስለዚህም ይህን ቅኔ እንድታቀናብር ራሱ መንፈስ ቅዱስ አስተዋፅዖ አድርጐ ነበር ማለት ይቻላል።

ቅኔው ሦስት ክፍሎች አሉት፡- የእግዚአብሔር ምገስ (1) በማርያም ላይ፤ 46-46፣ (2) በትሑታን ላይ፣ 50-53፣ (3) በእስራኤል ላይ፣ 54-55። በብሉይ ኪዳንና በእርሷ በራሷ ሕይወት ለነበረው የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ማርያም አጽንዖት ሰጥታለች። ከአንደበቷ በወጡት ቃላት ባሕርይዋ ተንፀባርቋል። ብሉይ ኪዳንን በሚገባ የምታውቅ፣ በእምነትና ለእግዚአብሔር የመስጠት ሕይወት የነበራት ትሑት ዕብራዊ ልጃገረድ ናት።

እዚህ ላይ የእሷ ትኩረት እግዚአብሔር የሰዎችን ሁኔታ በሚለወጥበት መንገድ ላይ ነው። እግዚአብሔር ትሑት የነበረችውን ሴት በማንሣት ከሴቶች ሁሉ መካከል ያከብራታል (ቁ 48-50)። (በቁጥር 48 ላይ ማርያም መቼም እየተቃረበ የመጣውን የመውለድዋን

አስፈለጊነት ተረድታለች):: እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያዋርዳቸዋል (ቁ 51-52):: የተራቡትን ያጠግባል (ቁ 53):: እስራኤልን እንደ ሕዝብ ከፍ ከፍ ያደርጋል (ቁ 54-55 ):: የዚህ ዝማሬ ዐቢይ ሐሳብ ሁኔታዎችን እንዳልነበሩ ማድረግ ነው (ማቴ 19÷30-20÷16፤ ያዕ 4÷10፤ 1ጴጥ 5÷6፤ ፊልጵ 2÷5-11 ጋር ያነ)::

ከቁጥር 51-55 ያለው እግዚአብሔር «አደረገ» ስለ ተባለው ሁኔታ የሚገልጽ ነው:: ሆኖም ይህ እግዚአብሔር ምናልባት ሁሌም እንደዚያ እያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ቅኔያዊ ገለጻ ሊሆን ይችላል::[15] እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን የሚበትነው እንዴት ነው (51)? አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ «በልባቸው ሐሳብ» ይላል:: በሌላ አነጋገር በጠማማ አስተሳሰባቸው አማካይነት እግዚአብሔር ሊበትናቸው ይችላል::

ዮሐንስ እስኪወለድ ድርስ ማርያም እዚያው መቆየቷ አልተነገረንም:: ይሁን እንጂ በእነዚህ ሦስት ወራት እዚያው መሆኗ (ቁ 56) የመውለጃው ጊዜ ሲደርስ እዚያው እንደምትሆን ያሳያል::[16] ዮሐንስ እስኪለወድ ድረስ እዚያው ከቆየች በኋላ ወደ አገሯ መመለሷ በጣም ተገቢ ይመስላል:: በዚህ ጊዜ ማርያም ወደ ናዝሬት ትመለሳለች:: ከዚያም ዮሴፍ የገጠማትን ሁኔታ ይረዳል (ማቴ 1÷18-25)::

**§ 8ሀ**
**የዮሐንስ መወለድ**
**(ሉቃ 1÷57-66 )**

57የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ቀን ደረሰ፤ ወንድ
ልጅም ወለደች:: 58ጐረቤቶቿና ዘመዶቿም ጌታ ታላቅ
ምሕረት እንዳደረገላት ሰሙ፤ የደስታዋም ተካፋዮች ሆኑ
59በስምንተኛውም ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ፤ በአባቱም
ስም ዘካርያስ ሊሉት ፈለጉ፤ 60እናቱ ግን፣ «አይሆንም
ዮሐንስ መባል አለበት አለች» 61እነርሱም፣ «ከዘመዶችሽ በዚህ ስም» የተጠራ ማንም
የለም አሏት::

[15] የአጻጻፉ ስልት "gnomic aorist" ይባላል::

[16] እየተከተልን ያለነው የጨረቃን እንጂ የፀሐይን ቀን አቈጣጠር አለመሆኑን መረዳት ይገባል:: በመሆኑም የአይሁዳዊቷ ሴት እርግዝና ጊዜ 10 እንጂ 9 ወር አልነበረም:: ይሁን እንጂ በምንባቡ መሠረት (ሉቃ 1÷26 እና 56) የተገለጸው ዘጠኝ ወር ብቻ ቢሆንም እንኳ ዮሐንስ ሲወለድ ማርያም እዚያው ነበረች ቢባል አግባብነት ይኖረዋል::



የዮሐንስ መወለድ የከተማው ወሬ ሆነ:: መልአክ ካበሰረው ካበስራትና ከዘካርያስ ዲዳ መሆን የተነሣ ታላቅ መገረም ነበረ:: ለኤልሳቤጥም ደኅንነት ጥንቃቄ እንዲደረግ ከፍተኛ ትኵረት ነበር:: እንዲያውም በእርሷ ዕድሜ ያለች ሴት መውለድ እንኳ አልነበረባትም:: ሆኖም እናትና ልጅ ጤናሞች ሆነው በመገኘታቸው ጐረቤቶቿ ሁሉ የደስታቸው ተካፋይ ሆኑ ::

እንደ ማንኛውም አይሁዳዊ ልጅ በስምንተኛው ቀን በሕጉ መሠረት እንዲገረዝ ኤልሳቤጥ አመጣችው:: ከእግዚአብሔር ጋር ላደረገው ኪዳን ምልክት እንዲሆን የግርዘት ትእዛዝ መጀመሪያ የተሰጠው ለአብርሃም ነበር (ዘፍ 17÷9-14):: ሰንበት ማክበርን ጨምሮ ግርዘት የእግዚአብሔር ሕዝብ መለያ ምልክት ሆኖ ነበር::

በስምንተኛው ቀን አንዳንድ የጐረቤት ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁን ትኵር ብለው ተመለከቱትና ስም ሊያወጡለት ፈልገው ያልሆኑ ስሞች መጥራት ጀመሩ:: እንደ አባቱ እሱም ዘካርያስ መባል እንዳለበት አስበው ነበር:: ለነገሩ በአይሁድ ባሕል ይህን መሳይ አጠራር የተለመደ ነበር:: ኤልሳቤጥ ግን በድንገት የተጀመረው ጥሪት እንዲቆም አደረገች:: ገብርኤል የሰጣት መመሪያ ዮሐንስ ብላ እንድትጠራው ነበር:: ስለሆነም ላለፉት ስምንት ቀናት ዮሐንስ እያለች ስትጠራው ነበር::

**ሉቃ 1÷62-66**

62አባቱንም ምን ስም ሊያወጣለት እንደሚፈልግ
በምልክት ጠየቁት 63እርሱም መጻፊያ ሰሌዳ እንዲሰጡት
ለምኖ፣ «ስሙ ዮሐንስ ነው» ብሎ ጻፈ፤ ሁሉም በነገሩ
ተደነቁ:: 64ወዲያውም አፉ ተከፈተ፣ አንደበቱ ተፈታ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ
መናገር ጀመረ:: 65ጐረቤቶቹም ሁሉ በፍርሃት ተሞሉ፤ ይህም ሁሉ ነገር በደጋማው

የይሁዳ ምድር ሁሉ ተወራ:: 66ይህንም የሰሙ ሁሉ፣ «ይህ ሕፃን ምን ሊሆን ይሆን?» እያሉ ነገሩን በልባቸው ያዙ፤ የጌታ እጅ በእርግጥ ከእርሱ ጋር ነበርና::

ጐረቤቶቿ ኤልሳቤጥ የነገረቻቸውን መስማት አልፈለጉም:: ስለዚህም አለመግባባቱን ለመፍታት በማሰብ ወደ ባሏ ዘወር አሉ:: በዚህ ጊዜ ዘካርያስ መናገር ብቻ ሳይሆን መስማትም እንደ ተሳነው ነበር ያለው:: (የቃሉ ተገቢ አጠቃቀም ይሄ ነው፤ ሉቃ 7÷22 ጋር ያነ) ስለዚህም ሐሳባቸውን የገለጡለት፣ «በምልክት ቋንቋ» ነበር:: የመጻፊያ ሰሌዳ እንዲሰጡት ጠየቀ:: ምናልባትም ይህ በላዩ የሚጻፍበትና እንደገና መጠቀም በሚያስችል ሰም የተሸፈነ ጣውላ ሊሆን ይችላል:: «ስሙ ዮሐንስ ነው» ብሎ በመጻፍ አለመግባባቱን አስወገደ:: የጻፈው «ስሙ ዮሐንስ ነው» የሚል ነበር:: በጣም አስደንጋጭ ነበር! ከአንድ ሌላው እየተቀበለ ወሬው አገሩን ሁሉ አዳረሰ:: በዚህ ለዓላማ በተወለደ ሕፃን ላይ የእግዚአብሔር እጅ እንደነበር ለሁሉም ግልጽ ነበር ይህ ሁሉ የት ሊያመራ እንደሚችል እየጠየቁ ነበር::

§ 8ለ
የዘካርያስ መዝሙር
(ሉቃ 1÷67-79)

67የሕፃኑም አባት ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ
ተሞልቶ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ፤
68የእስራኤል አምላክ ጌታ ይመስገን፤
መጥቶ ሕዝቡን ተቤዥቶአልና::
69በባሪያው በዳዊት ቤት፣ የድነት ቀንድ[ሀ] አስነሥቶልናል፤
70ይህም ጥንት በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ እንደ ተናገረው፤
71ማዳኑም ከጠላቶቻችንና ከተፃራሪዎቻችን ሁሉ እጅ ነው፤
72ይህንም ያደረገው ለአባቶቻችን ምሕረቱን ለማሳየት፣ ቅዱስ
ኪዳኑን ለማስታወስ፤
73ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን መሐላ ለማሰብ፤
74ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶ፣ ያለ ፍርሃት እንድናገለግለው፣
75በዘመናችንም ሁሉ በቅድስናና በጻድቅ በፊቱ ሲያቀመን ነው::



76ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፤ የልዑል ነብይ ትባላለህ የጌታን
መንገድ ለማዘጋጀት በፊቱ ትሄዳለህና፤
77የኃጢአታቸውን ስርየት ከማግኘታቸው የተነሣ፣ ለሕዝቡ
የመዳንን ዕውቀት ትሰጥ ዘንድ፣
78ከአምላካችን በጐ ምሕረት የተነሣ፣
የንጋት ፀሐይ ከሰማይ ወጣችልን፤
79ይኸውም በጨለማ ለሚኖሩት፣ በሞት ጥላ ውስጥም ላሉት እንዲያበራና
እግሮቻችንም ወደ ሰላም መንገድ እንዲመራ ነው::

*[ሀ] 69 ቀንድ በዚህ ስፍራ ብርታትን ያሳያል::*

የዘካርያስ አንደበት ተፈታ:: በጥንቶቹ ነቢያት ላይ እንደ ወረደ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእርሱም ላይ ወረደ::

«ቡራኬ» በመባል የሚታወቀው ይህ ንግግር ቅኔያዊም ትንቢታዊም ነው:: እንደ ማርያም ቅኔ (Magnificat) ሁሉ በዕብራዊና ብሉይ ኪዳናዊ አባባሎች የበለፀገ ነው:: በኢየሱስና በዮሐንስ መምጣት የተፈጸሙ በርካታ ትንቢትዊ ጉዳዩችን ይዘረዝራል:-

ሀ. የእስራኤል ድነት፣ ቁ 68::
ለ. ከዳዊት ቤት የድነት ቀንድ፣ ቁ 69::
ሐ. ከጠላቶቻችን መዳን፣ ቁ 71::
መ. ለአባቶቻችን የገባውን ተስፋ መፈጸሙ፣ ቁ 72-74::
ሠ. ያለ ምንም ፍርሃት እግዚአብሔርን ማገልገል መቻላችን፣ ቁ 74-75::
ረ. ለመሲሑ መንገድ የሚያዘጋጅ መምጣቱ፣ ቁ76::
ሰ. የኀጢአት ስርየት እንደሚገኝ፣ ቁ 77
ሸ. የእግዚአብሔር ብርሃን በጨለማ ለሚኖሩት ማብራቱ፣ ቁ 78-79::

ቅኔው የሚጀምረው መቤዠትን በማወጅ ነው። ቃል በቃል የቃሉ ትርጉም «ዋጋ» ወይም «ቤዛ» ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ቃሉ በዋነኛነት የሚናገረው ስለ እስራኤል ከግብፅ መውጣት ነበር በዚህ ወቅት ደግሞ አይሁድ በተመሳሳይ መንገድ ከሮም ቀንበር «መፈታትን» ተስፋ እያደረጉ ነበር (ሉቃ 24÷21)። እኛ ካለንበት አንጻር ስንመለከተው ኢየሱስ የሚሰጠው ቤዛነት በወታደራዊ ዘመቻ ሳይሆን በመስቀሉ በኩል እንደ ሆነ እንገነዘባለን። ኢየሱስ ተቀባይነት ያለውን ብቸኛ ክፍያ ለኃጢአታቹ ከፈለ ይኸውም የገዛ ደሙን ነው። መስቀሉ ቤዛነት ነው።

ቁጥር 69 ላይ ይህ መሲሕ፣ «የድነታችን ቀንድ» መሆኑ ተገልጾአል። በቅርብ ምሥራቅ የቀንድ እንስሳት ከነበራቸው ብርታት የተነሣ ቀንድ የኀይል ተምሳሌት ሆኗል። በአዲስ ኪዳን «ቀንድ» የሚለው ቃል ከዚህ ሌላ ጥቅም ላይ የዋለው በዮሐንስ ራእይ ላይ ብቻ ነው። በዚያ መጽሐፍ ሦስት ነገሮችን በማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ... ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር በግና የእግዚአብሔር መሠዊያን፣ በአንፃሩ ደግሞ ዘንዶውንና አውሬውን። ድነታችንን በተመለከተ በሁለት ታላላቅ ሆኖም በማይመጣጠኑ ኀይላት መካከል ለድነታችን ብርቱ ውጊያ እየተካሄደ ነው። በሁለቱም በኩል ያለው የኀይል አሰላለፍ ማሰብ ከምንችለው በላይ ቢሆንም ውጊያው ለእግዚአብሔር በእርግጥ እንደ ትልቅ ተግዳሮት እንዳልነበረ የዮሐንስ ራእይ ግልጽ አድርጎታል።

ይህ ትንቢታዊ ቃል ከሚልኪያስ ዘመን አንሥቶ የነበረውን የ400 ዓመት የዝምታ ጊዜ እንዲያበቃ አድርጓል። በቁጥር 71 ላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ በመዝሙር 106÷10 ማግኘት ይቻላል። ይሁን እንጂ ጽንሰ ሐሳቡ በእያንዳንድ የትንቢት መጽሐፍ ውስጥ አለ ማለት ይቻላል። በዘመኑ እንደ ነበሩ ሰዎች ሁሉ በዚህ ወቅት በዘካርያስ አእምሮ የነበረው የፖለቲካዊ ድነት እንደነበረ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ቀሪው የወንጌል ክፍል ፍጻሜው መንፈሳዊ ባሕርይ እንዳለው ግልጽ አድርጎታል።



ልጁ ዮሐንስ የመሲሑን መምጣት እንደሚያውጅ ዘካርያስ እንደሚገባ ያውቅ ነበር (ቁ 76)። ሌላው ቀርቶ የዮሐንስ የኀጢያትን ስርየት እንዴት እንደሚያበሥር እንኳ ገልጾታል (ቁ 77)። ለመሲሑ መንገድ የሚያዘጋጀው ነቢይ የሥራ ድርሻ ምን እንደሚሆን በብሉይ ኪዳን ስለ ተሰጠው መግለጫ በሚገባ ያውቅ ነበር (ሚል 3÷1፡ 4÷5፡ ኢሳ 40÷3፡ ማቴ 3÷3 ጋር ያነ)።

ዮሐንስ መንገድን ያዘጋጃል፡ መሲሑ ደግሞ ከበስተኋላው «ይነሣል»። በብሉይ ኪዳን «ይነሣል» የተሰኘው አባባል፣ በተለይ ከ«ቅርንጫፍ» ጋር ተያያዞ ከተነገረ፣ ጠንከራ መሲሐዊ አንድምታ እንደሚኖረው፣ እዚህም ላይ መገንዘብ ይገባል። የመሲሑ መምጣት ጨለማን ከሚያስወግደው የፀሐይ መውጣት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል (ማቴ 4÷16፤ ሉቃ 2÷32፡ ዮሐ 1÷4-9፡ 3÷20-21፡ 8÷12 ጋር ያነ)። ለእግዚአብሔር ሕዝብ የመዳን ተስፋ የሚያበሥር አዲስ ቀን እየወጣ ነው።

### § 8ሐ የዮሐንስ ማደግና (ሉቃ 1÷80)

[80]ሕፃኑም ልደገ፤ በመንፈስም ጠነከረ፤ ለእስራኤልም ሕዝብ በደፋ እስከ ታየበት ቀን ድረስ በበረሐ ኖረ።

ይህ ጥቅስ የ30 ዓመት ወቅት ይሸፍናል። «እስከ ታየበት» የሚለው «እስከ ተሾመበት»፣ «እስከ ተጠቆመበት» ወይም «ተመርቆ እስከ ወጣበት» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ስለ አንድ ባለሥልጣንን በይፋ መታጨት በይፋ የሚነገር ዓዋጅን ለማመልከትም ይሄው አባባል ይጠቀሳል። በሌላ አነጋጋር ይህ የሚያመለክተው የዮሐንስን፣ «ተመርቆ» መውጣት ነው።

ዮሐንስ የኩምራን ማኅበረ ሰብ አባል እንደሆነ በአንዳንዶች ዘንድ ይታመናል። ወላጆቹ በዕድሜ የገፉ በመሆናቸው ገና ልጅ እያለ ሞተው ከሆነ ይህ ማኅበረ ሰብ እንደ ማደጐ ልጅ አሳድጎት ሊሆን ይችላል።

ለነገሩ በድንግላዊነት ለሚኖር ማኅበረ ሰብ በዚህ መልክ ራሱን ለማሳደግ ይሄኛው እርምጃ መልካም መንገድ ነው:: ይሁን እንጂ እንደ ኩምራኖቹ ሁሉ ዮሐንስም የብትውና ሕይወት እየመራ በበረሐ ከመኖሩ ውጪ ይህን አመለካከት የሚደግፍ አንድም ታሪካዊ ማስረጃ እንደ ሌላ ግን መገንዘብ ይኖርብናል::

# ምድብ ሦስት
# ቀደምት የኢየሱስ ክርስቶስ ዓመታት

**§9**
**ዮሴፍ ስለ ኢየሱስ ተማረ**
**(ማቴ 1÷18-25)**

የማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያ ምዕራፍ ኢየሱስ ማነው? ለሚለው አንድ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ታስቦ የተጻፈ ነው:: ለጥያቄው ሁለት መልሶች አሉት:: የመጀመሪያውን መልስ የምናገኘውከቁጥር 1-17 ባለው ክፍል ነው:: በአሳዳጊ አባቱ በዮሴፍ በኩል የዳዊት ልጅ ነው::[1] እንዲያውም ከኢየሱስ ሌላ «የዳዊት ልጅ» ተብሎ የተጠራ ዮሴፍ ብቻ ነው (ቁ 20):: ሁለተኛው መልስ ደግሞ ፍጹም ንጹሕ በሆነ መንገድ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ቍ 18-25)፤ በመሆኑም አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ተብሎ ይሰየማል (ኢሳ 8፡10 ጋር ያነ):: ሁለቱም መልሶች ልደት ከሚለው ጋር በተያያዘ መልኩ የቀረቡ ናቸው (ቁ 1፣18):: የሚገልጡትም «ተሠግዎ» የሚለውን ሃሳብ ነው:: እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ ለብሶ በሰዎች መካከል ኖረ (ማቴ 17፡17፤ 18፡20፤ 26፡29፤ 28፡20 ጋር ያነ)::

**ማቴ 1÷ 18-21**

የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ እንዲህ ነው፤
እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ
ፀንሳ ተገኘች:: እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ስለ ነበርና
ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት ስላልፈለገ በስውር ሊተዋት
ወሰነ [20]በዚህ ሐሳብ ላይ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም
ተገለጠለት፤ እንዲህም አለው «የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ
እጮኛህን ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ፤

[1] ይህ ለማቴዎስ ቁልፍ መሪ ሐሳብ ነው:: ከማርቆስ ጋር ሲነጻጸር 10 እጥፍ ይልቅ ከሉቃስ ደግሞ 4 እጥፍ በዚህ ቃል ሲጠቀም ዮሐንስ ግን ይህንኑ ቃል አንድ [illegible] እንኳ አልተጠቀመም::

የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና። [21]ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም «ኢየሱስ» ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና።

*"21 ኢየሱስ በግሪክ ቋንቋ «ኢያሱ» የሚለው አቻ ሲሆን ትርጉሙም «እግዚአብሔር ያድናል» ማለት ነው።*

ይህ ሁኔታ የተፈጸመው ማርያም ሦስት ወር በኤልሳቤጥ ቤት ካሳለፈች በኋላ ሊሆን ይችላል። ስፊውን የአይሁዳውያንን ቀሚስ ለብሳ እንኳ በአሁኑ ጊዜ ማርያም መፀነሷ እየታየ ነው። አንድ ነገር መደረግ ነበረበት። በማርያም መፀነስ ምንም ድርሻ እንደሌለው ዮሴፍ አንድ ዓይነት መግለጫ ማድረግ ነበረበት።

ዮሴፍ ሁለት አማራጮች ነበሩት። እርሷን በማስወገር ሊያበቃ የሚችል አሳፋሪ ምርመራ በአደባባዩ እንዲካሄድባት ማድረግ ይችላል። አለዚያም በሁለት ምስክሮች ፊት የፍቺ ጽሑፍ ሰጥቶ ማሰናበት ይችላል። በማኅበረሰቡ ዓይን እንደ ረከሰች ትቆጠራለች።

ዮሴፍ ሁለተኛውን አማራጭ በመውሰድ ማርያምን በሰው ፊት እንዳታፍር ለማድረግ እርምጃ ሊወስድ ነበር። እርምጃው ትሑትና ምክንያታዊ ቢሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን እንዲህ አልነበረም። መልአክ በጉዳዩ በሕልም ጣልቃ ገባ። ምንም እንኳ ይህ ለአንዳንዶቻችን እንግዳ ቢሆንም በአይሁድ ዘንድ ግን ሕልሞችን ከእግዚአብሔር የመጡ መልእክቶች አድርጐ መቀበል የተለመደ ነበር። ብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በሕልም የተናገራቸው ዐሥራ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ነበሩ (ዘፍ 20፡3፤ 28፡12፤ 31፡10፤ 31፡24፤ 37፡5፤ 40፡9፤ 40፡16፤ 41፡1፤ መሳ 7፡13፤ 1ነገ 3፡5፤ ዳን 2፡3፤ 7፡1)። በተጨማሪም ኢዩኤል 2፡28 ሕልሞች ከመሲሑ ዘመን ምልክቶች መከከል እንደሚሆኑ ይናገራል። ከዚህም ባሻገር በአዲስ ኪዳንም ውስጥ አምስት ሕልሞች የተመዘገቡ ሲሆን ሁሉም የሚገኙት በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ነው ከአምስቱም ሦስቱ የዮሴፍ ሕልሞች ናቸው (ማቴ 1፡20፤ 2፡12-13፤ 19፡22፤ 27፡19)። ሕልሙ ለዮሴፍ ሦስት ነገሮችን ...

ማርያም አልረከሰችም። የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነበር እንጂ በመሴሰኗ አልነበረም። ስለዚህ ሚስትህ አድርገህ ልትወስዳት ትችላለህ። በሁለተኛ ደረጃ ማርያም ወንድ ልጅ ትወልዳለች። «አሳዳጊ» አባት እንደ መሆንህ መጠን ስሙን «ኢየሱስ» ማለትም («እግዚአብሔር ያድናል») በማለት ትጠራዋለህ። በፖለስቲና ባሕል መሠረት «ኢየሱስ» ብሎ ስም ማውጣቱ አሳዳጊው መሆኑን ያመለክል። ኢየሱስን እንደ ልጁ እየተቀበለው ነው። ስለዚህም ኢየሱስ እንደ ሕገ ወጥ ልጅ ሊቈጠር አይችልም። በሦስተኛ ደረጃ ይህ ልጅ የተለየ ልጅ ይሆናል። እርሱ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል።»

ይህ ሐረግ ለክርስቲያን አንባቢ ጥልቀት ያለው «መንፈሳዊ» አንድምታ አለው። ለአይሁዳውያን ግን አንድምታው ይበልጥ ተግባራዊና ፖለቲካዊ ነው። የእስራኤል ኃጢአት ብዙውን ጊዜ ባዕዳን መንግሥታት በአገር አቀፍ ደረጃ ቅጣት እንዲፈጽሙባት ምክንያት ሆኖአል። በሮም አገዛዝ አይሁድ እየደረሰባቸው የነበረውም በትክክል ነበር። በዘመኑ በሕዝቡ እንደ ነበረው አስተሳሰብ ሁሉ ዮሴፍም በኃጢአታቸው ምክንያት ከደረሰባቸው ቅጣት አይሁድን ነጻ የሚያወጣ ፖለቲካዊ መሲሕ ይጠብቅ እንደ ነበረ ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ የዚህ ትንቢት እውነተኛ ትርጉም በጦር ኃይል ሳይሆን በቀራንዮ መስቀል ላይ ነበር የሚገኘው።

**ማቴ 1፥22-25**

[22]ጌታ በነቢዩ (በኢሳይያስ) እንዲህ ሲል የተናገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ፤ [23]እነሆ፤ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤" ትርጉሙም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው። [24]ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃ፤ ከዚያም የጌታ መልአክ እንዳዘዘው ማርያምን ወደ ቤቱ ወሰዳት [25]ይሁን እንጂ የበኩር ልጇን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ የተወለደውንም ሕፃን «ኢየሱስ» ብሎ ጠራው።

*"23 ኢሳይያስ 7፥14*

ትንቢቱ ከኢሳይያስ 7፥14 የተወሰደ ነው። በዚህ ጥቅስ ያለው «አልማ» (alma) የሚለው ቃል ድንግል ወይም ወጣት ሴት ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በ732 ዓ.ቅ.ክ. ትንቢቱ መጀመሪያ ሲፈጸም ቃሉ «ኮረዳ» የሚል ትርጉም ነበረው። እግዚአብሔር በግብፅና በአሦር አማካይነት በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ለአካዝ ምልክት ሰጠው (ኢሳ 7፡11-19)። አንዲት ኮረዳ ወይም ወጣት ሴት ልጅ ትወልዳለች። ከዚሁ ጋር በማያያዝ እግዚአብሔር «ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ሲችል ቅቤና ማር ይበላል። ነገር ግን ሕፃኑ ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ከመቻሉ በፊት የፈራሃቸው የሁለቱ ነገሥታት ምድር ባድማ ይሆናል» (ቁ 15-16) ብሎ ነገረው። ይህ በአካዝ ዘመን ጉልህ ትርጉም ነበረው። አንዳንዶች ይህ ሰው ሕዝቅያስ ወይም ከንጉሣዊ ዘርያዎች አንዱ ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ መላው የይሁዳን ልጆች የሚያመለክት ነው ይላሉ። ሆኖም ዐውዱን በተሻለ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ካየነው እየተናገረ ያለው ስለ ማኸር ሻላል ሃሽ - ባዝ ነው (ኢሳ 8፡3)። እነዚህ ሁሉ አመለካከቶች ይቅረቡ እንጂ አንዱም እንኳ የድንግልን መወለድ አስፈላጊነት በተመለከተ አይናገርም።

ከትንቢቱ ዐውደ ሐሳብ (ኢሳ 8፥17-18፤ 9፥1-2፣6-7) እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ከተሰጠው ትርጉም (የማቴ 1፥23 ስንመለከተው ትንቢቱ በዋነኛነት ፍጻሜውን ያገኘው በኢየሱስ መወለድ ነበር። በዚህ ቦታም ሆነ በሉቃስ ወንጌል እየተነጋገርን ያለነው ስለ አንዲት ድንግል ነው። ማርያም ማሕፀን ውስጥ ያለው ሕይወት ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ ከወንድ ጋር በተፈጸመ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመሆኑን ገብርኤል ለዮሴፍ ነግሮታል።

ከድንግል የሚወለደው ልጅ «አማኑኤል ... እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ተብሎ ይጠራል። የቃሉ ትርጉም አንድምታ ከፍጥረታት ሁሉ በላይ የሆነ አምላክ በሰዎች መካከል ይኖራል የሚል ነው።



እስራኤላውያን የዚህን ጥላ ወይም ምሳሌ ከቅድስተ ቅድሳኑ ተመልክተዋል። በዚያም እንኳ ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነበር፤ ለዚያውም ቢሆን በዓመት አንዴ ብቻ ነበር። አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ሙቀቱ በረድ በሚልበት ወቅት በአትክልቱ ስፍራ እንደ ተመላለሰም ተነግሮናል። ከዚያም በላይ «ሰብዓዊ ገጽታ ያለው»፣ የሰው ልጅ በሰማይ ደመና ይገለጣል ተብሎ ተጽፎአል (ዳን 7÷13)። ይሁን እንጂ በኢየሱስ አኗኗር በሥጋ የተገለጠው አምላክ በዚያ ዘመን የነበሩ አይሁድ ከሚያስቡት ሁሉ እጅግ የሚልቅ ነበር።

ዮሴፍ ከእንቅልፉ ሲነቃ እግዚአብሔር በሕልም እንደ ተናገረው ተረዳ። ግን ከመልአኩ የተቀበለውን መልእክት ከተራ ዓይነት ሕልም እንዴት ነበር ለይቶ ማወቅ የሚችለው? መልሱ በጣም ግልጽ ነው በምንም አላወቀም ደግሞም ማወቅ አይችልም በመጀመሪያው መቶ ዓመት በነበሩ አይሁዳውያን ዘንድ ሕልሞች መለኮታዊ መልእክቶችን እንደ ያዙ ማለትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ የማግኘት ምልክት እንደሆኑ አድርጎ የመውሰድ አጠቃላይ አመለካከት ነበር። በጣም የተለመዱ ከመሆናቸው የተነሣ ታልሙድ፣ (ቤር 55 ለ)፣ «አንድ ሰው ምንም ሕልም ሳያይ ወይም ሕልሙን አስታውሶ ለሚተረጉምት ሳይናገር ሰባት የእንቅልፍ ሌሊቶች ካሳለፈ ያንን ሰው የተረገመ በሉት» (በእግዚአብሔር ዘንድ የተረሳ) ይላል (ኤደርሼይም I:155) በመሆኑም ዮሴፍ ለሕልሙ በመታዘዝ ማርያምን እንደ ሚስቱ አድርጎ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነ።

ብዙ ዝርዝር ያሉት ሕጋዊ መተጫጨት ከተደረገ በኋላ የሚቀር ነገር ቢኖር የሠርጉ ሥርዓት ብቻ ነው። የጋብቻው ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ሙሽሪት ከባሏ ጋር ለመኖር ትሄዳለች። ምን ዓይነት ሥርዓት እንዳደረጉ አልተነገረንም። ይሁን እንጂ ከእርሱ ጋር እንድትኖር ዮሴፍ ማርያምን ወደ ቤቱ ካመጣት ጊዜ ጀምሮ እንደ ባልና ሚስት ነው

የሚቆጠሩት:: ኢየሱስ እስከሚወለድ ድረስ ግን ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አላደረገም:: ይህም የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጥፎ በመሆኑ ሳይሆን፣ የኢየሱስ ልደት የተለየና ቅዱስ እንደ ነበር ነው ማንም እንዳይክድ ለማድረግ::[2]

**§ 10**
**የኢየሱስ ልደት**
**(ሉቃ 2፥1-7)**

በዚያን ዘመን የዓለሙ ሕዝብ እንዲቆጠርና
እንዲመዘገብ ከአውጉስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ። 2 ይህም
ቄሬኔዎስ የሶሪያ ገዥ በነበረበት ጊዜ የተደረገ
የመጀመሪያው የሕዝብ ቆጠራ ነበር። 3 ስለዚህ እያንዳንዱ
ሰው ለመመዝገብ ወደየራሱ ከተማ ሄደ።

በዘመኑ የነበረው ቄሣር ጋይዮስ ኦክታቪየስ ሲሆን የተወለደው መስከረም 23 ቀን 63 ዓ.ቅ.ክ ነበር:: በማደጉ ልጅነት ያሳደገው ትልቁ አጎቱ ዩልየስ ቄሣር ሲሆን እርሱም መጋቢት 15 ቀን 44 ዓ.ቅ.ክ ተገድሎአል:: በዚያ ጊዜ የ19 ዓመት ወጣት ቢሆንም ብልጣ ብልጥ ፖለቲከኛ ነበር:: በግዛቱ ከነበሩ ሦስት እጅግ ታላላቅ ሰዎች አንዱ ሆነ:: መስከረም 2 ቀን 31 ዓ.ቅ.ክ በአክቲየም በተደረገው ጦርነት ማርክ አንቶኒን ካሸነፈ. በኋላ፣ ሌሎች ተቀናቃኞቹንም እንዲሁ ድል አድርጎአል:: «ንጉሥ» እንዲሁም «አምባገነን» የሚሉትን ሹመቶች (መጠሪያዎች) ባለመቀበሉ አፄ የመሆን ፍላጎት የለውም ተብሎ እንዲታሰብ አድርጎ ነበር:: በኋላ ግን በተጨባጭ መንገድ ንጉሥ ሆኖ ነበር:: ያደረገው የኋላ ኋላ መለኮታዊ መሆኑን የሚያመለክተው የቄሣርን መጠሪያ የወሰደው ኦክታቪየስ ነበር:: ይህም ቄሳር በ14 ዓ.ም እስከ ሞተበት ድረስ ገዝቶአል::

[2] ቊጥር 25 ስለ ማርያም ልጆች እንደሚናገረው ክፍል ሁሉ በሕይወት ዘመንዋ ሁሉ በድንግልና ነበረች የሚለውን አስተሳሰብ የሚቃወም ይመስላል:: ይህ አስተሳሰብ የመጣው *Protevangelium of James* ከተባለው የአዋልድ መጽሐፍ 14፥15-19 ሲሆን ልጅ ስትወልድ እንኳ የማርያም ድንግልና አልተገሠሠም እስከ ማለት ርቆ ይሄዳል::



በኋለኛው የንጉሥነት ዘመኑ በተሻለ ሁኔታ ግብር መሰብሰብ እንዲቻል በመላው የሮም መንግሥት የሕዝብ ቆጠራ እንዲጀመር አደረገ::[3] ይሁን እንጂ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ነገር ማድረግ አልቻለም ነበር:: ስለዚህም በተለያዩ አውራጃዎች ያሉት በተለያዩ ጊዜያት እንዲመዘገቡ አደረገ:: የሮም ግዛት በጣም ሰፊና ውጥንቅጥ ስለ ነበር የአመዘጋገቡ ስልት ከእያንዳንዱ የተለየ ሕዝብ፣ ወገንና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም መሆን ነበረበት::

አይሁድን በተመለከተ በነገድ፣ በጐሳና በቤተሰብ ይመዘገባሉ:: ይህንንም ለማድረግ ወደ ትውልድ ከተሞቻቸው መሄድ ነበረባቸው:: ምናልባትም የትውልዱ ዘር ሐረግ መዛግብቱ የሚገኙት እዚያ ሊሆን ይችላል:: ዮሴፍም ከዳዊት ዘር እንደ መሆኑ መጠን ወደ ቤተልሔም እንደሚሄድ ግልጽ ነው (1ሳሙ 16፥1፤ 17፥58 ጋር ያነ)::

በጣም የታወቀው ቄሬኔዎስ የሶርያ ገዢ በነበረበት ወቅት አድርጎት የነበረው ሕዝብ ቈጠራ የተካሄደው በ6 ዓ.ም. ነበር:: የሚታወሰውም ዓመፅ የተቀሰቀሰበት ጊዜ በመሆኑ ነው (ሐዋ 5፥3፤ Josephus, Ant. 18.26) ይህ ደግሞ ከኢየሱስ ልደት ዐሥር ዓመት ያህል ወደ ፊት ቀደም ይላል:: ታዲያ፣ ሉቃስ ዐሥር ዓመት ቀድሟል ማለት ነውን? ለዚህ ሁለት መፍትሔዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: የመጀመሪያው ቄሬኔዎስ ከ6-7 ዓ.ም. የሶሪያ ገዢ ከመሆኑ በፊት በሶሪያ (ከ8-4 ዓ.ቅ.ክ) ወታደራዊ መሪ ነበር:: ስለዚህም እዚህ ላይ ሉቃስ እየተናገረ ያለው ቄሬኔዎስ ወታደራዊ መሪ እያለ ስለ ተደረገው የመጀመሪያው ሕዝብ ቆጠራ እንጂ ገዢ ከሆነ በኋላ ስለ ተደረገው ሁለተኛ ቆጠራ አልነበረም:: ሁለተኛውና በጣም ቀላሉ መፍትሔ protė የሚለውን ቃል «መጀመሪያ» ብሎ ከመተርጐም ይልቅ «በፊት» ብሎ መተርጐም ነው:: ስለሆነም ሉቃስ የሚለው በቄሬኔዎስ አገዛዝ ዘመን ስለ ተደረገው ታዋቂ ሕዝብ ቆጠራ ሳይሆን ከዚያ በፊት ስለ ተደረገው ነበር ማለት ነው::[4]

[3] Tacitus, *Ann*. 1.11; Dio Cassiu 53.30.2 ጋር ያነ::

[4] B. Pearson, "The Lucan Census Revisited," *CBQ* 61/1 (1999): 262-282;

በሐዋርያት ሥራ 5÷37 ስለ ጠቀሰው ሉቃስ በ6 ዓ.ም. ስለተደረገው የሕዝብ ቆጠራ በሚገባ ይገነዘባል:: በተጨማሪም ቄሬኔዎስ መጠቀሱ ለትረካው አስፈላጊ አይደለም ማለት ይቻላል:: ስለዚህም ሉቃስ ራሱ አጠራጣሪ ወይም መሠረት የሌለውን መረጃ እንዳያካትት ጥንቃቄ ስለሚያደርግ ትክክለኛውን ነገር ነግሮናል ብለን እንወስዳለን:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ የቄሬኔዎስ ስም መጠቀሱ በፊተኛውና በኋላኛው የሕዝብ ቆጠራ ለመለየት የተደረገ ይመስላል:: ሉቃስ ካደረገው ተአማኒነት ያለው ጥናት አንጻር እኛ የማናውቀውን ታሪክ እርሱ ሊያውቅ እንደሚችል በማሰብ የሚጽፈው ትክክል መሆኑን መቀበሉ ተገቢ ይሆናል::

4ዮሴፍም ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ በገሊላ
ሉቃ 2÷4-7 አውራጃ ከምትገኘው ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ የዳዊት
ከተማ ወደ ሆነችው ቤተልሔም ወደምትባል ከተማ ወደ
ይሁዳ ወጣ:: 5ወደዚያም ለመመዝገብ የተጓዘው፣ የመውለጃ ጊዜዋ ከተቃረበው
ከእጮኛው ከማርያም ጋር ነበር:: 6በዚያም እንዳሉ የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ 7የበኵር
ልጅ የሆነውን ወንድ ልጅ ወለደች፣ በጨርቅም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማረፊያ
ቦታ ስላላገኙ በግርግም አስተኛችው::

ዮሴፍ ማርያምን ይዞ ከናዝሬት ወደ ቤተልሔም 112 ኪ.ሜ. ተጓዘ:: ይህች፣ «እንጀራ ቤት» ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ 8 ኪ.ሜ. ያህል ትርቃለች:: «የሕይወት እንጀራ» የተወለደው በዚህ ቦታ (በግምት ታህሳስ 5 ዓ.ቅ.ክ ወይም ጥር 4 ዓ.ቅ.ክ ነበር:: ይህም የሚክ 5÷2 ትንቢት ፍጻሜ ነበር:: በዚህች አነስተኛ መንደር መሲሑ ተላቀን መገለጡን አደረገ::

W.Brindle, "The Census and Quirinius, Luke 2:2," *JETS* 27 (Mar 1984): 47-52 እና J.Nolland, *Luke*, ገጽ 101 ይመልከቱ::

ዮሴፍና ማርያም ጋብቻ ለመፈጸም ቃል ኪዳን የገቡ መሆናቸውን ሉቃስ ማመልከቱ ትክክል ነበር:: ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመታቀባቸው በስተቀር በእርግጥ ባልና ሚስት ነበሩ (ማቴ 1÷24 ጋር ያነ):: ወደ መንደሩ ሲደርሱ የሚያርፉበት ቦታ ፈለጉ:: ስለ ኢየሱስ ልደት በአእምሮአችን የሳልነው የተለመደ አስተሳሰብ ዮሴፍና ማርያም ግድ በሌለው ወይም እንግዶች በበዙበት አሳላፊ የሚያርፉበት ቦታ ተነፍገው በረት ውስጥ ማረፋቸውን ነው:: ይህ ግን ትክክል እንዳልሆነ ባይሌ መከራከሪያ ያቀርባል::[5] በመጀመሪያ ደረጃ የፖለስቲና ሰዎች እንግዳ በመቀበል የተደነቁ ናቸው:: ለእነዚህ ሁለት ሰዎች አንድ ክፍል የሚያዘጋጅ ሰው አይጠፋም፤ ይልቁንም ማርያም ቀኗ የደረሰ እርጉዝ ከመሆኗና ከተማውም የዮሴፍ ዘመዶች ያሉበት ከመሆኑ አንጻር ይሄ ሊሆን ይገባል:: የእንግዶች ማረፊያ በአብዛኛው በሮማውያን እንጂ በአይሁድ ዘንድ የተለመደ አልነበረም:: ቤተልሔም ትልቅ ከተማ ወይም የንግድ መለዋወጫ መስመር ላይ ስላልነበረች በዚያ ቦታ በመደበኛ መኖሪያ ቤቶች ከሚገኝ የእንግዶች ማረፊያ ሌላ ሊኖር አይችልም:: ይህ ቃል «የእንግዶች ክፍል» ተብሎ ቢተረጐም በእርግጥ የተሻለ ይሆን ነበር (ሉቃ 22÷11 ጋር ያነ):: «የእንግዶች ማረፊያን» ለመግለጽ የተለመደው ቃል ፓንዶቼዮን (*pandocheion*) (ሉቃ 10÷34 ጋር ያነ) እንጂ ካታሊማ (*katalyma*) አልነበረም:: ስለሆነም ኢየሱስ የተወለደው በግለሰብ ቤት እንጂ በበረት ውስጥ አልነበረም የሚል ሐሳብ እናቀርባለን::[6]

ታዲያ ቤት ውስጥ ግርግም (የከብቶች መመገቢያ) መኖሩ ለምን አስፈለገ:: ባይሌ እንደሚለው ብዙ ጊዜ የፖለስቲና ቤቶች ቤተሰቡ

[5] K.E. Bailey, "The Manager and the Inn, '*Bible & Spade* 10 (Sum Aut 1981): 74-35.

[6] ጥንታዊው ትውፊት ኢየሱስ የተወለደው በዋሻ ውስጥ ነበር ይላል (Justin Martyr, *Dialogue with Trypho*, 79; *Protevangelion of James*, 7-14) ሆኖም ብዙ የፖለስቲና ቤቶች ከዋሻ የተሠሩ ነበሩ::

ከሚኖርበት እልፍኝ በታች የምድር ቤት መግቢያ ነበራቸው (ሉቃ 13÷15 ጋር ያነ):: ከብቶቹ ሌሊት እንዳይሰረቁ ወይም በክረምት ወቅት ቤቱን ለማሞቅ ወደ ውስጥ እንዲገቡ ይደረግ ነበር:: እርግጥ ነው ከግድግዳው ጋር የተያያዘ ወይም ወደ ምድር ቤት በመግቢያውና ከፍ ብሎ በተሠራው በቤተሰቡ እልፍኝ መካከል የከብቶቹ መመገቢያ ይኖራል:: በአጭር አነጋገር በፖለስቲና ቤቶች ውስጥ በረት መኖሩ የተለመደ ነበር:: ስለሆነም ከቀጥር 6-7 ያለው «ማርያምና ዮሴፍ ወደ ቤተልሔም ከመጡ ከጥቂት ወቅቶች በኋላ ማርያም ወለደች::[7] የእንግዶቹ ክፍል ተይዞ ስለ ነበር በዋናው እልፍኝ አካባቢ ወለደች፤ ግርግሙንም ለሕፃኑ ማስተኛ ተጠቀመችበት» ተብሎ እንዲነበብ ሃሳብ እናቀርባለን:: በተለመደው የአይሁድ ወግ ሙቀት እንዲያገኝና ከጥቃት ለመከላከል የሕፃኑን እግሮች በጨርቅ ጠቀለለቻቸው::

ኢየሱስ «በኩር» ተብሎአል:: ይህ በዋነኛነት ደረጃ በሙሴ ሕግ መሠረት የነበረውን ሕጋዊ አቋም (ዘፀ 13÷2፤ ዘዳ 21÷15-17) ከማሳየቱም በተጨማሪ ማርያም ሌሎች እንደ ነበሯትም ያመለክታል:: ከልጆቿም መካከል ቢያንስ ስድስቱ በስም ተጠቅሰዋል:: ያዕቆብ ዮሴፍ ይሁዳ፣ ስምዖንና (ማቴ 13÷55) ቢያንስ ሁለት እኅቶቻቸው:: ምንባቡን እንዲሁ ብንቃኘው እንኳ ኢየሱስ በእናቱ በኩል ታናናሽ ወንድሞችና እኅቶች እንደነበሩት በቀላሉ ማየት ይቻላል::

**§ 11**
**የእረኞቹ መስገድ**
**(ሉቃ 2÷8-20)**

8በዚያው አገር በሌሊት መንጋቸውን ሲጠብቁ
በሜዳ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ:: 9የጌታም መልአክ
ድንገት መጥቶ በአጠገባቸው ቆመ፤ የጌታም ክብር
በዙሪያቸው አበራ፤ ታላቅም ፍርሃት ያዛቸው 10መልአኩ
ግን እንደዚህ አላቸው፤ «አትፍሩ፤ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን
ታላቅ ደስታ የምሥራች አምጥቼላችኋለሁና» 11ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኅን
ተወልዶላችኋልና እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነው:: 12ይህ ምልክት ይሆናችሁ፤ ሕፃን ልጅ
በጨርቅ ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ:: 13ድንገትም ብዙ የሰማይ ሰራዊት
ከመልአኩ ጋር ታዩ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ እንዲህ አሉ 14«ክብር ለእግዚአብሔር
በአርያም ሰላምም እርሱ ለሚወዳቸው ይሁን»::

*11ወይም መሲሕ «ክርስተስ» (ግሪክኛ) እና «መሲሑ» (ዕብራይስጥ) የሁለቱም ትርጉም «የተቀባው» ማለት ሲሆን በቁ 26 ላይም አለ::*

እረኝነት ከሥራዎች ሁሉ በጣም ዝቅተኛ ሥራ ነው:: ሥራው የተናቀ ሊሆን የቻለው እንደሚገባው የሕጉን መመሪያ ጠብቆ የእረኝነት ተግባርን መፈጸም አጅግ አዳጋች በመሆኑ ነበር:: ስለሆነም ከመጀመሪያው አንሥቶ ማኅበረሰቡ የሚንቃቸውን በሙሉ እግዚአብሔር በምሕረቱ ይመለከታቸው እንደነበር እናስተውላለን::

በሌላ በኩል ደግሞ እረኝነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለሚጠበቁ ምሳሌ መሆኑንም መገንዘብ ይኖርብናል:: ይህ ምሳሌ ወጣት እረኛ ከነበረው ከዳዊት የእረኞች አለቃ እስከሆነው ኢየሱስ ድረስ፣ ከእስራኤል ሽማግሌዎች አንሥቶ እስከ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ድረስ በተምሳሊት የሚያገለግል ነው (መዝ 23÷1 ኢሳ 40÷11፤ ኤር 23÷1-4፤ ዕብ 13÷20 1ጴጥ 2÷25፤ 5÷2)::

ምናልባትም እነዚያ ዝቅተኛ መስለው የሚታዩት እረኞች ለመሥዋዕት የሚሆኑ የበግ ግልገሎችን እየጠበቁ ሊሆን ይችላል:: በሌላ አነጋገር በጐቹ ካደጉ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ይወሰዱና ለእስራኤል ኃጢአት መሥዋዕት ሆነው ይታረዳሉ:: እነዚህ እረኞች ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት ስለሚሞተው የአግዚአብሐር በግ (ዮሐ 1÷29) በጭላንጭል ለመመልከት ተቃርበው ነበር:: ድርብ ተምሳሊት አለን:: እረኞቹ አንዱን እውነተኛ እረኛ ያገኙታል፤ እርስ በርሱ የሚቃረን ቢመስልም እንኳ እውነተኛውንም በግ ያገኙታል::

[7] ቁጥር 6 ወደ ቤተልሔም በደረሰበትና ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ መካከል ጥቂት ጊዜ ሳይኖር እንደማይቀር የማያገናዝብ ይመስላል::

እረኞች በረት ውስጥ ከማስገባት ይልቅ ከበጐቻቸው ጋር በሌሊት ውጪ ማደራቸው እንግዳ ነገር ይመስላል:: ይሁን እንጂ ለሕዝብ ቆጠራው ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱት ሰዎች በድንገት ቁጥራቸው ከፍ ብሎ ይሆናል ብለን ብናስብ፤ ይህ ጊዜ ለእነርሱ መሥዋዕት ለማቅረብ ምቹ ጊዜ ይሆንላቸዋል:: ምናልባት በረቶቹ ሁሉ ሞልተው ሊሆን ይችላል:: በታኅሣሥና በጥር በፓለስተና እረኞቹ መስክ ላይ ያሉትን በጐች እየጠበቁ ማደር እስከማይችሉ ድረስ ሌሊቱ በጣም አይበርድም:: ሆኖም ሉንግኔከር እንደሚለው ይህ ኢየሱስ ስለ ተወለደበት ቀን የሚያመለክተው እጅግም ጉዳይ የለውም:-

> የተለመደው የልደት ቀን የተወሰነው ሁኔታው ከተፈጸመ በኋላ ብዙ ዓመታት ቆየቶ ነበር፤ በዚህ ቀን እንዲውል የተደረገውም ከአረማውያን በዓል ጋር እንዲገጣጠም ታስቦና «የማትሸነፈው ፀሐይ» (Sol Invictus) በእርግጥ መሸቃፋን ለማሳየት ነበር:: በአራተኛው መቶኛ ዓመት መጨረሻ ላይ ታኅሣሥ 25 የኢየሱስ ልደት ቀን ሆኖ በስፋት ይከበር ነበር:: ጥር 6 ደግሞ ሰብዓ ሰገል እንደመጡ የሚታሰብበት በመሆኑ እንደ አስፈላጊ ቀን የሚቈጠርና በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ኢፒፋኒ ተብሉ የሚከበር በዓል ነበር (ገጽ 845)::

እረኞቹ መላእክቱን ሲያዩ ፈርተው ነበር:: መላእክትን ዐይቶ የማይፈራ ማነው? ዘካርያስ፣ ማርያምና ዮሴፍ ሁሉም መልአክን ተመልክተዋል ሁሉም ደግሞ ፈርተው ነበር:: ከመልአኩ በተጨማሪ እነዚያ እረኞች የጌታን ክብር በዙሪያቸው ሲያበራ አይተዋል:: ስለሆነም ታላቅ ፍርሃት መፍራታቸው ሊያስገርመን አይችልም::

በ«ዳዊት ከተማ» ምልክትን ለማየት እንዲጠባበቁ ተነግሯቸዋል:: በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ይህ ሐረግ አርባ ሦስት ጊዜ



ተጠቅሷል:: በሁሉም ስፍራ አብዛኞቹ ደግሞ ሐረጉ የተጠቀሰው ከኢየሩሳሌም ጋር በተያያዘ ነበር:: ሆኖም ዳዊትም የተወለደው እዚያ በመሆኑ ቤተልሔምንም ሊያመለክት ይችላል (1ሳሙ 17÷12):: ምልክቱ በጨርቅ ተጠቅልሎና ግርግም ውስጥ ተኝቶ የሚያገኙት አዲስ የተወለደ ሕፃን ነበር:: አዲስ የተወለደ ሕፃን በጨርቅ «መጠቅለል» የተለመደ የድኅረ ወሊድ እንክብካቤ ነው:: ሆኖም ይህን ምልክት የተለየ የሚያደርገው በረቱ ነው:: ግርግምን እንደ ሕፃን አልጋ መጠቀም የተለመደ አይደለም::

መላእክት የምሥራች በተናገሩበት በሦስቱም ጊዜያት ለእግዚአብሔር ሕዝብ እምነታቸውን የሚያጸና ምልክት ተሰጥቷቸው እንደ ነበር እንገነዘባለን:: ዘካርያስ ዲዳና ደንቆሮ ሆኖ ነበር:: ኤልሳቤጥ በስተ እርጅናዋ በተአምር እንደ ፀነሰች ማርያም አይታለች:: አሁን ደግሞ እረኞቹ በመላእክቱ በተነገራቸው ሁኔታ ኢየሱስን ሊያገኙ ነው:: ከዚህ የምንማረው ነገር አለ:: እግዚአብሔር በጭፍን እንድናምን አይፈልግም:: አስፈላጊውን ነገር ከነገረን በኋላ፣ የሰጠንን መልእክት በምልክቶች ያጸናዋል:: የተአምራት ዓላማም ይኸው ነው:: እምነት ማለትም «እግዚአብሔር እንደ ቃሉ ያደርጋል ብሉ መቀበል» ማለት ነው::

በዚያ ተመሳሳይ ወቅት ብዛት ያለው የመላእክት ሠራዊት (ቃል በቃል፣ «የሰማይ ሠራዊት»)፣ ተዋጊ መላእክት ተገልጠው ጦርነትን ሳይሆን ሰላምን ዓወጁ:: በተጨማሪም ሙይለርና ዶድ ሁለቱም አውደኪያስ (*eudokis* - በጐ ፈቃድ) ፈቃድን ወይም ምርጫን እንጂ ስሜትን የሚመለከት አለመሆኑን ገለጸዋል::[8] በሌላ አነጋገር

[8] C.H. Dodd, "New Testament Translation Problems II," *BT* 28/1 (Jan 1977): 104-110; and T. Mueller, "Observations on Some New Testament Texts Based on Generative Transformational Grammar," *BT* 29 (Jan 1978): 117-120.

እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ድነትን የሰጠው በሰዎች ደስ በመሰኘቱ አይደለም:: ይልቁንም ይህን ታላቅ ስጦታ በክርስቶስ በኩል በስጦታ ማበርከት ስለ መረጠ ነው:: ማጠቃለያው ሐሳብ እግዚአብሔር ኢየሱስን የሰጠን በራሱ ሉዓላዊ ምርጫ እንጂ በሰዎች ደስ የሚያሰኝ ባሕርይ ምክንያት አልነበረም::

**ሉቃ 2÷15-20**

[15]መላእክቱ ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ
ከወጡ በኋላ እረኞቹ «ጌታ የገለጠልንን ይህን የሆነውን
ነገር እንድናይ ወደ ቤተልሔም እንሂድ» ተባባሉ [16]እነርሱም
ፈጥነው ሄዱ፤ ማርያምንና ዮሴፍን፣ ሕፃኑን በግርግም ተኝቶ አገኙ:: [17]ካዩም በኋላ
ስለ ሕፃኑ የተነገራቸውን ገልጠው አወሩ:: [18]ይህንንም የሰሙ ሁሉ እረኞቹ በነገሩቸው
ነገር ተደነቁ፤ [19]ማርያም ግን ይህንን ሁሉ በልቧ ይዛ ታሰላስል ነበር:: [20]እረኞቹም
ሁሉም ነገር እንደ ተነገራቸው ሆኖ በማግኘታቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ
እግዚአብሔርን እያከበሩና እያመሰገኑ ተመለሱ::

እረኞቹ እየገሠገሡ በቀጥታ ወደ ቤተልሔም ሄዱ (ምናልባትም በጐቹን ዕጣ ለወደቀበት ምስኪን እረኛ በአደራ ሰጠተው ይሆናል):: በእርግጥም መላእክቱ እንደ ነገሯቸው ሆኖ አገኙት:: ያዩትን ሁሉ በከተማው አካባቢ አደረሱ፤ እንደሚጠበቀውም ሁሉ ነገሩን የሰሙ ሁሉ ተደነቁ:: አሽልባ ለነበረች እንደ ቤተ ልሔም ላለች ትንሽ ከተማ በጣም ትልቅ ጉዳይ ነው:: ማርያም የምትፈልገውን ሁሉ አግኝታለች:: እስከ በዚህን ጊዜ መረዳት የቻለችውን ሁሉ አስቡ:: ከመልአኩ ገብርኤል፣ ከዮሴፍ ሕልም፣ ኤልሳቤጥ ከተናገረችው፣ የዘካሪያስን ትንቢት፣ እረኞቹ ያመጡትን መገለጥና ሌሎችንም መሲሐዊ ትንቢቶች ሁሉ ስምታለች:: አሁን ደግሞ ከስምዖንና ከነቢይቱ ሐና ተጨማሪ መገለጥ ልታገኝ ነው::[9]

ማርያም የምታስበው ብዙ ነገር ነበራት:: «ታሰላስል ነበር» የሚለው ታብሰለስል ነበር በማለት ሊተረጐም ይችላል:: ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በአእምሮዋ ውስጥ ታወጣ ታወርድ ነበር::

**§ 12**
**የኢየሱስ መገረዝ**
**(ሉቃ 2÷21)**

[21]ስምንት ቀን ሆኖት የመገረዣ ጊዜው ሲደርስ
ከመፀነሱ በፊት መልአኩ ባወጣለት ስም ኢየሱስ ተባለ::

ሉቃስ የዮሐንስንና የኢየሱስን ልደት ማወዳደርና ልዩነታቸውን ማመልከት ቀጠሉአል:: እንደ ዮሐንስ ሁሉ ኢየሱስም (1) በስምንተኛ ቀኑ ተገርዟል (2) በተገረዘበት ዕለት ስም ወጥቶለታል (3) ገና ከመፀነሱ በፊት ተገልጾ በነበረ መልአክ ስም ተሰጥቶታል::

በእርግጥም ኢየሱስ የተወለደው፣ ከሕግ በታች ነበር (ገላ 4÷4):: ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በሁለንተናው ምንም እንከን የማይገኝበት ነበር:: ትረካው የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው::

---

[9] በአሁኑ ጊዜ ማርያም ስለ ኢየሱስ ያወቀቻቸውን ሁሉ አስቡ፡-

**I. ከገብርኤል** (ሉቃ 1÷31-35)፣ (1) ታላቅ እንደሚሆን፣ (2) የልዑል ልጅ መሆኑን፣ (3) በዳዊት ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ (ኢሳ 9÷6-7 ጋር ያነ)፤ (4) በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘላለም እንደሚነግሥ፣ (5) ለመንግሥቱ ፍጻሜ እንደሌለው፣ (6) ቅዱስ እንደ ሆነ፣ (7) የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ተነግሮአታል::

**II. ከኤልሳቤጥ** (ሉቃ 1÷43)፣ (8) «የጌታዬ እናት» መባሏ::

**III. ከማርያም መዝሙር** (ሉቃ 1÷48-55)፣ (9) «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» ማለቷ፣ (10) እስራኤልንና የአብርሃምን ዘሮች ሁሉ እንደሚረዳ::

**IV. ከዮሴፍ** (ማቴ 1÷20-23)፣ (1) ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚፀነስ፤ (2) ሕዝቡን ከኃጢአታቸው እንደሚያድናቸው፤ (3) አማኑኤል («እግዚአብሔር ከእኛ ጋር») እንደሚባል በኢሳ 1÷4 መሠረት::

**V. ከእረኞቹ** (ሉቃ 2÷11)፣ (14) አዳኝ መሆኑ::

**VI. ከስምዖን** (ሉቃ 2÷26-35)፣ (15) ክርስቶስ መሲሕ መሆኑን፤ (16) ድነትና ለአሕዛብ መገለጥን የሚሰጥ ብርሃን መሆኑ (ኢሳ 42÷6 እና 49÷6 ጋር ያነ)፤ (17) በእስራኤል ለብዙዎች መነሣትና መውደቅ ምክንያት እንደሚሆን፣ (18) በራሷ የማርያም ነፍስ በሰይፍ እንደሚወጋ::

**VII. ከነቢያት** (ሉቃ 2÷38)፣ (19) [illegible] እንደሚሆን አውቃለች::

### § 13 ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ተወሰደ (ሉቃ 2፥22-38)

የመንጻት ሥርዓትን ለመፈጸም (1ሳሙ 1፥24፣28 ጋር ያነ) ወላጆቹ ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ ሲወስዱት ከሁለት የከበሩ ሰዎች ጋር ተገናኙ፡ እነርሱም፡- ስምዖንና ሐና ነበሩ:: ሁለቱም በዕድሜ የገፉና በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ነበሩ:: በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ይህን ልጅ ለማየት ሲጠባበቁ ስለ ነበር የጠበቁትን በማየታቸው ሕይወታቸው የተሟላ ሆነ:: ከዚህም በላይ የስምዖን ትንቢት፣ (Nunc Dimittis) ከዘካርያስ ቡራኬ ("Benedictus") ጋር ይመሳሰላል:: ሁለቱም የተናገሩት አዲስ የተወለደው ሕፃን የሚኖረውን የአገልግሎት ድርሻ ያብራራሉ::

**ሉቃ 2፥22-24**

22 በሙሴ ሕግ መሠረት የመንጻታቸው ወቅት
በተፈጸመ ጊዜ ዮሴፍና ማርያም ሕፃኑን ለጌታ ለማቅረብ
ወደ ኢየሩሳሌም ይዘውት ወጡ፤ 23 ይኸውም በጌታ ሕግ
ተባዕት የሆነ በኩር ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ ይሆናል ተብሎ እንደ ተጻፈ ለመፈጸምና[ሀ]
24 ደግሞም በጌታ ሕግ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች» እንደ ተባለ
መሥዋዕት ለማቅረብ ነበር::[ለ]

*[ሀ]23 ዘፀአት 13፥2፣12 [ለ]24 ዘሌ 1፥28*

ዘሌዋውያን 12፥1-8 አንዲት ሴት ከወለደች በኋላ ሊኖራት ስለሚገባ የመንጻት ጊዜና መሆን ስላለበት ነገር ይናገራል:: የተወለደችው ሴት ከሆነች እናትዬዋ ለዐሥራ አራት ቀናት ርኩስ ትሆናለች፤ ደግሞም «ከደሟ እስክትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን» ድረስ ልትቆይ ይገባል:: ወንድ ልጅ ከወለደች በኋላ ለሰባት ቀን ርኩስ ትሆናለች፤ ስምንተኛው ቀን የልጁ የመገረዣ ቀን ይሆናል፤ ሴትዬዋም «ከደሟ እስክትነጻ ድረስ ሠላሣ ሦስት ቀን» ድረስ ልትቆይ ይገባል:: ከዚህ ጊዜ (ወንድ ከሆነ ከዐርባ ቀን ሴት ከሆነች ከሰማንያ ቀን) በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ ሁለት መሥዋዕቶች ታቀርባለች:: የመጀመሪያው ለሚ[illegible] ጠቦት ማቅረብ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ርግብ ወይም ዋኖስ ለኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነው:: ድሀ ከሆነች ግን ከጠቦት ይልቅ ዋኖስ ወይም የርግብ ጫጩቶች ማቅረብ ትችላለች::: የሁለቱ ወፎች ዋጋ ከኢት. ብር 2.00 ያነሰ ነው:: ማርያምና ዮሴፍ እንዲህ ያለ መሥዋዕት በማቅረባቸው ከድሆች ወገን እንደ ነበሩ አስመስክረዋል:: በሴቶች የማምለኪያ አደባባይ መባ የሚቀመጥባቸው ዐሥራ ሦስት የመለከት ቅርጽ ያላቸው ቅርጫቶች ነበሩ:: በእነርሱ አጠራር ሦስተኛው የመለከት ቅርጽ ያለው ግን ድሆች ለመሥዋዕት ለሚሆኑ እንስሳት የሚከፍሉትን መባ ወይም ስጦታ መክተቻ ነበር::

የመንጻቱ ሥርዓት ሁለት ዓላማዎች ነበሩት:: የመጀመሪያው የሰውን ልጅ ርኩሰትና የእግዚአብሔርን ንጽሕና ማሳየት ነው:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማርገዝ ወይም መውለድ ኃጢአት እንደ ሆነ አድርገን በመቍጠር ያልተጻፈ ነገር ማንበብ የለብንም:: ሁለተኛው ግን ጉዳዩ ንጽሕናን ከመጠበቅ አኳያ ብቻ ሊታይ ይገባል:: እናትና ልጅ ለዐርባ ቀን ያህል ከሰዎች ተገልለው ለብቻቸው ያርፋሉ::

ዘፀአት 13፥2-12 በኩር ወንድ ልጅ ስለሚቀደስበት ሁኔታ ይናገራል:: ሰውም ይሁን እንስሳ እግዚአብሔር በኩር የሆነ ሁሉ ለእርሱ እንዲሰጠው ይጠይቃል:: ከዚያ በኋላ የተወሰነ ዋጋ በመክፈል ከጌታ መልሰው ይዋጇቸዋል:: የሚወሰነው ዋጋ በግምት አርባ አምስት ወይም ዘጠና ብር ይሆናል:: ይህ ሥርዓት የተደነገገው ዐሥረኛው መቅሠፍት ግብፅ ላይ ወርዶ የበኩር ልጆች ሁሉ ከተገደሉ በኋላ እንደ ነበር መረዳት አለብን:: እስራኤላውያን ነፃ የወጡት ከዚህ መቅሠፍት በኋላ ነበር:: የበኩር ልጅ መቀደስ በምልክትነት እንዲያገለግል የታቀደ ነበር:: እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ እንዴት እንዳዳነ የሚያስታውስ መታሰቢያ ነበር::

**ሉቃ 2÷25-32**

25በዚያን ጊዜ ጻድቅና ትጉሕ የሆነ ስምዖን
የሚባል አንድ ሰው በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር እርሱም
የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅና መንፈስ ቅዱስ በላዩ
ያደረ ሰው ነበር። 26ደግሞም የጌታን መሲሕ ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ ቅዱስ
ተገልጦለት ነበር፤ 27እርሱም በዚህ ጊዜ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ
የልጁም ወላጆች በሕጉ ልማድ መሠረት ተገቢውን ሊፈጽሙለት ሕፃኑን ኢየሱስን ይዘው
በገቡ ጊዜ 28ስምዖን ተቀብሎ ዐቅፈው እግዚአብሔርን እያመሰገነ እንዲህ አለ፦

29ጌታ ሆይ ቃል በገባኸው መሠረት፤
አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተው፤
30ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን፣
31ማዳንህን አይተዋልና።
32ይህም ለአሕዛብ መገለጥን የሚሰጥ ብርሃን ለሕዝብህ ለእስራኤልም ክብር ነው።

ስምዖን በግልጽ ካህን ነው። እንዲያውም ሕፃኑን ይዘውት በቀረቡ ጊዜ በእጁ አቅፎ ባርኮታል። ይህ ደግሞ የካህን ተግባር ነበር። ሆኖም እርሱ ከካህንም በላይ ነበር። በንጽሕናውና ትዕግስትን በተላበሰ ተስፋ መሲሑን ሲጠባበቅ በመኖሩ እግዚአብሔር ነቢይ እንዲሆን ፈቅዶለታል። እንደ ጥንቱ ነቢያት ሁሉ መንፈስ ቅድስ በእርሱ ላይ ወርዶ በእርሱ የሕይወት ዘመን መሲሕ እንደሚመጣ ገልጦለት ነበር። ማርያምና ዮሴፍ ሕፃኑን ወደ ቤተ መቅደስ ባመጡት ጊዜ እንኳ በትክክለኛው ጊዜ በትክክለኛው ስፍራ እንዲገኙ እርምጃቸውን መንፈስ ቅድስ ራሱ ይመራ ስለ ነበር፣ ያገኙት የመጀመሪያ ካህን እርሱ ነበር።

ስምዖን ኢየሱስን በእጁ ዐቅፎ፣ «የእስራኤል መጽናናት» ስለ መጣ እግዚአብሔርን አመሰገነ (ኢሳ 40÷1፤ 49÷13፤ 51÷3፤ 52÷9፤ 54÷11፤ 61÷2፤ 66÷13፤ ኤር 31÷13)። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለእስራኤል መጽናናት ከመሆኑም በላይ ለአሕዛብም ብርሃን ነበር። ይህ በስምዖን ዘመን ለነበሩ አይሁድ እንግዳ ሐሳብ ነበር። ምንም እንኳ ብሉይ ኪዳን ስለ አሕዛብ መዳን በተደጋጋሚ ቢያመለክትም (ዘፍ 12፡3፤ መዝ 67÷2፤ ኢሳ 2÷2፤ 42÷6፤ **49÷6**፤ ኢዩ 2÷28፤ አሞ 9÷11-12 ወዘተ) አይሁድ ግን በዚህ ጉዳይ የአሕዛብን መካተት ሲቃወሙ ቆይተዋል። ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን እንኳ ይህን መቀበል ከብዷት ነበር። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አሕዛብን በቤተ ክርስቲያን መቀበል አለመቀበልን ያህል ከፍተኛ ክርክር ያስነሣ ነገር አልነበረም (10-11፣ 15፤ ምዕራፎችንና 28÷28 ጋር ያነ)።

**ሉቃ 2÷33-35**

33አባቱና እናቱም ስለ እርሱ በተነገረው ነገር
ተገረሙ። 34ስምዖንም ባረካቸው፤ እናቱን ማርያምንም
እንዲህ አላት፤ «ይህ ሕፃን በእስራኤል ለብዙዎች መነሣትና
መውደቅ ምክንያት እንዲሆን፣ ደግሞም ክፉ ለሚያስወሩበት ምልክት እንዲሆን
ተወስኖአል፤ 35የብዙዎችም የልብ ሐሳብ የተገለጠ እንዲሆን፣ የአንቺም ነፍስ ደግሞ
በሰይፍ ይወጋል።

ምንም እንኳ ስምዖን ስለ ኢየሱስ አንዳንድ አስደናቂና አበረታች ነገሮችን ቢናገርም የተናገረው ሁሉ አዎንታዊ አልነበረም። በእስራኤል ለብዙዎች መነሣት ምክንያት ይሆናል። ለሌሎች በተለይም ለሚቃወሙት ግን የመሰናከያ ዓለት ይሆናል (ኢሳ 8÷14፤ ማቴ 21÷42፣44፤ ሐሥ 4÷11፤ ሮሜ 9÷33፤ 1ጴጥ 1÷23)። ለሚቀበሉት ትንሣኤና ሕይወት ነው (ዮሐ 11÷25፤ ሮሜ 6÷4፣9፤ ኤፌ 2÷6)።

ለመላው ሕዝብ እንደሚሆን ሁሉ ለማርያምም፣ «ውጋት» ይሆናል። ሰይፍ ነፍስዋን ይወጋል። ይሄኛው ሰይፍ አጭርና ቀልጣፋው የሮማውያን ዓይነት ሰይፍ ማቻይራ (*machaira*) አልነበረም። እየተናገረ ያለው ከፍተኛ ሕመምና ስቃይ ስለሚያስከትለው ስለ ረጅሙና ጠፍጣፋው ዓይነት ሰይፍ (ሮምፋይያ - *romphaia*) ነበር። ወደ አእምሮአችን ፈጥኖ የሚመጣው የኢየሱስ ስቅለት ነው። ማርያም

የምታጣው ልጇን ብቻ አይደለም፤ ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንኳ ስለ እስራኤል መዳን የነበራትን ተስፋ ሁሉ ታጣለች።

ሆኖም እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሰይፍ ሌላ የሚያመለክተው ነገርም ይኖራል። በብሉይ ኪዳን ሰይፍ አንዱን ከሌላው ለይቶ የሚያጠፋ ፍርድን ሲያመለክት (ሕዝ 14÷17)፣ በአዲስ ኪዳን ግን የእግዚአብሔርን ቃል ይወክላል (ዕብ 4÷12)። በአንድ ዓይነት መንገድ ይህ ሰይፍ በማርያም ላይ ለየት ያለ ፍርድ ያመጣል። ስለ ማርያም እንደ ገና በምናነብበት በሉቃስ 8÷19-12 ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል መመልከት ይቻላል (ማር 3÷31-35 ጋር ያነ)። እርሷና ሌሎቹ ልጆቿ ኢየሱስን ለማግኘት በመጡ ጊዜ እንደ ዝመድናቸው ቅርበት የተለየ አቀራረብ እንዳልተደረገላቸው ተረዱ። ይልቁንም አዲሱ የኢየሱስ ቤተሰብ የሚያካትተው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት ነው። ቤተሰብን ስለሚለያየው ሰይፍ ኢየሱስ በተናገረበት በማቴዎስ 10÷34-36 ይህ መሪ ሐሳብ በድጋሚ ተነሥቶአል። ምንም እንኳን ማርያም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ብትሆንም እንደ እናትነቷ ማግኘት የነበረባትን የተለየ መብት ይህ ሰይፍ እንዳሳጣት ተሰምቷታል። ይህ ግንዛቤ ከሉቃስ 2÷41-50 ለምንመለከተው ቀጣይ ሁኔታ ያዘጋጀናል።

<table>
<tr><td></td><td>36 ደግሞም ከአሴር ወገን የሆነች የፋኑኤል ልጅ፣</td></tr>
<tr><td>ሉቃ 2÷36-38</td><td>ሐና የምትባል ነቢይት በዚያ ነበረች፤ እርሷም በጣም<br>እርጅታ ነበር፣ በድንግልናዋ ካገባችው ባሏም ጋር ሰባት</td></tr>
</table>

ዓመት የኖረች ነበረበች 37 ዕድሜዋም ሰማንያ አራት ዓመት እስኪሆናት ድረስ ቀንና
ሌሊት ከቤተ መቅደስ ሳትለይ፣ በጾምና በጸሎት የምታገለግል መበለት ሆና ቆየች።
38 በዚያኑም ጊዜ ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም መቤዠት
ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ ሕፃኑ ተናገረች።

*37 ወይም ለሰማንያ አራት ዓመት መበለት የነበረች*



የስምዖን ባልደረባ ወደ መድረኩ ብቅ አለች። ስሟ ሐና ይባል ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት አያሌ የሴት ነቢያት አንዷ ነበረች (ዘፀ 15÷20፤ መሳ 4÷4፤ 2ነገ 22÷14፤ ነህ 6÷14፤ ኢሳ 8÷3፤ ሐሥ 2÷17፤ 21÷9፤ 1ቆሮ 11÷5)። በዚያን ጊዜ ሰማንያ ዓመት የሆናት አሮጊት መበለትም ነበረች።[10] ለሰባት ዓመት ያህል ከባሏ ጋር ነበረች። እንግዲህ ስታገባ የዐሥራ ሰባት ዓመት ልጃገረድ እንደ ነበረች ብናስብ ለስድሳ ዓመታት ያህል በመበለትነት ኖራለች ማለት ነው። በመቅደሱ አካባቢ በጣም የታወቀች ነበረች።

ለመሲሑ መምጣት እግዚአብሔር ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ሲያመቻች እንደ ነበረ አስተውላለች።[11] ዩሊየን ቄሣር ሥልጣን ሲይዝ በኋላም በሰው እጅ እንደ ተገደለ ታውቃለች። ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ከዕዝራና ከነህምያ ዘመን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ነጻነትን ያቀዳጀ አስደናቂው የመቃብያን የሥልጣን ዘመን በጥድፊያና በአሳዛኝ ሁኔታ ሲወድቅ ተመልክታለች። ሮማዊው ጄኔራል ፖምፔ መካከለኛ ምሥራቅን ለሮም ድል ባደረገበት ወቅት ወጣት ሴት ነበረች። የተጠሉት ኤዶማውያን የሄሮድስ ቤተሰብ በፖለስቲና ሥልጣን መያዛቸውን ታውቃለች። ሁለቱ ተቃራኒ ሃይማኖታዊ ቡድኖች (ፈሪሳውያንና ሰዶቃውቃን) በተነሱበት ወቅት ታዛቢ ነበረች። በሮማውያን ከባድ የግብር ቀንበር እንዲሁም በአይሁድ ሃይማኖታዊ የወግ አጥባቂነት ቀንበር ሥር ኖራለች። ለክርስቶስ መምጣት ጊዜው እየተመቻቸ ነበር። እርሷም ለዘመናት ይህንኑ ስትጠብቅና ተስፋ ስታደርግ ኖራለች።

---

[10] አዲሱ መደበኛ ትርጉም (ምንባቡ ላይ) ሐና 84 ዓመቷ እንደ ነበር እንድናምን ይጋብዘናል። ሆኖም እንደ አዲሱ መደበኛ ትርጉም የቁጥር 37 ግርጌ ማስታወሻ «ለ84 ዓመት መበለት ነበረች» ተብሎ ሊተረጐምም ይችላል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከ100 በላይ ይሆናታል ማለት ነው። M.P. John, "Luke 2:36-37: How Old Was Anna?" *BT* 26 (Apr 1975): 247 ላይ እንዳረጋገጠው እንዲህ ሊሆን ቢችልም እርሷ ያን ያህል ዘመን መኖሯ የሚመስል ጉዳይ አይደለም ብሏል (ዮዲት 16÷ 22-23 ጋር ያነ)።

[11] Nolland (ገጽ 125) የሐና ዕድሜ ምሳሌያዊ እንጂ ቃል በቃል የሚወሰድ እንዳልሆነ ያመለክታል። «84» ምናልባት፣ 7X12= መሲሑ ሲጠበቅ የነበረበት ዘመን የሚያበቃበትን የሚወክል ሊሆን እንደሚችል ይናገራል።

ሐና ለስድሳ ስድስት ዓመት ያህል መቅደስ ውስጥ ስታመልክ ይልቁንም፣ «ስታገለግል» ኖራለች:: ጸሎትና ጾም ግሥ ሳይሆኑ ስሞች ናቸው (dative):: ስታገለግል የነበረችባቸውን ሁኔታዎች ያመለክታሉ:: ለዚያውም ከሌዊ ነገድ ያልሆነች ሴት ስለ ነበረች መሥዋዕት ማቅረብ ወይም ሌሎች የካህናት ተግባሮችን ማከናወን አትችልም:: ስታገለግል የነበረው ማድረግ በምትችለው በጸሎትና በጾም ብቻ ነበር::

ወቅቱ መሲሑ በታላቅ ጉጉት ሲጠበቅ የነበረበት ወቅት ነበር:: ኢየሩሳሌም በሮማውያን ተይዛለች:: ምግባረ ብልሹ የነበረው ኦዶማዊው ሄሮድስ የአይሁድ ንጉሥ ነበር:: ከመቶ ሃመሳ ዓመት በፊት ተነሥቶ የነበረው የመቃባውያን ዐመፅ ትዝታ ብቻ ሆኖ ቀርቷል:: ቅዱሳት መጻሕፍት ግን አይሁድ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናቸውን ለዘመናት ሲያስተጋቡ ኖረዋል:: በእነርሱ በኩል አዳኙ ይመጣል:: በጣም የሚያሳዝነው ግን የሚታይና የሚዳሰስ ነገርን መሠረት ያደረገው የግሪኮች ባሕል በሔለናዊ ተፅዕኖ መንፈሳዊ ተስፋቸውን ስላጨለመ ወታደራዊና ፖለቲካዊ መሲሕን እንዲጠብቁ አደረጋቸው::

### § 14
### የምሥራቅ ጠቢባን ኢየሱስን ለማየት መጡ
### (ማቴ 2፥1-12)

ምንባቡ ግር የሚያሰኝ ዓይነት ነው:: ለአሕዛብ ወንጌልን የጻፈው ሉቃስ ኢየሱስ መቅደስ ውስጥ እንደ ነበር ሲያቀርብ፣ ለአይሁድ ወንጌልን የጻፈው ማቴዎስ ግን አሕዛብ ሰጥተውት የነበረውን ክብርና ምስጋና አቅርቦአል (ኤደርሼም I:202):: በስምዖን ትንቢት ማጠቃለያ ላይ የትንቢቱን የመጀመሪያ ፍጻሜ ፍንጭ ማለትም ኢየሱስ የአሕዛብ ብርሃን መሆኑን እናያለን:: እስካሁን ድረስ የወንጌል ዘር ሴቶችን፣ በማኅበረሰቡ የተገለሉትን (እረኖች)፣ አሕዛብን (ሰብዓ ሰገል) ጉልህ በሆነ መንገድ እየነካ እንደ ነበረ እናያለን::



[1]በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው፣[ሀ] [2]የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በምሥራቅ[ለ] ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናል» ሲሉ ጠየቁ:: ማቴ 2፥1-6

[3]ንጉሡ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፤ እንዲሁም መላይቱ ኢየሩሳሌም አብራ ታወከች [4]እርሱም የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን በሙሉ ሰብስቦ፣ ክርስቶስ[ሐ] የት እንደሚወለድ ጠየቃቸው:: [5]እነርሱም፣ «በይሁዳ ቤተልሔም፤ ነቢዩ እንዲህ ብሎ ጽፎአልና አሉ፤

[6]በይሁዳ ምድር የምትገኚው አንቺ ቤተልሔም፤
ከሌሎቹ የይሁዳ ገዢዎች በምንም አታንሺም፤ የሕዝቤ
የእስራኤል[መ] ጠባቂ የሚሆን፣ ከአንቺ ይወጣልና::»

[ሀ]1 በተሰምደ ሰብዓ ሰግል [ለ]2 ወይም ኮከቡ ሲወጣ
[ሐ]4 ወይም መሲሕ [መ]6 ሚክያስ 5፥2

ጠቢባኑ በሜዶን በኋላም በፋርስ ንጉሣዊ አገዛዝ ከፍተኛ ፖለቲካዊ /ሃይማኖታዊ አማካሪዎች ወይም ባለ ሥልጣኖች ነበሩ:: አዲስ ንጉሥ እንደሚነሣ ትንቢት በመናገርና በማቋቋም ያገለግሉ ነበር (በታይሪዴትስ ታሪክና በኔ ኔሮ ማየት እንደሚቻለው [Pliny *Natural History* 30.6.17]):: ይህ መልእክት ሄሮድስንና የተቀሩትን የኢየሩሳሌም መኳንንት ማደናገጡ የሚገርም አይደለም:: በሜሶፖታሚያ በነበረው ክልል ዙሪያ የነበሩት የሮም መንግሥት ወደ ምሥራቅ የሚያደርገውን መስፋፋት ያደርጉት ከነበረው ከፍተኛ ተቃውሞ አኳያ ስንመለከተው ይህ ይበልጥ ግልጽ ይሆንልናል::[12]

[12] R.A. Horsley, *The Liberation of Christmas* (New York: Continuum, 1493), pp. 53-60. በተጨማሪ R.E. Brown, *Birth*, pp. 167-170.

ምንም እንኳ ጠቢባኑ ከአስማታዊ ጥንቆላ አሠራር የጸዱ ነበሩ ባይባልም በዋነኛ ደረጃ ከፍተኛ ምሑራን ነበሩ። ከከብ ቆጠራን በሚመለከት ብቻ ሳይሆን፣ ሥነ ፈላክን፣ ሕክምናን፣ ሒሳብንና የተፈጥሮ ሳይንስንም ያጠኑ ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታም በአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍትና በባቢሎን ምርኮ ዘመን በሰጡት ጥበብ ሳይማረኩ አልቀሩም።

ጠቢባኑ በባቢሎን እያሉ አንድ ዓይነት የክዋክብት እንቅስቃሴ አስተውለዋል፤ ይህም አዲስ የአይሁድ ንጉሥ እየመጣ መሆኑን እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። ይህ ክስተት ምን ሊሆን እንደሚችል በርካታ ግምቶች ሲሰጡ ነበር።[13] በኮምፒተር በመታገዝ የሥነ ፈለክ ምሑራን በ6ዓ.ቅ.ክ ከሜሶፖታሚያ በግልጽ ሊታይ በሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሮአዊ የሰማይ አካላት በአንድ ረድፍ የሆኑት እንዴት እንደ ነበር ለመመርመር ሞክረዋል። በ6ዓ.ቅ.ክ በፒሽሽ የክዋክብት ክምችት ውስጥ ጁፒተርና ሳተርን በአንድ ረድፍ የሆኑበት ወቅት እንደ ነበር የሚጠቁም ሁኔታ አግኝተዋል። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያለው ሁኔታ የሚከሰተው በስምንት መቶ ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም ኢየሱስ ሊወለድ አካባቢ ግን ሦስት ጊዜ ማለትም (በግንቦት፣ በጥቅምትና በታኅሣሥ) ሆኖ ነበር። ከዓመት በኋላ ደግሞ ማርስ ከእነዚህ ዓለማት ጋር አብሮአቸው ሆነ። ይሁን እንጂ በቁጥር 9 ላይ እንደ ቀረበው ኮከቡ እየመራቸው ሕፃኑ እስካለበት ድረስ ወሰዳቸው የሚለውን ማንኛውም ተፈጥሮአዊ ፅንስ ሃሳብ አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሊገልጽልን አይችልም። ጠቢባኑ የአስጊ ወይም አሳሳቢ ነገሮች አመልካች እንደ መሆናቸው መጠን ለኮከብ ቆጠራ ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጡ ግልጽ ነው። ይህን የፕላኔቶች በአንድ ረድፍ መሆን በተመለከተም እንደ አንድ ዓይነት መለኮታዊ መልእክት ሊተረጉሙት ይችላሉ (ኤደርሼይም 1:209-216)።

ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት አቅጣጫ እንጂ ኢየሱስን ፈልገው አልነበረም። የአይሁድ ንጉሥ ወደ ነበረው ወደ ሄሮድስ እየሄዱ ነበር። ይህን ያህል ክብደት ያለው ጉዳይ ይዘው ሰው ወደ አገሪቱ መሪ መሄዳቸው ተገቢ ነገር ነው። ከዚያም በተረፈ ኢየሩሳሌም የአይሁድ ሃይማኖት መዲና ነበረች። ጠቢባኖቻቸው እንዲህ ላለው ጥያቄ መልስ ሊኖራቸው ይገባል።

ከጠቢባኑ ጋር የነበረው ቆይታ ሄሮድስን በጣም ረበሸው። በፖለቲካ እንቅስቃሴው ሄሮድስ በተለይ ከገዛ ቤተሰቡ በኩል ይደርስበት በነበረው ዐመፅና ችግር ሲታወክ ኖሯል። መንግሥቱን ይወስዱብኛል በሚል ሥጋት (ደግሞም ይህ የመሆኑ ዕድል ከፍተኛ ነበር) ከራሱ ልጆች በርካቶቹን፣ ሚስቱ ማሪያምንና (Josephus, *Ant.* 7, 61-145) እንዲሁም የሚስቱን እናት ገድሎአቸዋል።

በዚህ ላይ ደግሞ ሄሮድስ የሚሞትበት ጊዜ ተቃርቦ ነበር። ያ ጊዜ በአእምሮ ቀውስ እየተሰቃየ የነበረበት ወቅት ነበር። አካሉ ይቆሳሰልበትና በጣም የመነመነበት ጊዜ ነበር። በጣም ታምሞ የነበረበት የአእምሮ መረጋጋት ያጣበትና ከመቼውም ይልቅ ጭካኔው የበረታበት ወይም አረመኔ የሆነበት ወቅት ነበር። መንግሥቱን ሊቀናቀን ይችላል ብሎ ስለ ሠጋበት ስለዚህ ሕፃን ሲሰማ ሄሮድስ መሸበሩ ብዙ የሚገርም አይሆንም። ለእርሱ በማዘን ሳይሆን ለሁኔታው ምን ዓይነት ምላሽ ይሰጥ ይሆን ብለው በመሥጋት መላው የኢየሩሳሌም ከተማ ከሄሮድስ ጋር ታወከ። ሕዝቡ ሁሉ ዝናውን በሚገባ ያውቃል።

ምንም እንኳን በሞት አፋፍ ላይ እስኪደርስ ቢታመምም ሄሮድስ በዚያ ሁኔታ እያለም ተንኰለኛ ነበር። ቁጥር አራት ላይ ሄሮድስ የካህናት አለቆችና ጸሐፍትን ሁሉ በአንድነት መጥራቱን ተመልክተናል። መሲሕ የሚወለደው የት እንደ ነበር ከእነርሱ ተረድቷል። ቁጥር ሳባት

[13] S. Begley, "The Christmas Star— Or Was it Planets?" *Newsweek* (Dec 30,1991): 54-55. በዋነኛነት የቀረቡ አማራጮች ደማቅ ኮከብ፣ ተወርዋሪ ኮከብ ወይም የፕላኔቶች በአንድ ረድፍ መሆን ናቸው (R.E. Brown, *Birth*, pp. 170-173 ጋር ያነ)።

ላይ በምስጢር ጠቢባኑን ጠርቶ ማናገሩን እናያለን:: ሕፃኑ የሚወለደው መቼ እንደሚሆን የተረዳው ከእነርሱ ነበር:: ስለሆነም የተሟላ መረጃ በሄሮድስ እጅ የነበረ ይመስላል:: ለተወለደው ሕፃን ሄዶ መስገድ እንደሚፈልግ ያስመስል ነበር:: ስለዚህም ስለ ተወለደው ሕፃን ማግኘት የሚችለውን መረጃ ሁሉ ለማግኘት አቀደ:: ደግነቱ ግን ሄሮድስ ስላሰበው ተንኰል እግዚአብሔር ለጠቢባኑ (ቁ 12) ለዮሴፍ (ቁ 13) ስለ ገለጠላቸው ሁሉም ማምለጥ ቻሉ::

የመቅደሱ አስተዳዳሪዎችና (የካህናት አለቆች) የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን (ጸሐፍት) መሲሕ የሚወለደው በቤተልሔም እንደሆነ ከድምዳሜ ላይ ደደርሰዋል:: ሚክያስ 5÷2 በወቅቱ የነበረው አተረጓጎም ይኸው ነበር (ከJer. Ber. ii. 4) ሆኖም ቁጥር 6 ከሚክያስ 5:2 ምንባብ ብዙ ቃላትን ለውጧል::[14] በሌላ አነጋገር በትክክል የተጠቀሰ ሳይሆን «ፍቺን ያዘለ ትርጉም» ነበር:: የማቴዎስ ጽሑፍ አንባቢዎች አይሁድ እውነተኛ ትርጉሙን ይበልጥ እያብራራ ነበር እንጂ «እየዘባረቀ» እንዳልነበረ ይረዱታል:: ይህ ደግሞ በስብከት አቀራረብ ወቅት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች እንደሚብራሩ ሁሉ በአይሁድ ዘንድ በዚህ መልክ ማስተማር የተለመደ ነበር:: ሂተር የተባሉት ደራሲ በሰጡት አስተያየት ማቴዎስ በእውነቱ ሦስት ጥቅሶችን በአንድነት አጣምሮ በማቅረብ (ዘፍ 49÷10፤ 2ሳሙ 5÷2፤ ሚክ 5÷2) መሲሑ በኢየሩሳሌም መወለዱን በመተንበይ በኩል እንዴት ሦስቱም እንደሚስማሙ እያሳየ ነበር::[15]

[14] ዝርዝር ሐሳብ ለማግኘት A.J. Petrotta, "A Closer Look at Matt 2:6 and Its Old Testament Sources," *JETS* 28/1 (Mar 1985): 47-52; and G. Archer & G. Chirichigno, *O.T. Quotations in the N.T* (Chicago: Moody, 1983) ገጽ 157 ይመ::

[15] H. Heater, "Matthew 2:6 and Its O.T Sources, "*JETS* 26 (Dec 1983): 395-397.



[7]ከዚያም ሄሮድስ ጠቢባኑን በምስጢር አስጠርቶ በማነጋገር ኮከቡ የታየበትን ትክክለኛ ጊዜ ተረዳ::[8]ጠቢባኑም ወደ ቤተልሔም ልኮ፣ «ሂዱና ሕፃኑን ፈልጉ፤ እኔም ሄጄ እንድሰግድለት፣ እንዳገኛችሁት ወደ እኔ ተመልሳችሁ የት እንዳለ ንገሩኝ አላቸው:: ማቴ 2÷7-12

[9]ጠቢባኑ ንጉሡ ያለውን ከሰሙ በኋላ ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ይህም በምሥራቅ ያዩት[a] ኮከብ እየመራቸው ሕፃኑ እስካለበት ድረስ ወሰዳቸው:: [10]ኮከቡንም ሲያዩ ከመጠን በላይ ተደሰቱ:: [11]ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩ፤ ተንበርክከውም ሰገዱለት:: ሣጥኖቻቸውን ከፍተው ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም አቀረቡለት:: [12]እግዚአብሔርም ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በሕልም ባስጠነቀቃቸው መሠረት፣ መንገድ አሳብረው ወደ አገራቸው ተመለሱ::

*[a] 9 ወይም ከፍ ከፍ ሲል ተመለከቱት*

ማርያምና ዮሴፍ በቤተልሔም ምናልባትም በራሳቸው ቤት እየኖሩ ነበር:: በቤተልሔም መቆየት ለምን እንደፈለጉ አልተነገረንም:: ይሁን እንጂ እነርሱም ሆኑ ልጃቸው እንደ ተፈጸመ በሚታሰበው ሴሰኛ ነት ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችለውን ስድብ ናዝሬት ተመልሶ ከመጋፈጥ ይልቅ እዚያ መሆኑ ይበልጥ የተመቸ ይሆናል:: በተጨማሪም ዮሴፍ አናጢ እንደ መሆኑ መጠን የናዝሬትን ያህል በቤተልሔምም ሥራ ማግኘት ይችላል::

ጠቢባኑ ከዮሴፍና ከማርያም ቤት እስኪደርሱ ድረስ ኮከቡን ተከተሉ:: ይህ የሆነው እረኞቹ መጥተው ካዩዋቸው በኋላ ብዙ ቆይቶ እንደ ነበር ግልጽ ነው:: ሄሮድስ ከሁለት ዓመት በላይ የሆናቸውን ወንድ ልጆች ሁሉ መግደለ ፈልጓል:: በመጨረሻ ሕፃኑን ሲያዩ በጣም ደስ አላቸው:: ተንበርክከው በመስገድ የከበሩ ስጦታዎችን አቀረቡለት:: ስጦታዎቹ ራቅ ብሎ ያለውን የአገራቸውን ባለጸጋነት የሚመሰክሩ

ነበሩ::[16] ስጦታው ለንጉሥ ያላቸውን አክብሮት የሚገልጡበት ነበር:: እግዚአብሔር የልጁን ማንነት ያስመሰከረበትም መንገድ ነበር:: ምንም እንኳ የኢየሱስ መወለድ በናዝሬት ተድበስብሶ የነበረ ቢሆንም ሰማይ ራሱ ግን አምላክነቱን እየመሰከረ ነበር:: በተጨማሪም ኢየሱስ መጀመሪያ በአሕዛብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘቱ ጠቢባኑ ምስክር ይሆናሉ:: ይህ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን አመልካች ነው::

**§ 15**
**ኢየሱስ ወደ ግብፅ መወሰዱ**
**(ማቴ 2፥13-18)**

[13]ጠቢባኑ ከሄዱ በኋላ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣ «ተነሥ! የምትመለስበትን ጊዜ እስካስታውቅህ ድረስ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ በመሸሽ በዚያ ቆይ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይሻልና» አለው [14]ስለዚህም ዮሴፍ ተነሣ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ፤ [15]በዚያም ሄሮድስ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ኖረ:: በዚህም፣ «ልጄን ከግብፅ ምድር ጠራሁት»[u] በማለት እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት የተናገረው ቃል ተፈጸመ::

[u]15 ሆሴዕ 11፥1

ሄሮድስ በ4 ዐቅ.ክ ቆስሎና አካሉ ተልቶ እጅግ ዘግናኝ ዓይነት አሟሟት ነበር የሞተው:: (Josephus, *Ant.* 17. 146-192):: አይሁድ እንደሚጠሉትና ሞቱን ለማየት ይጓጉ እንደነበረ ያውቅ ነበር:: ስለዚህም ከመሞቱ በፊት ታላላቅ የአይሁድ ሰዎችን በሙሉ ካስከበበ በኋላ ሒፖድሮም በሚባል ቦታ እንዲጠበቁ አደረገ:: በሚሞትበት ቀን የሚያለቅስ ሰው እንዳይጠፋ እርሱ በሚሞትበት ዕለት ይጠበቁ የነበሩት ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ:: በጣም ደስ የሚለው እርሱ ሲሞት እነ

[16] የቀረቡት ስጦታዎች ሦስት ዓይነት ስለ ነበሩ ጠቢባኑ የግድ ሦስት ነበ ማለት አይደለም:: ይሁን እንጂ ጃስፖር፣ ሜልኮየርና ቤልሳጥር ይባ እንደነበር ትውፊት ይናገራል::



ታላላቅ የአይሁድ ሰዎች በሙሉ እንዲፈቱ አዘዘች:: የሚገርመው ደግሞ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ለሄሮድስ የተከበረ የቀብር ሥርዓት ማድረጋቸው ነበር::

እንግዲህ ይህ ታሪካዊ ዳራ በእዚህ ለሚሆነው መድረኩን ያመቻቻል:: ለመሞት እየጣጣረ የነበረው ሄሮድስ ቀውስ ጨካኝና በርጋጋ ሆኖ ነበር:: አዲስ የተወለደው ሕፃን ሌላው ቢቀር በተጣመመው የሄሮድስ አስተሳሰብ ለመንግሥቱ ትልቅ ስጋት ፈጥሮ ነበር:: ሕፃኑን ማስወገድ ነበረበት:: መልአኩ ዮሴፍን ባስጠነቀቀው ጊዜ ጨለማን ተገን በማድረግ ቤተሰቡን ይዞ ወደ ግብፅ አመራ::

ምንም እንኳን በዘልማድ በግብፃውያን አይሁዶች በ150 ዓ.ቅ.ክ የታነጸው ቤተ መቅደስ ወደ ነበረበት ሞቶሪያ ወደሚባል ቦታ እንደሄዱ ቢናገርም የግብፅ ድንበር ሰባ አምስት ማይል ርቀት ብቻ ነበር:: በዚያን ዘመን ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ አይሁዶች በግብፅ ይኖሩ ነበር:: አብዛኛው ማኅበረሰብ በተለይም አሌክሳንደሪያ ለአይሁድ የተመቸ ነበር:: ስለዚህም ወደዚያ በሄዱ የሚቀበሉዋቸው የአይሁድ ማኅበረሰብ በቀላሉ ማግኘት ይችሉ ነበር::

ማቴዎስ እንደሚነገረን ይህ ሁነት በሆሴዕ 11፥1 ላይ፣ «ልጄን ከግብፅ ጠራሁት» ተብሎ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ ነው:: ይሁን እንጂ ችግሩ ሆሴዕ 11፥1 በግልጽ የሚናገረው ስለ እስራኤል ሕዝብ እንጂ ስለ መሲሑ አለመሆኑ ነው:: እንዲያውም ሆሴዕ 11፥2፣ «እስራኤልን አብዝቼ በጠራኋቸው ቁጥር፣ አብዝተው ከእኔ ራቁ፤ ለበዓል አማልክት ሠው፤ ለምስሎችም ዐጠኑ» ይላል:: ማቴዎስ ይህን ከዐውደ ሐሳቡ ነጥሎ በማውጣት ተገቢ ባልሆነ መልኩ ለመሲሑ አውሎት ይሆን? አይደለም፣ ማቴዎስ ሆሴዕ 11፥1ን የወደፊቱን እንደሚያመለክት ትንቢት አድርጎ አልወሰደውም:: ሆሴዕ ስለ መሲሑ ትንቢት እየተናገረ ነው ማለቱ አልነበረም:: ይልቁንም ኢየሱስ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚወክልና በሁለቱ መካከል አጋጣሚ መባል ከሚችል የበለጠ

አንዳንድ ተመሳሳይ ነገሮች በእርግጥ መኖራቸውን ማመልከቱ ነበር:: ማቴዎስ የኢየሱስን ሕይወትና የእስራኤልን ሕይወት ሲያወዳድር ሁለቱም ግፍ የተፈጸመባቸውና ሁለቱም በእግዚአብሔር ወደ ግበፅ መጠራታቸውን ይገነዘባል:: በሌላ አነጋገር ማቴዎስ ከሆሴዕ ትንቢት በመነሳት ኢየሱስን እያየ አይደለም:: ይልቁንም ከኢየሱስ በመነሣትና ወደ ኋላ በመመልከት ከእስራኤል ሕይወት ጋር ተጓዳኝ የሚሆኑ ሁኔታዎችን ይመለከታል:: ማቴዎስ የሆሴዕ 11÷1ን ቀጥተኛና ታሪካዊ ትርጉም በፍጹም አልካደም::[17]

ማቴ 2÷16-18

16ሄሮድስ ጠቢባኑ እንዳታለሉት በተረዳ ጊዜ በጣም ተናደደ:: ከጠቢባኑ በተነገረው መሠረት ዕድሜያቸው ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች የሆኑትን የቤተልሔምንና የአካባቢዋን መንደሮች ወንድ ልጆች ሁሉ ልኮ አስገደለ:: 17በዚህም በነቢዩ በኤርሚያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤ 18የልቅሶና የታላቅ ዋይታ ድምጽ፣ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤ መጽናናትም አልቻለችም፤ ልጆቿ ሁሉ አልቀዋልና»::

መልአክ ለዮሴፍ ወደ ግብፅ እንዲያመልጥ በሕልም ነገረው:: ጠቢባኑ ወደ አገራቸው ሲመለሱ በኢየሩሳሌም በኩል እንዳያልፉ መልአክ አስጠንቅቆአቸዋል:: በዚያን ዘመን ሄሮድስ በዓለም እጅግ ከፍተኛ ኃይል ከነበራቸው አንዱ ነበር:: አእምሮው የተቃወሰና ጨካኝም ነበር:: ጠቢባኑ አለመመለሳቸውን ሲረዳ ሄሮድስ እንደ ተታለለ ገባው:: ስለዚህ የቤተልሔምንና የአካባቢዋን ሕፃናት እንዲገድሉ ወታደሮቹን ላከ:: ወታደሮቹ እንዲፈጽሙት የታዘዙት ተግባር ጭካኔ የሞላበትና ዘግናኝ ነበር:: ይሁን እንጂ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት እንደ ተገደሉ

[17] በT.L. Howard የቀረበውን "The Use of Hosea 11:1 in Matthew 2:15: An Alternative Solution." *BibSac* 143 (Oct 1986): 314-328 እጅግ በጣም ጥሩ መግለጫ ይሰ::



ማሰብ የለብንም:: ቤተልሔምንና የአካባቢዋን ሕዝብ ብዛት ግምት ውስጥ በማስገባት ስንመለከተው ሄሮድስ ያስገደላቸው ሕፃናት ከ20 እጅግም የበለጠ አይሆኑም::

ጆሴፈስ ስለዚህ ሁሉ ሁኔታ የተናገረው የለም:: ዝምታው ማስገረሙ እንዳለ ሆኖ፣ ሄሮድስ በተለይም የአእምሮ ጤንነቱን እያጣ በመሰለበት በዘመኑ ማብቂያ አካባቢ ከፈጸማት አሰቃቂ ተግባሮች ጋር ሲወዳደር ይህ ለዘብ ያለ እርምጃ ነበር:: ለምሳሌ ያህል መንግሥቱን ይወስዱብኛል ብሎ በመፍራት ሄሮድስ ከወንድ ልጆቹ በርካቶቹን አስገድሎ ነበር:: ሌላው ቀርቶ የገዛ ሚስቱን ማሪያምኔን እንኳ አስገድሎአል:: በዚህ ሰው እጅ የሞቱት በጣም ብዙ ከመሆናቸው አንጻር የእነዚህ ጥቂት ሕፃናት መገደል እምብዛም ትኩረት የሚሰጠው አይደለም:: ከዚህም በላይ ለሚተርከው ትረካ በጣም ወሳኝ ሆኖ ካላገኘው በቀር ጆሴፈስ ከክርስትና ጋር የተያያዘን መረጃ በቸልታ እንደሚያልፈው ይታወቃል:: የሚጽፈው ስለ ተነሣው አዲስ የአይሁድ ሃይማኖት የማወቅ ፍላጎት ለሌላቸው ለሮማውያን አንባቢዎች ነበር:: ስለዚህም ጆሴፈስ ይህንን የሕፃናት መጨፍጨፍ ሁኔታ ሳያሳፍረው መቅረቱ አስገራሚ አይሆንም::

ከዚህም ባሻገር ማቴዎስ ጽሑፉን በትንቢት ያስደግፋል:: በቤተልሔም ተፈጽሞ የነበረውን የሕፃናት ግድያ፣ በኤርምያስ 31÷15 «ድምጽ በራማ ተሰማ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች» የሚለው ትንቢት ፍጻሜ እንደ ሆነ ያያል:: ራማ ከኢየሩሳሌም ስሜን አምስት ማይል ርቃ የምትገኝ ትንሽ መንደር ነበረች:: የራሔል ልጆች ኤፍሬም፣ ምናሴና ብንያም ናቸው:: እነዚህ ሦስት ነገዶች በሰሜናዊው ይሁዳና በሰማርያ በነበረው ክልል ሰፍረው ነበር::

መጀመሪያ ላይ ይህ ትንቢት ከኢየሩሳሌም መፍረስ 586 ዓ.ቅ.ክ በኋላ የተደረገውን የባቢሎንን ምርኮ የሚመለከት ነበር:: የይሁዳ ሰዎች ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ ከዚያም ወደ ባቢሎን ሲወሰዱ መጀመሪያ

በሚያልፉባት መንደር በራማ የልቅሶ ድምፅ ተሰምቶ ነበር። ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ ይህ ሁኔታ ልጆች ሲሞቱ የተደረገውን ልቅሶ ይመስለታል። ስለሆነም ከዚህ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ተጠቅሷል። በዚሁ አጠቃላይ አካባቢ የነበረችው የቤተልሔም ከተማም እንዲሁ ልጆቿን አጥታለች። ማቴዎስ በኤርምያስ 31÷15 ላይ ያለው ሁኔታ በእርሱ ሕይወት የተፈጸመውን እንደሚያንጸባርቅ እንጂ በኢየሱስ ሕይወት የተፈጸመ ትንቢት እንደሆነ አይናገርም።

ማቴዎስ የተለመደውን የረቢዎችን (የመምህራንን) አተረጓጎም መንገድ እየተከተለ ነው። ይህ ዓይነቱ አተረጓጎም ለእኛ እንግዳ ሊሆንብን ቢችልም በአይሁድ ዘንድ ግን በጣም የተለመደና ተቀባይነት ያለው ነበር። ከዚህም በላይ ማቴዎስ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ይረዳ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ሚና ችላ ማለት የለብንም። ምናልባትም ኢየሱስ ራሱ ከእነዚህ ክፍሎች አንዳንዶቹን ለደቀ መዛሙርቱ አብራርቶላቸው ይሆናል (ሉቃ 24÷27 ጋር ያነ)። በመጨረሻም፣ ኢየሱስ በእስራኤል ተምሳሌትነቱ የእነዚህን ክፍሎች ጥልቅና የተሟላ መረዳት በእርግጥ ይወክላል።

**§ 16**
**ወደ ናዝሬት መመለስ**
**(ማቴ 2÷19-23**
**ሉቃ 2÷39)**

ማቴዎስ ኢየሱስ በግብፅ ስለነበረው የስደት ቆይታ ይገልጻል። ሉቃስ ግን ወደ መቅደስ ወስደው በእግዚአብሔር ፊት ካቀረቡት በኋላ ቤተሰቡ ወዲያው ወደ ናዝሬት መመለሱን ብቻ ነው የሚናገረው። ማቴዎስ በጻፈው ሉቃስ አይስማማም ማለት ሳይሆን የኢየሱስን ሕይወት ዝርዝር ጉዳይ በመተው ታሪኩን ጠቅለል ማድረግ ፈልጎ ማለት ነው።

ማቴ 2÷19-23

[19]ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ
ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣ [20]ተነሣ፣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ
ወደ «እስራኤል ምድር ተመለስ፤ ሕፃኑን ለመግደል የሚሹት
ሞተዋልና» አለው። [21] ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን
በመያዝ ወደ እስራኤል ምድር ተመለስ፤ [22]ነገር ግን
አርኬላዎስ በአባቱ በሄሮድስ ቦታ በይሁዳ መንገሡን በሰማ ጊዜ ወደዚያ መሄድ ፈራ።
ጌታ በሕልም ስላስጠነቀቀው ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ፤ [23]ናዝሬት ወደምትባል ከተማም
ሄዶ መኖር ጀመረ። በዚህም በነቢያት «ናዝሬዊ ይባላል» ተብሎ የተነገረው ትንቢት
ተፈጸመ።

ሄሮድስ የሞተው በ4ዓ.ቅ.ክ መጋቢት ወይም ሚያዚያ ወር ነበር። ጆሴፈስ አሟሟቱ ምን ያህል ዘግናኝ እንደ ነበር በዝርዝር ገልጧል (*Ant.* 17. 168-192)። በዐመፅና በክፋት ከተሞላ ሰው የሚጠበቅ የሕይወት ፍጻሜ ነበር። አርኬላዎስ የገሊላና ከዮርዳኖስ ማዶ ያለው አገር (ፔሪያ) ገዢ እንዲሆን ሄሮድስ ተናዝዞ ነበር (Josephus, *Ant.* 17. 146)። በኋላ ግን አእምሮውን ስቶ ሞት አፋፍ ላይ እያለ ምናልባትም በእግዚአብሔር ሉዓላዊ አሠራር ኑዛዜውን ለወጠ። አርኬላዎስ ይሁዳን እንዲገዛ፣ ሄሮድስ አንቲጳስን ደግሞ ወደ ገሊላና ከዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው አገር (ፔሪያ) እንዲዛወር አደረገ (Josephus. *Ant.* 17. 188-189)። ይህ ግምት የሚሰጠው እርምጃ ነበር። አርኬላስ ተንኰለኛና ሥልጣን ፈላጊ ሰው ነበር። አባቱ በሕይወት እያለ እንኳ ዙፋኑን ለመንጠቅ ብዙ ጊዜ ሙከራ አድርጐ ነበር። በኢየሩሳሌም ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የእርሱን ሥልጣን የሚቃናቀኑ 3000 ሰዎችን ቤተ መቅደስ ውስጥ አስገደለ (Josephus, *Ant.* 17. 213-218)። ቤተሰቡን ይዞ አርኬላዎስ ወደሚገዛው አገር መሄድ ለዮሴፍ በጣም አደገኛ ይሆናል። ስለዚህም እግዚአብሔር አርኬላዎስን ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲዛወር አደረገ። ይህም ዮሴፍን ማቴዎስ የነቢያት ቃል ፍጻሜ አድርጎ ወደሚመለከተው ወደ ናዝሬት እንዲ[illegible]

ናዝሬት ኋላ ቀርና በግብርና የሚተዳደሩ ሰዎች የሞሉባት ስፍራ ነበረች:: ንግድ ከሚያካሂዱ አሕዛብ ጋር በየጊዜው ይገናኙ ነበር:: ይህች ትንሽ ከተማ ከኢየሩሳሌም ከደቡባዊው ገሊላ ባሕር ጫፍ በምዕራብ አቅጣጫ 29 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ነበር የምትገኘው:: እንደ ገቡቴ በአሥራ አምስት የገሊላ ተራራዎች ተከባ ተሰውራ ተቀምጣለች:: ሰማዩ ጥርት ባለበት ቀን ከዚህ አካባቢ ከረብታ ጫፍ ላይ ቢወጣ 48 ኪ.ሜ. ያህል ዙሪያ ገባውን ማየት ይቻላል::

የገሊላ ሰዎች ላይ በርካታ አሉታዊ ትችትና ነቀፋ ይሰነዘር ነበር:: ከኢየሩሳሌም ጋር ስትወዳደር ናዝሬት ግምት የሚሰጣት ስፍራ አልነበረችም:: ናትናኤልም ይህንኑ ናዝሬት ይሰጣት የነበረውን የንቀት አመለካከት ነበር የገለጠው (ዮሐ 1÷46):: በዘመኑ በነበረው የአነጋገር ዘዬ አንጻር  የአነጋገር ፈሊጣቸው የባላገር ዓይነት ነበር:: ገሊላ በተለይም ቀናተኞች በሚባሉት ይካሄድ የነበረው የፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መፋፋሚያ ቦታ ነበረች:: ይህም በኢየሩሳሌም በኩል ለሚሰነዘርባቸው ትችት የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል:: በተጨማሪም በአሕዛብ የተከበቡ በመሆናቸው ሕግን በተለይም፣ የአባቶች ወግ በመፈጸም ረገድ የኢየሩሳሌም አይሁድን ያህል ጠንቃቆች አልነበሩም:: እንግዲህ ዋናው ነጥብ ከእንዲህ ዓይነቱ ከተናቀና አጠያያቂ ከሆነ ስፍራ የአይሁድ መሲሕ ይመጣል ተብሎ በፍጹም የማይጠበቅ ነበር ማለት ነው:: እንዲያውም በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ አንድም ነቢይ ከገሊላ ተነሥቶ አያውቅም ይሉ ነበር (ዮሐ 7÷52):: ይህ ግን ትክክል አልነበረም:: ዮናስና ምናልባትም ናሆም የተወለዱት በገሊላ ነበር፤ ኤልያስና ኤልሳዕም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው አገልግሎት አገልግለው ነበር:: ስለሆነም መሲሑ ከዚያም ሊነሣ ይችል ነበር::

ማቴዎስ ይህን ሁሉ አንድ እርምጃ ወደፊት ወስዶታል:: ኢየሱስ ወደ ናዝሬት ያደረገው ጉዞ የትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ዘግቧል:- «ናዝራዊ ይባላል» ብሏል:: የቻላችሁትን ያህል ብትፈልጉም ይህን ዐረፍተ ነገር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ማግኘት አትችሉም:: ስለሆነም ማቴ-ዎስ ከትንቢት እየጠቀሰ ሳይሆን ሁኔታውን በተዘዋዋሪ መንገድ «ከነቢያት» ጋር እያያዘው ነው ወደሚል መደምደሚያ እንመጣለን:: እንዲያውም የአንድን «ጥቅስ» ምንጭ ለመጥቀስ ማቴዎስ በብዙ ቁጥር «ነቢያት» በማለት የተናገረው በዚህ ቦታ ብቻ ነው:: ዋናው መሠረታዊ ነጥብ ማቴዎስ በቀጥታ እየጠቀሰ ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የታወቀ ዐቢይ ሐሳብ እያቀረበ መሆኑ ነው::[18] ምናልባትም ማቴዎስ፣ «ናዝሬት» የሚለውን ቃል ቅኔያዊ በሆነ መንገድ ስለ መሲሑ ለመግለጽ እየተጠቀመበት ነው:: ናዝሬት የሚለው ቃል የመጣው «ቅርንጫፍ» (ኔዘር - nezer) የሚል ትርጉም ካለው ከዕብራይስጥ ቃል ነው:: ስለ መሲሑ ለመናገር ይጠቀሙባቸው ከነበሩት ተለዋጭ ዘይቤች አንዱ ነው (ኢሳ 11÷1):: ቅርንጫፍ የሚል ትርጉም ያለው ሌላው ቃል ደግሞ ዘማች (Zemach)  የሚለው ነው:: ይህኛው ይበልጥ ጠንከር የሚል መሲሐዊ አንድምታ አለው (ኤር 23÷5፤ 33÷15፤ ዘካ 3:8፤ 6÷12):: በእንዲህ ያለ የቃሉን ጥልቅ ትርጉም ፈልፍሎ የማውጣት መንገድ ማቴዎስ የዳዊት ቅርንጫፍ (ማለት መሲሑ) በናዝሬት ማደጉን ያመለክታል:: ምንም እንኳ ናዝሬት መሲሑ ያደገባት ከተማ መሆኗ አስደናቂ ቢሆንም ማቴዎስ ይህ ሊሆን እንደሚችል ነቢያት በቅድሚያ አላመለከቱም ማለት እንዳልሆነ ያሳያል::

**§ 17-19**
**የኢየሱስ ዕድገት**
**(ሉቃ 2÷40-52)**

ከዚህ ገለጻ በስተቀር ስለ ኢየሱስ የወጣትነት ዘመን ምንም የተነገረ ነገር የለም:: ኢየሱስ ተአምር የማድረግ ችሎታውን አንዳንድ አላስፈላጊ ነገሮችን ለማከናወን እንደ ተጠቀመባቸው በብዛት የሚያመለክቱ ጥቂት

[18] W.B. Tatum, "Matthew 2:23: Wordplay and Misleading Translations," *BT* 27/1 (Jan 1976): 135-138.

የአዋልድ ሥነ ተረቶች አሉ (ለምሳሌ *Mary, Protevangelion Infancy*)፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ከወንጌል ዓላማም ሆነ ከጌታ ባሕርይ አንጻር በፍጹም ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አጭር ትረካ እንኳ በወጣትነት ዘመኑ ኢየሱስ ክብርና ጥበብ እንደ ነበረው ነው የምናነበው፡፡ ባር ሚትጽቫ[19] (bar mitzvah) ከሚባለው የዕድሜ ወቅት ሲደርስ በተለየየበትም ቀን ቢሆን ኢየሱስ መለኮታዊ ማንነቱንና መሲሐዊ ዓላማውን ይገነዘብ እንደ ነበርም በግልጽ እንገነዘባለን፡፡

ቁጥር 49 ለምንባቡ ቁልፍ ነው፡፡ በዚህ ቁጥር ዙሪያ በሚያጠነጥኑ ሦስት ዐበይ ሐሳቦች ላይ ማተኮር ይገባናል፡፡ መጀመሪያው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ነው (ሉቃ 1÷32፣35፤ 3÷22፤ 4÷3፣9፣41፤ 8÷28፤ 9÷35፤ 10÷22፤ 20÷13፤ 22÷70 ጋር ያነ)፡፡ ማርያም ዮሴፍን አባቱ እንደ ሆነ አመልክታለች (ቁ 49)፡፡ ኢየሱስ ግን እውነተኛው አባቱ እግዚአብሔር እንደሆነ ያስገነዝባታል (ቁ 49)፡፡ ሁለተኛው ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስ በሰጣቸው መልስ መደነቃቸውና ግራ መጋባታቸው ነው (ቁ 50)፡፡ ኢየሱስ ገና ሰዎችን ማስደነቅና ግራ ማጋባቱን ይቀጥላል (ሉቃ 4÷22፣32፣36፤ 5÷26፤ 8÷25፣56፤ 9÷7፣43፤ 11÷14፤ 24÷22፣41)፡፡ ሦስተኛው ኢየሱስ በመለኮታዊ ምሪት መንቀሳቀሱ ነው፡፡ ኢየሱስ በአባቱ ቤት መገኘቱ አስፈላጊ (*dei*) መሆኑን ተናገረ፡፡ በአገልግሎቱ ሁሉ ኢየሱስ የሚመራው በመለኮታዊ ምሪት ነበር (ሉቃ 4÷43፤ 9÷22፤ 13÷33፤ 17÷25፤ 19÷5፤ 19÷5፤ 22÷37፣42፤ 24÷7)፡፡ ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ኢየሱስ ማርያምና ዮሴፍ ለነበራቸው የወላጅነት ሥልጣን የሚታዘዝ ነበር (ቁ 51)፡፡

[19] ባር ሚትጽቫ ከመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ይልቅ በኋላ እየተለመደ የመጣ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን በኢየሱስ ዘመን እንኳ በአንድ ልጅ ሕይወት ከልጅነት ወደ ዐዋቂነት ሽግግር የሚያደርግበትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚመጣ መብትና ኃላፊነት የሚቀበልበት ወቅት መኖሩን የሚያመላክት ፍንጭ እንደ ነበር ማሰብ ይቻላል፡፡



[40]ሕፃኑም እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤ በጥበብ ተሞላ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበር፡፡ ሉቃ 2÷40

ኢየሱስ በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ቤተ መቅደስ ውስጥ ስላደረገው የሚናገረው ታሪክ፣ በተናጠል አልቀረበም፡፡ በአካል፣ በማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት ስለ ማደጉ በሚናገሩት ሁለት መግለጫዎች መካከል የገባ ነው (ቁ 40 እና 52)፡፡ ኢየሱስ ስላሳለፈው ሠላሳ የፀጥታ ዓመት ጥቂት ፍንጭ የምናየው ከሉቃስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ወቅት ወይም ገጠመኝ መመረጡ ተገቢ ነው፡፡ ወሳኝ በሆነ የኢየሱስ ሕይወት ወቅት ነበር ይህ የተፈጸመው፡፡[20] ከልጅነት ወደ ሙሉ ሰውነት ሽግግር እያደረገ ነበር፡፡ በኢየሱስ ሕይወት ማንነቱ ግልጽ ያልሆነበት አንድም ጊዜ አልነበረም፡፡ ለወላጆቹ በተወለደ ጊዜ ተነግሮአቸዋል፡፡ በዕድሜው ወደ ዐሥራዎቹ ዓመታት ሲሸጋገርም ይህን ተረድቶ ነበር፡፡

ይህ ሁኔታ በሉቃስ ወንጌል ያሉ በርካታ ዐቢይ ሐሳቦችን ያንጸባርቃል፡፡ ለምሳሌ ወንጌሉ የሚጀምረውም ሆነ የሚያበቃው በኢየሩሳሌም ነው፡፡ የሉቃስን ሰፋ ያለ ዓውድ ሊያመለክቱ የሚችሉ የታሪኩን ዋና ዋና አላባውያንን ማለትም ፋሲካን፣ ሦስቱን ቀኖች፣ እና ያለቦታው ኢየሱስን መፈለጋቸውን መጽሐፉ ብዙውን ጊዜ ያካትታል፡፡[21] በሌላ አነጋገር የኢየሱስ የሙሉ ሰውነት ዘመን፣ ከልጅነት ዕድሜው ጋር የተጣጣመ ነበር፡፡ መልእክቱም ያው ሰውየውም ያው ናቸው፡፡

[20] በግሪኮችና በሮማውያን ሥነ ጽሑፍ ዐሥራ ሁለተኛ ዓመት በጀግኖች ሕይወት በጣም አስፈላጊ ጊዜ እንደነበር ኖላንድና ጆንሰን ይጠቁማሉ፡፡ ከልጅነት ወደ ሙሉ ሰውነት ዕድሜ በሚሸጋገሩበት ጊዜ የፈጸሙትን ጀብዱ ወይም ትኩረት የሚስብ ተግባር ማውሳት የተለመደ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ Xenophon, *Cyropaedia* 1.2.8; Josephus, *Ant.* 5, 348; Philo, *Life of Moses*, 1:21 ይመ፡፡ ይበልጥ የተሟላ ዝርዝር የተሰጠው በde Jong, "Sonship, Wisdom, Infancy: Luke 2:41-51a," *NTS* 24 (1977-78): 317-354.
[21] J.F Jansen, "Luke 2:41-52," *Int* 30 (Oct 1976): 400-404.

ሉቃ 2፥41-45

[41]ወላጆቹም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ
ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር፡፡ [42]ልጁም ዐሥራ ሁለት ዓመት
በሆነው ጊዜ፣ እንደ ተለመደው ወደ በዓሉ ወጡ፡፡
[43]በዓሉን ከፈጸሙ በኋላ፣ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም
ቀረ፤ ወላጆቹ ግን መቅረቱን አላወቁም ነበር፡፡ [44]አብሮአቸው ያለ መስሎአቸው፣
የአንድ ቀን መንገድ ተጓዙ፤ በኋላ ግን ከዘመዶቻቸውና ከወዳጆቻቸው ዘንድ
ይፈልጉት ጀመር፤ [45]ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡

ይህ በዓል ድሀው ቤተሰብ በየዓመቱ ረጅም ጉዞ የሚያደርግበት ወቅት ነበር፡፡ በዓመቱ ካሉ ሃይማኖታዊ በዓላት ከፍተኛው ነበር፡፡ ይህን በዓል በየዓመቱ በኢየሩሳሌም ለማክበር ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ ማንኛውም አይሁድ በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ እንዲያከብራቸው የሚጠበቅበት ሦስት በዓሎች ነበሩ (ዘፀ 34፥22-23)፣ እነርሱም ፋሲካ፣ በዓለ ሃምሳና የዳስ በዓል ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለብዙዎች ይህ የማይቻል ነበር፡፡ የኢየሱስ ወላጆች ቢያንስ በፋሲካ በዓል ላይ ተገኝተው ነበር፡፡

እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረቡ የመዓረግ መዝሙር የተባሉትን መዝሙሮች ይዘምራሉ (መዝ 120-134)፡፡ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የአገሬው ሰዎች በየቤታቸው ያስተናግዱዋቸው ነበር፡፡ ነዋሪዎቹ ለጋሶች ነበሩ፣ ለበዓሉ የመጡ ሰዎች ፍላጐት መጠነኛ የመሆኑን ያህል ለበዓሉ የሚወጣው ወጪ ደግሞ በጣም የተትረፈረፈ ነበር፡፡

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሆነው ወላጆቹ ዓመታዊውን የፋሲካ ጉዞ አደረጉ፡፡ ወደ «ሙሉ ሰውነት» ዕድሜ የሚሸጋገርበት በመሆኑ ይህ ለኢየሱስ ልዩ ጊዜ ነበር፡፡ አንድ አይሁዳዊ ልጅ በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ከሙሉ ሰው ዕድሜ እንደ ደረሰ ይታሰብ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ከባር ሚትጽቫ ትርጉሙም «የቃል ኪዳኑ ልጅ» ማለት ነው በዓል



ጋር ተጣምሮ ይከበራል፡፡ ሉቃስ አሁን ስለ ኢየሱስ ሲናገር ቃላት እየለወጠ እንደሆነ እናስተውላለን፡፡ እስከ አሁን ድረስ «ሕፃኑ» (ፓዶዮን - Paidion) በማለት ነበር የሚጠራው (ቁ 40)፡፡ አሁን ግን «ልጁ» (ፓይስ - Pais) ይለዋል (ቁ 43)፡፡ በዚህ ዕድሜ ያለ አይሁዳዊ ሕጉን እንዲፈጽም፣ ሙያ እንዲማርና በታላላቅ የአይሁድ በዓሎች ላይ እንዲገኝ ይጠበቅበት ነበር፡፡ በቤተ መቅደስ ተገኝቶ ሲታይ ይህ ለኢየሱስ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር፡፡ 210,000 ያህል ሰዎች በሚገኙበት በዚህ ቦታ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ መስዋዕቶችን፣ የመታጠብ ሥርዓቶችን፣ በጽሞና የሚጸልዩ ካህናትን፣ እንስሳትንና ገንዘብ ለዋጮችን ይመለከታል፡፡ የቤተ መቅደሱ ሕንፃ በተለይ ገሊላን ከመሰለ ትንሽ መንደር ለመጣ ልጅ እጅግ ግርማ ያለው ነበር፡፡

ቁጥር 43 «በዓሉን ከፈጸሙ በኋላ» ቤተሰቡ ወደ ቤታቸው ለመመለስ እንደተነሡ ይናገራል፡፡ ሆኖም ሉቃስ ቃል በቃል «ቀናቱ እንደ ተፈጸሙ» ነው የሚለው፡፡ ምናልባትም እንደ እውነቱ በዓሉ ገና ላያበቃ ይችላል፡፡ በዓሉ ሰባት ሙሉ ቀኖች ቢወስድም ሕዝቡ ግን የሚጠበቅበት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀኖች እንዲገኝ ነበር፡፡ የፋሲካውን እራት በልተው ስጦታቸውን አቅረበው፣ በበዓሉ ዋና ዋና ሥርዓቶችም ላይ ተሳትፈው ይሆናል፡፡ ኤደርሼይም (II:248-249) እንደሚለው ገና በዓሉ አላበቃም» ነበር፡፡ በዓሉ እየተከበረ ሳለ መምህራኑ ወደ አደባባይ መጥተው ሲያስተምሩ የነበሩ ቢሆንም በኋላ ግን በዚያ እንደማይገኙ ገልጿል፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ መምህራኑን በመቅደሱ አደባባይ ያገኛቸው በዓሉ እየተከበረ እያለ ምናልባትም ከሶስተኛው እስከ አምስተኛው ቀን ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ የበዓሉ የመጀመሪያ ሦስት ቀኖች ካበቁና ምርጥ የሆነው ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ አብዛኞቹ ሰዎች ወደቤታቸው ለመመለስ ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ በአጠቃላይ ከገሊላ የመጡት ከወዳጆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በአጀብ ሆነው ነበር የሚጓዙት፡፡ ዐሥራ ሁለት

ዓመት የሆነው በሳል ልጅ ከዘመዶቹና ከወዳጆቹ ጋር በአጀብ እየሄደ በዓይነ ቁራኛ ሊጠበቅ አለማስፈለጉ አስደናቂ ሊሆን አይችልም:: በዚህ የሽግግር ዕድሜ ያለ ልጅ ከሴቶች፣ ከወንዶችና ከትልልቅ ልጆች ጋር ሊሆን እንደሚችል ይገመታል::

ጉዞ ላይ የነበረው ሕዝብ የምሽት ዕረፍት ለማድረግ ሲቆም ማርያምና ዮሴፍ ልጃቸውን መፈለግ ቀጠሉ (ቁ 44):: ይህ ጠንከር ያለ ቃል ነው:: አካባቢያቸውን ሁሉ በዓይናቸው ይቃኙ እንደ ነበር ያመለክታል:: ሉቃስ ልጃቸውን አጥብቀውና ሳያቋርጡ ይፈልጉ እንደ ነበር ይናገራል::

ሉቃ 2÷46-50

[46]ከሦስት ቀንም በኋላ፣ በመምህራን መካከል
ተቀምጦ ሲያደምጣቸውና ጥያቄ ሲቀርብላቸው በቤተ
መቅደስ ውስጥ አገኙት፤ [47]የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና
በመልሱ ይደነቁ ነበር:: [48]ወላጆቹም ባዩት ጊዜ ተገረሙ፤ እናቱም «ልጄ ሆይ፣ ለምን
እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር» አለችው::
[49]እርሱም፣ ለምን «ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ
አላወቃችሁምን?» አላቸው:: [50]እነርሱ ግን የተናገራቸው ነገር አልገባቸውም::

ኢየሱስን ለማግኘት ሦስት ቀን ወሰደባቸው:: የመጀመሪያው ቀን ከኢየሩሳሌም ወጥተው የሄዱበት ነው:: ሁለተኛው ቀን እንደ ገና የተመለሱበት ነበር:: በሦስተኛው ቀን ኢየሱስን ቤተ መቅደስ ውስጥ አገኙት:: በአይሁድ አነጋገር ዘዬ መሠረት ይህ፣ «ከሦስት ቀን በኋላ» ሊባል ይችላል::

ስለ ልጅ አዋቂ የምንነጋገር ከሆነ እንግዲያውስ ኢየሱስ በሳል ጥያቄዎችን ሲያቀርብና መልሶችንም ሲሰጥ ብቻ አልነበረም:: ለጥያቄ-ዎቻቸውም መልስ እየሰጠ ነበር:: እርግጥ ነው ጥያቄ መጠየቅና መልስ መስጠት የተለመደ የአይሁድ መማሪያ መንገድ ነበር:: ሆኖም፣ ኢየሱስ ንቁ አእምሮ የነበረው ልጅ እንደ ነበር ግልጽ ነበር:: ከሃያ አንድ ዓመት በኋላ አንድ ቀን ኢየሱስ ላይ ሊፈርድበት ያለው ሐና በዚያን ዘመን ሊቀ



ካህን ነበር:: ምናልባትም እርሱ ራሱ በዚህ ምሑራዊ ክርክር ከኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ ነበር ወይ? ብለን ብንጠይቅ አግባብ ይሆናል:: ከዚህም ባሻገር በ112 ዓ.ቅ.ክ ሳይወለድ እንዳልቀረ የሚገመተው ሒላል ትውፊት እንደሚነግረን መቶ ሃያ ዓመት ኖሮአል:: ይህ ሁኔታም የተፈጸመው በ8 ዓ.ም. ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል:: ስለዚህም ሒላል ራሱ እዚያ ተገኝቶ ሊሆን ይችላል የሚል ደምሳሳ ግምት አለ:: የልጅ ልጁ ገማልያል ግን በእርግጠኝነት እዚያ ሊገኝ ይችላል::

ከጥያቄዎቹ አንዳንዶቹ ፋሲካና በመሲሑ መምጣት እውነተኛ ትርጉሙን ማግኘቱን በሚመለከት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሊሆኑ ይችላሉ:: ምናልባትም ኢሳይያስ 53ን፣ የእግዚአብሔር በግን፣ ወይም የመዝሙር 22ን ትርጉም መሠረት በማድረግ መሲሑ ስለሚገደልበት ሁኔታ አንሥተው ተነጋግረውም ይሆናል::

ቁጥር 48 ላይ ካለው የበለጠ ሰብዓዊነትን የሚያሳይ ምላሽ ማሰብ ይቻላል? ልጇ ሲጠፋበት የዚያን ዓይነት ስጋት የማይኖራት ምን ዓይነት እናት ናት? የጠፋ ልጇን ስታገኝ የማታቅፍና የማትገሥጽ ምን ዓይነት እናት ናት? እዚህ ላይ ማርያም ይህን ዓይነት ዝንባሌ አሳይታ እንደ ነበረ ፍንጭ እናገኛለን:: «ተጨንቀን» (ቁ 48) የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ከከባድ ከሕመም ጋር ተያይዞ ነው የሚቀርበው:: ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ሲፈልጉ ጉዳት ደርሶባቸዋል:: ስለዚህም ማርያም፣ «ተጨንቀን ስንፈልግህ ...» አለች::

«በአባቴ ቤት መሆን እንደሚገባኝ» የሚለውን መፈጸም እንደሚገባው ማወቅ እንደ ነበረባቸው ኢየሱስ ተናገረ:: ሌሎች ትርጉሞች ደግሞ፣ «በአባቴ ሥራ» ይላሉ:: እንደ እውነቱ «ቤት» የሚል ቃል አልተጠቀሰም:: የግሪኩ ሐረግ በሁለቱም መንገድ ሊወሰድ ይችላል:: ይሁን እንጂ ማርያም የጠየቀችው የኢየሱስን አድራሻ እንደ መሆኑ መጠን የእርሱም መልስ ከዚያው ጋር የተያያዘ እንደሚሆን ማሰብ ምክንያታዊ ይሆናል::[22]

[22] Also the preposition *en* generally refers to location.

በእርግጥም ይህ ለማመን የሚከብድ ታሪክ ነው:: በሉቃስ በኩል ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የሰፈረ የኢየሱስን ቃል እንሰማለን ደግሞ መጀመሪያ ጊዜ ስለ ራሱ የነበረውን «የመሲሐዊ ግንዛቤ» ፍንጭ እንገነዘባለን:: ገና በዐሥራ ሁለት ዓመቱ እንኳ እውነተኛ አባቱ ማን መሆኑን ያውቅ ነበር:: መሠረታዊ ተግባሮቹም ምንና ምን እንደነበሩም ያውቅ ነበር::

ከቶውንም ዮሴፍ ይህንን ተረድቶ እንደሆነ አናውቅም:: ሌላው ቀርቶ እንደዚያ ያለውን እርምጃ ለመውሰድ እንኳ ደፋርና ትሑት ነበር:: ይሁን እንጂ ማርያም ደረጃ በደረጃ ከኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት እየተማረች ነበር:: እስከ ትንሣኤው ድረስ እርሷም እንኳ ሙሉ በሙሉ መረዳት ማግኘት አልቻለችም ነበር:: ሌላ ማንም የተረዳ ሰው ስለ መኖሩም እርግጠኞች አይደለንም::

ሉቃ 2÷51-52

[51]ከዚያም ከብርስቸው ወደ ናዝሬት ወረደ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር:: እናቱም ይህን ሁሉ ነገር በልቧ፣ ትጠብቀው ነበር:: [52]ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ::

የኢየሱስ መለኮትነት ከተረጋገጠ በኋላ ሰብዓዊነቱም እንዲሁ ጐልቶ ወጣ:: ፍጹም በሆነ ትሕትና ኢየሱስ ፍጹም ላልሆኑ ወላጆች ታዘዘ:: ሰብዓዊ ባሕርዩ በመታዘዙ በግልጽ ይታይ ነበር:: በእግዚአብሔር የተሰጠ ሥልጣንን ኢየሱስ ይገነዘብ ነበር:: በተገቢው መንገድ ሥልጣን ለተሰጣቸው የማንታዘዝ ከሆነ ለእግዚአብሔርም መታዘዝ አንችልም::

ማርያም እነዚህን ነገሮች ሁሉ በልቧ ትይዝ እንደነበር በድጋሚ እንመለከታለን (ሉቃ 2÷19 ጋር ያነ):: በሚገርም ሁኔታ አስተዋይና የተረዳችውን መግለጥ የምትችል ወጣት ነበረች::



በወጣቱ ኢየሱስ ጤነኛና አዎንታዊ ዕድገት እናያለን (1ሳሙ 2÷26 እና ምሳሌ 3÷4 ጋር ያነ):: የኢየሱስ የልጅነት ዘመን ታሪክ እዚህ ላይ ያበቃል:: በውጭ ሲታይ መንፈሳውያን ወላጆች እንዳሉት እንደ ማንኛውም ሁነኛ አይሁዳዊ ልጅ ነበር:: ይሁን እንጂ መሲሕነቱን እርሱም ሆነ ማርያም ይገነዘቡ ነበር:: በማደግ ላይ እያለ በእግዚአብሔር ጥሪ መሠረት ታዋቂነት ካልነበራት ናዝሬት ወጥቶ አገር አቀፍ አገልግሎቱን እስኪጀምር ድረስ ይጠብቁ ነበር::